# የአሁኑ ዘመን የቤተክርስቲያን ተሀድሶ



ኖኤል ውድሩፍ

NOEL WOODROFFE

# የአሁኑ ዘመን
# የቤተክርስቲያን ተሃድሶ
# The Present Reformation
# of the Church

ኖኤል ውድሩፉ

Noel Woodroffe

1996 ዓ.ም.

2003 እ.ኤ.አ

*በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የቀድሞው መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉምና በተጨማሪ በቅርቡ ከታተመው አዲስ መደበኛ የመጸሐፍ ቅዱስ ትርጉም ውስጥ ነው።*

*Copyright © 1998 by Noel Woodroffe*

*All rights reserved*

*Reproduction of text in whole or in part without the express written consent by the author is not permitted and is unlawful according to the 1976 United States Copyright Act.*

*ይህ መጽሐፍ የተተረጐመው ከፀሐፊው (ከዶክተር ኖኤል ውድሩፉ) በተገኘ ሕጋዊ ፈቃድ ሲሆን ይህንን መጽሐፍ ከአሳታሚዎቹ ፈቃድ ውጭ በከፊልም ሆነ በሙሉ ማባዛት በሕግ ያስጠይቃል።*



## ማስታወሻ

ይህን መጽሐፍ ፀሐፊው ለሶስት ሴት ልጆቻቸው (ጆና፣ ኒኮላና ጃኔል) እንዲሁም የእነርሱ ትውልድና የአሁኑ ዘመን ተሃድሶ ወራሾች ለሆኑት በመታሰቢያነት ያበረከቱት ነው።

# መ ግ ቢ ያ

አሁን ባለንበት ዘመን እግዚአብሔር አስቀድሞ ያቀደውንና እንዲሆን የፈቀደውን ሃሳቡን በቤተክርስቲያን በኩል በምድር ሁሉ እየፈፀመው ይገኛል። ቤተክርስቲያን የተለያዩ የእግዚአብሔር መንፈስ እንቅስቃሴዎችን ተቀብላ በማስተናገድ አሁን ወዳለችበት ወሳኝና የዘመን ፍጻሜ ሀሳብን የያዘ መለኮታዊ ተልእኮ ወቅት ላይ ትገኛለች። ይህ ዘመን ቤተክርስቲያን ካለችበት ሃይማኖታዊ ሥርዓት፣ የእውቀትና የመረዳት ባለጠግነት ጉደሎነት በመውጣት መሆን ወደሚገባት ትክክለኛ ማንነት እንድትሸጋገር "ተሃድሶ" የሚል ለማያዊ የአዋጅ ድምፅ በምድር ሁሉ እያስተጋባ ነው።

ይህ ተሃድሶ ቤተክርስቲያንን የአሁኑን የእግዚአብሔርን ፈቃድና ሃሳብ ለመተግበር ጉልበትና ጥንካሬ ካጣችበት ከማንኛውም አይነት ሁኔታ ነጥቆ የማውጣት ብቃትና ችሎታ ያለው በሐዋርያዊና ትንቢታዊ ፀጋ እንቅሳቃሽነትና መሪነት እየተካሄደ የሚገኝ አስደናቂና አስገራሚ የዘመናችን ገሀድ ክስተት ነው። ይህን የተሃድሶ ድምፅ ከእግዚአብሔር በተቀበሉት ፀጋና ተልእኮ በምድር ሁሉ ተገልጠው በመንቀሳቀስ እየሠሩ ያሉ ሐዋርያትና ነብያት ሥራው በተፋፋመበት አውደ ውጊያ ላይ አመርቂ ተግባር እያፈፀሙ ይገኛሉ። ከነዚህ መካከል አንዱ የሆኑት ሐዋርያ ኖኤል ውድሩፍ በኢትዮጵያ ውስጥ አሁን በተግባራዊ የስራ እንቅስቃሴ ላይ ለሚገኘው የቤተክርስቲያን የተሃድሶ ስራ ፈር ቀዳጅ (Pioneer) የእግዚአብሔር ሰው ናቸው።

ሐዋርያ ኖኤል ውድሩፍ በ1988 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው በሰጡት የአጭር ጊዜ አገልግሎት ብዙ የቤተክርስቲያን መሪዎች የተሰቀቀውን የእውነት ቃልና ፀጋ በመቀበል ዛሬ በምድሪቱ ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ ያላቸው እንዲሆኑ አድርጎአቸዋል። በተጨማሪም ዶክተር ኖኤል ውድሩፍ አብረዋቸው በስራ ላይ በአንድ ኔትዎርክ (World Breakthrough Network) የሚገኙትን ነብያትና ሐዋርያት በተለያዩ አመታት ወደ ኢትዮጵያ ይዘው



በመምጣት የእግዚአብሔርን መንግስት የአገዛዝ አሠራር የተከተለ አዲስ የቤተክርስቲያን ቅርጽና ይዘት እንዲኖር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል። ይህ መጽሐፍ የወቅቱን የእግዚአብሔርን የልብ ሃሳብ በትክክል ተረድተው ተግባራዊ ለሆነ የሕይወት አካሄድና አገልግሎት የልብ ፈቃደኝነትና ዝግጁነት ላላቸው በየትኛውም የአላማችን ክፍል ለሚገኙ ሰዎች ከፍተኛ የሆነ የህይወት ሽግግርን በመፍጠር ገኘር የሆነ አስተሳሰብና መንፈሳዊ ጉልበት እንዲኖራቸው ያደርጋል። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኘው እውነትና ፀጋ ወደ አንባቢው የሚተላለፈው ከፍ ለሚል የአመለካከትና አስተሳሰብ ሽግግር የተዘጋጀ ውስጣዊ የሕይወት አቋም ሲኖር ብቻ ነው። ለተቀበሉት የወቅቱን የእግዚአብሔርን መንግስት ተልእኮ ወደ ፍጻሜ ለማድረስ ይህ መጽሐፍ እጅግ ከፍ ያለ ጠቀሜታ እንደሚኖረው ጽኑ እምነት አለን።

በዚህ መጽሐፍ የትርጉም ስራ ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረገውን ወንድም ደበበ ታፈሰን በጣም እናመሰግናለን።

ፓስተር ተክለአብ ዘሩ
Jubilee Reformation Center
(Senior Leader)
W.B.N Development
Coordinator (Horn of Africa)

# <u>ማ ው ጫ</u>

ማስታወሻ

መግቢያ

1. የተሃድሶ ትርጉም ..................................... .1

*የአሕዛብ በሚያስደነግጥ መደነቅ ይናወጣሉ*
*ማህተሞቹን መፍታት*
*ሐዋርያዊነት የተሃድሶ እንዘርት ነው።*
*የሐዋርያዊ ሽግግሮች ኃይል*

2. የአሁኑ ተሃድሶ መሠረቶች ........................... 15

3. የተሃድሶ መንፈስና የአእምሮ አቋም ከመጥመቁ ዮሐንስ የሚገኝ ትምህርት ......................... 33

*የተሃድሶ መሠረታዊ ሃሳብ*
*የተሃድሶ መርሆች ከመጥመቁ ዩሐንስ ሕይወት*
*ስተሃድሶ አስተሳሰብ ከዩሐንስ የምናገኘው ጠቃሚ ትምህርት*
*የተሃድሶ አካባቢያዊ ሁኔታ*

4. የተሃድሶ ቴክኖሎጂ ....................................... 53

*የቴክኖሎጂ ትርጉም*
*ተሃድሶና ትንቢታዊ እይታ*
*የሚሠራ ቴክኖሎጂ፡- የተሃድሶ መርሆችን አጥርቶ መመልከት*
*የተሃድሶ ተጨማሪ መርሆች*
*የተሃድሳ ቁልፎች*

5. በተሀድሶ ውስጥ ጥርመሳን የሚያስገኙ ስልቶች .................................... 79

*የተሃድሶ ሕዝብ ባህሪ*
*የተሃድሶ ውጤታማነት አንቀሳቃሽ ኃይል*
*አምስት የጥርመሳ ስልቶች*

6. ተሃድሳን ማቀጣጠል ................................. 101

*ከኢዮስያስ ጠቃሚ መርሆች*

7. የተሃድሶ ኃይል፡- ችግሩን መፍታት አህዛብን መባረክ ........................................ 125

*የችግሩ ተፈጥሮአዊ ምንነት*
*የተደባለቀችው ቤተክርስትያን "ተዘናግቶ መቀመጥ"*
*እስራኤል ሆይ ! እግዚአብሔር አምላክህን ለመገናኘት ተዘጋጅ*
*የዳዊት ድንኳን ተመልሶ መተከል*
*የድንኳኑ አራት መርሆች*

8. ስተሃድሶ የተመረጠ ትውልድ ................... 155

*በትውልዶች መካከል ማስተላለፍ*
*የተሃድሶን ትውልድ ለይቶ ማወቅ*
*ልክ በዚያ ቀን ...*

# ምዕራፍ 1
# የተሃድሶ ትርጉም

ዘመናችን የአዲስ ምዕተ ዓመት ዋዜማ ነው:: መንፈስ ቅዱስ በጥንቷ ሐዋሪያት ላይ ወርዶ ቤተክርስቲያን በኢየሩሳሌም ከተወለደችበት ከዚያ ታሪካዊ የጴንጤቆስጤ ቀን ወዲህ አለማችን በዓይነቱ ፍጹም እንግዳ በሆነ የታላላቅ ለውጦች ሞገድ ውስጥ ትገኛለች:: በምድር ላይ ዛሬ አንድ ትልቅ የእግዚአብሔር ንቅናቄ አለ:: ይህ ንቅናቄ በአንድ የተወሰነ ባህል ነገድና ጎሳ ዙሪያ ብቻ የሚያጠነጥን አይደለም:: ለአንድ የዓለም የኢኮኖሚ ማህበረሰብ የተለየ ወይም አስቀድሞ በታለመ አንድ ድርጅታዊ ችግር ላይ ያነጣጠረ አይደለም:: እግዚአብሔር በዓለም አቀፉ ቤተክርስቲያን የአእምሮ አቋም (paradigm) አስቀድሞ ተገድቦና ተወስኖ ከኖረበት ሰው ሠራሽና ባህላዊ አጥር ሰብሮ እየወጣ ነው:: ይህ የአእምሮ አቋም (አመለካከትና አስተሳሰብ) ሰዎችን በዕለት ተዕለት ኑሮአቸው ለሚያጋጥሙአቸው ማንኛውም ነገሮች ምላሽ የሚሰጡበት ነው:: ይህንን የቀደመውን አስተሳሰብና አመለካከት እግዚአብሔር በዘመኑ ተሃድሶ በመስበርና በመለወጥ ከዚህ በፊት ያልታየ አዲስና ለየት ያለ ነገር በምድር ሁሉ እያደረገ ነው::

> "ሰምተሃል፣ ይህን ሁሉ ተመልከት እናንተም የምትናገሩት አይደላችሁምን፣ የተሰወሩትን ያላወቅሃቸውንም አዲሶች ነገሮች ከዚያም ጀምሬ አሳይቼሃለሁ:: እነርሱም አሁን እንጂ ከጥንት አልተፈጠሩም እንተም:- እነሆ አውቄአቸዋለሁ እንዳትል ከዛሬ በፊት አልሰ-ማሃቸውም::"
>
> ኢሳ 48:6 -7

እግዚአብሔር በምድር ላይ አሁን እየሠራ ያለው አዲስ ነገር *መነቃቃት* (Revival) በሚል ቃል ሲጠቀለል የሚችል አይደለም። ምድርን ሁሉ ያካለለ ፍጹም የሆነ የቤተክርስቲያን ተሃድሶ እየተካሄደ ነው። ይህ "ተሃድሶ (መታደስ)" የሚለው ቃል የሚገኘው በአዲስ ኪዳን መጽሐፍ እብራውያን 9:9-10 ሲሆን ይህም ቃል ከአሮጌው ኪዳን ወደ አዲሱ የተደረገውን መዋቅራዊ ሽግግር የሚገልጽ ነው። የጌታን አዲስ መንፈሳዊ ተሃድሶ በምድር ላይ ለመግለጥ የዚህን የለውጥ አሠራር መሠረታዊ መርሆች በዚህ መጽሐፍ ቀሪ ምዕራፎች ውስጥ በዝርዝር እንመለከታለን።

ተሀድሶ የሚለው ቃል በግሪክ ዳይኦርቶሲስ (Diorthosis) ሲሆን ይህም ማለት መዋቅራዊ ለውጥ ማድረግ፣ የተሰበረውን፣ ከመስመር ያፈነገጠውን፣ መልኩ የተጨማደደውን እንደነበር አድርጎ መልሶ መጠገን ወደ ትክክለኛ ቅርጽና ሥርአት መመለስ ማለት ነው። ይህ ትርጉም ውጫዊውን ውበትና ቅርጽ ከብልሽት በፊት ወደነበረበት ሥፍራው ለመመለስ ተሸካሚውን ውስጣዊ ማገር (Skeleton) በማቃናት፣ ከፊት ለፊት ባለው (በውጫዊው ግዴታ) ላይ ተጽእኖ ያደረገውን ከጀርባ ያለ የአሠራር ጉድለት ማስተካከል ነው።

ይህ አባባል ከመንፈሳዊ ነገሮች አኳያ ሲታይ በዓለም ያለችውን የኢየሱስ ክርስቶስን ቤተክርስቲያን ውጫዊ ገጽታ ለመለወጥ በግንዛቤ፣ በአመለካከት፣ በሥነምግባር፣ በአቋም፣ በዝንባሌና በጽንሰ ሐሳብ ደረጃ ለዚያ በውጪ ለሚታይ ገጽታ ጉልበት የሚያመነጭለትን ውስጣዊ መዋቅር ፈትሾ እርማት ማድረግን ያካትታል። ጊዜው በሁሉም የክርስቶስ አካል ውስጣዊ አሠራሮች ላይ በሚደረግ ጠበቅ ያለ የለውጥ እርምጃ በኩል እግዚአብሔር ሥር በሰደደና ሁሉን አቀፍ በሆነ መልኩ የቤተክርስቲያንን ውጫዊ ገጽታ መልሶ እየቀረጸ የሚገኝበት የታሪክ ወቅት ነው። በ16ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ በማርቲን ሉተር በኩል ከተገለጠው ተሀድሶ ጋር ሲነፃፀር በስፋቱም ሆነ በጥልቀቱ ወሰን በሌለው ታላቅ ተሀድሶ ውስጥ እንገኛለን።





## አሕዛብ በሚያስደነግጥ መደነቅ ይናወጣሉ

ቤተክርስቲያን ራሷን በምድር ላይ የምትገልጽበት መንገድ ካሁን ቀደም ከሚታወቀው እጅጉን የተለየና የረቀቀ ይሆናል። በዚያው ልክ ደግሞ አለም ለኢየሱስ የምትሰጠው ትኩረትና ኢየሱስ ለሰው ልጆች ያለው ተፈላጊነት ከምን ጊዜውም ይልቅ እየጨመረና እየጎላ ይመጣል።

> " እነሆ ጉበኞች ጮኸዋል እግዚአብሔር ወደ ጽዮን በተመለሰ ጊዜ ዓይን በዓይን ይተያያሉና ድምፃቸውን ያነሣሉ በአንድነትም ይዘምራሉ። እናንተ የኢየሩሳሌም ፍርስራሾች ሆይ እግዚአብሔር ሕዝቡን አጽናንቶአልና ኢየሩሳ-ሌምንም ታድጓልና ደስ ይበላችሁ በአንድ-ነትም ዘምሩ። እግዚአብሔር የተቀደሰውን ክንዱን በአሕዛብ ሁሉ ፊት ገልጦአል በምድር ዳርቻ የሚኖሩትም ሁሉ የአምላካችን መድኃኒት ያያሉ።
>
> እናንተ የእግዚአብሔር ዕቃ የምትሸከሙ ሆይ እልፍ በሉ እልፍ በሉ ከዚያ ውጡ ርኩስን ነገር አትንኩ ከመካከልዋ ውጡ ንጹሐን ሁኑ። እግዚአብሔር ይቀድማችሁልና የእስራ-ኤልም አምላክ ይከተላችኋልና በችኮላ አትወጡም በመኰብለልም አትሄዱም።
>
> እነሆ ባሪያዬ በማስተዋል ያደርጋል ይከብራል ከፍ ከፍም ይላል እጅግ ታላቅም ይሆናል። ፊቱ ከሰዎች ሁሉ ይልቅ መልኩም ከሰዎች ልጆች ይልቅ ተጐሳቍሎአልና ብዙ ሰዎች ስለ አንተ እንደ ተደነቁ እንዲሁ ብዙ አሕዛብን ያስደንቃል ያልተነገረላቸውንም ያያሉና ያልሰሙትንም ያስተውላሉና ነገሥታት ስለ እርሱ አፋቸውን ይዘጋሉ " ኢሳ 52 : 8-15

ጌታ የሚጎበኝበት ቀን በቤተክርስቲያን ታላቅ ደስታ የሚታይበት ቀን ይሆናል። የእግዚአብሔር ዓላማ ልዩ በሆነ

የእግዚአብሔር የመጨረሻ ዘመን የተስፋ ቃል ነው። ነቢዩ በጩኸት ወደ እርሱ ላቀረበው ልመና እግዚአብሔር ድንገተኛ የቃል መልስ ሲሰጥ እናያለን።

" እናንተ የምትንቁ ሆይ አንድ ቢተርክላችሁ እንኳ የማታምኑትን ሥራ በዘመናችሁ እሠራለሁና እዩ ተመልከቱ ተደነቁ።" ዕን1:5

ከእኛ የሚጠበቀው ትልቅና መሠረታዊ ነገር አለምአቀፋዊ ራዕይ መያዝ ነው። እንግሊዝኛው ትርጉም "Look among the nations and watch" ይላል። ከጠባብ አመለካከት ወጥተን የዓለምን ሕዝቦች ወደ ሚጠቀልል አመለካከት መሸጋገር አለብን። ተሀድሶ ልብን አስፋቶ ከፍ ወዳለ እይታ መግባትን ይጠይቃል። ከአመለካከት ጠባብነትና ከእይታ ውስንነት ሰብሮ መውጣት የግድ ነው። በአዲስና የተለወጠ አመለካከት ካልሆነ በቀር ዛሬ በዘመናችን እግዚአብሔር በምድር ላይ ምን እየሠራ እንዳለ ልናውቅ አንችልም። የአመለካከት ለውጥ ያስፈልጋል። ወደዚህ ዕውቀት የሚያስገባን ትንቢታዊ መረዳት ነው እንጂ የቀደመው የራሳችን የግል ገጠመኝና ልምምድ አይደለም። በባህላዊና በጠባብ ጕሣዊ አመለካከት የተተበተበች በመዋቅራዊ በጥቃቅን (denominational) ልዩነቶች የምትታወቅ ቤተክርስቲያን በዘመነ ተሀድሶ ወደሚከሰተው ምድርአቀፍ (global) ታላቅ የእግዚአብሔር ንቅናቄ ለብሮ መግባት ይቸግራታል። እጃችንን በአፋችን ላይ የሚያስጭነን እግዚአብሔር ነው። እጅን በአፍ ላይ መጫን የሚያመለክተው ከማስተዋል አድማሳችን ውጪ የሆነን ነገር ከማየት የተነሳ በአድናቆት መመታትን ነው። ተሀድሶን ሰዎች ሊያመጡ አይችሉም። ጀማሪውም የበላይ ተቆጣጣሪውም ራሱ እግዚአብሔር ነው። አሠራሩ ከእኛ ቁጥጥር ውጪ ነው። ምን ለመሥራት እንዳቀደ ዝርዝሩን አስቀድሞ ቢያሳየንም እንኳ መሥራት በሚጀምርበት ጊዜ መናገር እስከማንችል ድረስ በአድናቆት እንሞላለን። በዘመነ ተሀድሶ ልንገባበት ቃል የተገባልን ነቢዩ እንባቆም ለእኛ ያየልን የእግዚአብሔርን ንቅናቄ ይህንን ያህል የገዘፈ ነው።





ነቢዩ ስለዚህ የመጨረሻው ዘመን ክስተት ተጨማሪ መረጃ ፍለጋ እግዚአብሔርን ደጅ ሲጠና እናያለን።

" በመጠባበቂያዬ ላይ እቆማለሁ በአምባ ላይም እወጣለሁ የሚናገረኝን ስለክርክሬም የምመል-ሰውን አውቅ ዘንድ እመለከታለሁ።"
ዕን 2 : 1

እነዚህ ለምድራችን የታሰቡላት ታላላቅ ክስተቶች "መጨረሻው" ተብሎ በሚታወቅ አንድ የጊዜ ነጥብ ላይ በእግዚአብሔር ሰዓት ተፈጻሚ ይሆናሉ። እንባቆም ሊገነዘባቸው ፈጽሞ ያልተቻሉት እነዚህ ክስተቶች በዚያ ሰዓት ለመረዳት በጣም የቀለሉ ከመሆናቸው የተነሳ ራዕዩን አንብበው በተረዱት የእግዚአብሔር ሰዎች ዘንድ ወደተግባር የሚያንቀሳቅስ ትልቅ ሩጫ ይኖራል። ራዕዩ በጊዜው ጥርት ያለና የማያሻማ ሆኖ ስለሚገለጥ ምንም ዓይነት ግራ መጋባት አይኖርም። ራዕዩ ይናገራል "እርሱም አይዋሽም"። የተሠወረ ሚስጥር በነዚያ ቀኖች አይኖርም።

" እግዚአብሔር መለሰልኝ እንዲህም አለ፡- አንባቢው ይፈጥን ዘንድ ራዕዩን ጻፍ በጽላትም ላይ ግለጠው። ራዕዩ ገና እስከ ተወሰነው ጊዜ ነው ወደ ፍጻሜውም ይቸኩላል እርሱም አይዋሽም ቢዘገይም በእርግጥ ይመጣልና ታገሠው እርሱ አይዘገይም " ዕን 2 : 2 - 3

ዋነኛው ቁልፍ ነገር ጥንታዊያኑ ነቢያት ሊያገኙት ያልቻሉትን ምስጢር ራዕዩን "አንባቢ" የሆኑ የመጨረሻው ዘመን ቅድሳን በቀላሉ የሚገነዘቡት መሆናቸው ነው። በምስጢር የተሞላው ሁሉ ምስጢር መሆኑ ያከትማል። የመጨረሻው ዘመን ትንቢታዊ ቅዱሳን እንቅስቃሴ ለቀደሙት ነቢያት ተከድኖባቸው የኖረውን ሚስጥር በትክክል በመረዳትና በማወቅ ላይ የተመሠረተ ነው። አለማወቃቸው እነዚያን እንዳይንቀሳቀሱ የከለከላቸውን ያህል ጊዜው ሲደርስ የተለቀቀው እውቀት እነዚህን ለተግባር ያወጣቸዋል። በዚህ ሐዋሪያዊና ትንቢታዊ

**" እግዚአብሔር በቤተክርስቲያን አንዳንዶቹን እስቀድሞ ሐዋሪያትን ሁለተኛም ነቢያትን ሦስተኛም አስተማሪዎችን ቀጥሎም ተአምራት ማድረግን ቀጥሎ የመፈወስ ስጦታን እርዳታንም አገዛዝንም የልዩ ልዩ ዓይነት ልሳኖችንም አድርጎአል" 1ኛ ቆሮ 12:28**

ቀዳሚነትን የሚያመለክተው ቃል በግሪክ ፕሮቶን (Proton) ይባላል:: በጊዜ፣ በሥፍራ፣ በተለማኒነት፣ በማዕረግና በደረጃ ቀዳሚ መሆን:: "ቀዳሚ" የሚለው ቃል ሐዋርያት ከሌሎች አልግሎቶች ይበልጣሉ በላያቸውም ይሠለጥናሉ ለማለት አይደለም:: አምስቱም ስጦታዎች ከእግዚአብሔር የመጡ ናቸው:: የተለያዩ የክርስቶስ ቀባት መገለጫ ደርዞች እንጂ የደረጃ ልዩነቶች አይደሉም:: ማንኛውም የክርስቶስ ክፍል ከሌላው አይበልጥም አያንስም:: በሥነመለኮታዊውም ሆነ በተግባራዊ መልኩ የሚታሰብ ጉዳይ አይደለም:: ክርስቶስ የፍጹምነት መለኪያ ነው:: አንዱ ከሌሳው ሲወዳደር ለንካላ ወይም ደካማ የሚባል ምንም ገጽታ የለውም::

"ቀዳሚ" የሚለው ቃል ሐዋሪያዊው ስጦታ ከሌሎቹ ለየት የሚልበትን አንድ ገጽታ ያመለክታል:: በሌሎች ስጦታዎች ውስጥ ያንን ያህል ጎልቶ የማይታይ የጥርመሳ ጉልበት በሐዋሪያዊው ፀጋ ውስጥ ተከማችቶ ይገኛል:: እግዚአብሔር ቤተክርስቲያንንም ሆነ አለምን ሥር ነቀል በሆነ መንገድ ለመቀየርና ወደአንድ አዲስ ክልል በትኩስ የተሀድሶ አሠራር ለማንቀሳቀስ "ቀዳሚ" የሆነውን ሐዋሪያዊ የጥርመሳ ቅባት ከሁሉ በፊት አስቀድሞ ይልከዋል:: ማርቲን ሉተር በመካከለኛው ዘመን ለነበረችው ቤተክርስቲያን ትኩስን መና ከሰማይ ያወረደ (ያዘነበ) ሐዋርያ ነበር::

ሥራን ለመሥራት (ማለትም ተግባርን ለማከናወን) ከሚወሰድ ቀዳሚነትና ተከታይነት ውስጥ "ቀዳሚ" መሆን ማለት ከሌሎች መብለጥ ሳይሆን ይችሳል:: እግዚአብሔር ሥሳሴ ወይም ሦስት አካላት በአንድ አምሳክ ነው:: መንፈስ





ቅዱስ ከኢየሱስም ከአብም በምንም የማይተናነስ አምሳክ ነው:: ቢሆንም ተግባርን ከመፈጸም አንጻር ከእነርሱ መካከል ራስ የሆነ መኖሩን ክርስቲያን ሁሉ ያስተውሳል:: አብ ተግባራዊ ራስ ቢሆንም ከኢየሱስና ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ በመለኮትና በሥልጣን ሙሉ በሙሉ የተካከለ ነው::

ሐዋርያት ለቤተክርስቲያን ተግባራዊ ራስ ናቸው:: ይሄም የሆነው ጥልቀ ወደሆነ ነገር ጠርምሶ መገስገስን፣ የእግዚአብሔርን ዓላማ ጥርት ባለመልኩ የማብራራትን፣ የእግዚአብሔር ኃይል በኃይማኖታዊና ፖለቲካዊ ጫጫታ ሳይገታ ወደፊት እንዲራመድ የማስቻልን ብቃት ለቤተክርስቲያን ማስታጠቅ የሚያስችሳቸው የመገንባትና የመግዛት ቅባት በሳያቸው ላይ ስላለ ነው:: ሐዋሪያዊ መለቀቅ ለእግዚአብሔር ተሀድሶአዊ ንቅናቄ እንደቀስተ ጫፍ የሚቆጠር ነው::

## የሐዋርያዊ ሽግግሮች ኃይል

ሐዋርያዊ አገልግሎት በኤፌሶን 4:11 ሳይ ከተዘረዘሩት ሌሎች የአገልግሎት ስጦታዎች ተነጥሎ የሚታይ አይደለም:: የእግዚአብሔርን ሥራ ከፍጻሜ ለማድረስ የሁሉም ድርሻና ቅንጅት አስፈሳጊ ነው:: ሐዋርያዊው ቅባት በሙሉ ጉልበት የምትንቀሳቀስን ለኬታማ ቤተክርስቲያን ለማስገኘት የሚሠራ ነው:: የመጀመሪያይቱ ቤተክርስቲያን ታሳቅ መጽሐፍ "የሐዋርያት ሥራ" ተብሎ የሚታወቅ ቢሆንም በውስጡ የምናየው ግን የሐዋርያት ብቻ ሳይሆን የሌሎች የአገልግሎት ስጦታዎችና የተራው ምዕመን በሙሉ ቅንጅትና መተጋገዝ የጋራ ሥራ የተገለጠበት መጽሐፍ ነው::

የዚህ የሐዋርያት መራሹ የተሀድሶ ንቅናቄ ኃይልና ሥልጣን የሚመነጨው እግዚአብሔር ባለፉት ዘመናት ላከናወናቸው ድርጊቶች ከተሰጠ ዕውቀናና አክብሮት ነው:: የእግዚአብሔርን የአለፉ ዘመናት ሥራዎች እርግጠኝነት ይቀበሳል፣ ያሁን እንጂ ወደ አንድ እግዚአብሔር ወደ ሚቆጣጠረው ትክክለኛ የወደፊት ጊዜ ቤተክርስቲያንን

**" በእስራኤል ውስጥ መሪዎች ስለመሩ ሕዝቡም ነፍሳቸውን በፈቃዳቸው ስለ ሰጡ እግዚአብሔርን አመስግኑ" መሳ 5 : 2**

**" እግዚአብሔር የኃይልን በትር ከጽዮን ይልክልሃል፣ በጠላቶችህም መካከል ግዛ። ከአንተ ጋር ቀድሞ በኃይልህ ቀን በቅዱሳን ብርሃን ከአጥቢያ ኮከብ አስቀድሞ ከሆድ ወለድሁህ" መዝ 110 : 2 - 3**

እውነተኛና እንቀሳቃሽ የሆነ ተሀድሶ በሰዎች አእምሮ ላይ በግድ የሚጫን ነገር አይደለም። ነገር ግን ቅዱሳን የእግዚአብሔርን ዘለዓለማዊ ሐሳብ ወደ ፍጻሜ ለማምጣት በሚደረገው መንፈሳዊ ጉዞ ላይ እንደ አንድ እጅግ አስፈላጊ የሆነ ልምምድ ቆጥረው ከራሳቸው በሆነ ሙሉ ፍላጎት ሊቀበሉት የሚገባ እውነት ነው። ነህሚያ የመራውን ተሀድሶ ስንመለከት ዕውቀትና መረዳቱ የነበራቸው ወገኖች ናቸው አዲስን ቃል ኪዳን ወደ መግባት ደረጃ የተሻገሩት (ነህሚያ 10:28)። ይህንን አዲስ ቃል ኪዳን ያደረጉት ተገድደው ሳይሆን "ትእዛዝ በራሳቸው ላይ አደረግን" (ንህምያ 10:32-33) በማለት ከራሳቸው በሆነ ተነሳሽነትና ፍላጐት ሊሆን ይህ አዲስ አቋም የሚጠበቅባቸውን የእግዚአብሔርን መንግስት ሥራ ለማከናወን ብቃት ሰጥቶአቸዋል።





# ምዕራፍ 2

# የአሁኑ ተሀድሶ መሠረቶች

እግዚአብሔር ለየት ባለ አዲስ መንገድ በምድር ላይ መንቀሳቀስ ሲጀምር ለዚያ ንቅናቄው ስም ለማውጣት ልማድ እንደሌለው እናውቃለን። ግልጽነትና ትርጉም እንዲኖረው በማሰብ ሰዎች ናቸው ለእያንዳንዱ ንቅናቄ ስያሜን የሚሰጡት። እንደዚህ ያሉ ስያሜዎች ግን ብዙውን ጊዜ የሰዎችን አእምሮ ቆልፈው በመያዝ ከአንድ የተወሰነ የአመለካከት ክልል በላይ እንዳያስተውሉ ያደርጋሉ። እግዚአብሔር ከዚያ ሠፋ ባለ ሁኔታ ተንቀሳቅሶ በዓለም ዙሪያ በአንድ ጊዜ እያሌ የተለያዩ ድርጊቶችን እያከናወነ ሳለ ከነዚህ ስያሜዎች ውስንነት የተነሳ ሰዎች እግዚአብሔርን በጠባብ ክስተቶች ዙሪያ ብቻ ሊጠብቁት ይገደዳሉ። ስለዚህ ለእግዚአብሔር ነገሮች ስያሜን በምንሰጥበት ጊዜ ስያሜዎቹ እንዳስፈላጊነቱ ሊለጠጡና ሠፋ ያለ ሐሳብን ሊያገለግሉ እንደሚችሉ ሆነው ሊቀረጹ ይገባል እንጂ አሣሪ ወይም ያለምንም ጥያቄ የምንቀበላቸው (dogma) እንዲሆኑብን መፍቀድ የለብንም። በምድር ውስጥ በተከታታይ ሁኔታ የሚገለጡትን አዳዲስ የእግዚአብሔር ትንቢታዊ ክንውኖች በየአመጣጣቸው ደረጃ ለመረዳትና ለመቀበል የሚከላከል የድንጋይ ግንቦችንና አዳዲስ ምሽጎችን በሰዎች አእምሮ ላይ ላለመገንባት በመጠንቀቅ እግዚአብሔር አሁን በዚህ ዘመን እየሠራ ላለው ነገር ግልጽና ትክክለኛ ስም መስጠት ይኖርብናል። ይህንን ሐሳብ ከግንዛቤ በማስገባት እግዚአብሔር በዚህ በእኛ ዘመን አሁን በአለማችን ላይ እያደረገ ያለውን ሥራ ለመግለጥ ብዙ የተለያዩ ስያሜዎች ተሞክረዋል። ጥቂቶቹ እነዚህ ናቸው፦

- ከዲኖሚኔሽኖች በኋላ የተከሰተው የእግዚአብሔር ንቅናቄ
- ሁለተኛው ተሀድሶ

- *ሐዋርያዊ /ትንቢታዊ የእግዚአብሔር ንቅናቄ*
- *አለማቀፋዊው የጸሎት እንቅስቃሴ*
- *ሐዋርያዊ ተሃድሶ*

እነዚህ ከላይ የተገለጡት ሰሞች እግዚአብሔር አሁን በምድር ላይ እያደረገ ያለውን እንቅስቃሴ በከፊል በመግለጥ የንቅናቄውን ገጽታዎች ከፊል ገጽታውን በማሳየት መንገድ ሁሉም ትክክል ናቸው።

በዓለም ዙሪያ በሁሉም የቤተክርስቲያን የአገልግሎት ዘርፎች በመንጸባረቅ ላይ ካሉት የአሁኑ ንቅናቄ ገጽታዎች መካከል እስቲ ጥቂቶቹን አስፍ አለፍ ብለን በአጭሩ እንዘርዝር፤ የጊዜውን የቤተክርስቲያን ተሀድሶ አጠቃላይ መልክ ለመገንዘብ ያስችሉናል ብለን እናምናለን።

***★ በእምነታችን ላይ የነበረውን ማንኛውንም ዓይነት የድንበር ድንጋይ እግዚአብሔር ስለሚያፈራርሰው ቤተክርስቲያን አጠቃላይና ሥር ነቀል የአመለካከት ለውጥ ይኖራታል።***

እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን በማንቀሳቀሰ ሐዋርያዊ የጸጋ መካፈል ውስጥ ባለው ኃይል በኩል ዓለም አቀፏን ቤተክርስቲያን ለ21ኛ ክፍለ ዘመን አዲስ ወደሆነ የአመለካከት ከፍታ (Paradigm) እያሻገራት ነው። የሐዋርያዊው (ቅባት) የውጊያ ብቃት የሚለካው ለፈሪሳዊ መናፍስት ጥሩ መሸሸጊያ የሆኑ፣ ከእድሜያቸው ርዝመት የተነሳ የጨረጨሱ ኃይማኖታዊ አመለካከቶችን ከሥር መሠረታቸው መንግሎ መጣል በመቻሉ ላይ ነው። እነዚህ የፈሪሳዊ መናፍስት ናቸው መንግሥቱ ወደፊት እንዳይገፋና እንዳያድግ ማነቆ ሆነው ለውጥን የከለከሉ።

> " የጦር ዕቃችን (ሐዋሪያዊው) ሥጋዊ አይደለምና ምሽግን ለመስበር ግን በእግዚአ-ብሔር ፊት ብርቱ ነው፤ የሰውንም አሳብ በእግዚአብሔርም እውቀት ላይ የሚነሣውን ከፍ ያለውን ነገር ሁሉ እናፈርሳለን ለክርስ-





> ቶስም ለመታዘዝ አዕምሮን ሁሉ እንማርካለን መታዘዛችሁም በተፈፀመች ጊዜ አለመታዘዝን ሁሉ ልንበቀል ተዘጋጅተናል"
>
> **2ቆሮ 10 : 4 - 6**

> " እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን መንግሥተ ሰማያትን በሰው ፊት ስለምትዘጉ ወዮላችሁ እናንተ አትገቡም የሚገቡትንም እንዳይገቡ ትከለክላላችሁ" ማቴ 23 : 13

አሮጌ አመለካከቶችን በመለወጥና በመቀየር ነው እግዚአብሔር ለዘመናችን ወዳሰበውና ደረጃ በደረጃ ወደሚገለጠው ፈቃዱ መድረስ የምንችለው።

> " *መልካም ደስ የሚያሰኝና ፍጹም የሆነውን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ምን እንደሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በአዕምሮአችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን አለም አትምሰሉ* " ሮሜ 12 : 2 (አ.መ.ት)

***★ ዘመናትን ወደ ፍጻሜ በማምጣት ረገድ እስከ ዛሬ ከነበሩት ትውልዶች ይልቅ በተሻለ አቋም ላይ የምንገኝና ታላቅ ፍጻሜ ያለን ትውልድ መሆናችንን ማስተዋል።***

ትንቢታዊና ሐዋርያዊ አገልግሎት በክርስቶስ አካል ውስጥ ዋጋ ያለውና ሁሉም ሊማረው የሚገባ የመንፈስ ቅዱስ አሠራር ነው። ዘመናችን ከሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የመጀመሪያ ወራት ፣ወዲህ ታይቶ ያልታወቀ በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ለሐዋርያዊ እና ትንቢታዊ አገልግሎት ተገቢ ትኩረትና ተቀባይነት የተሰጠበት የመሆኑ ጉልህ ምልክት እየታየ ነው። ለብዙ ዘመናት "ነቢያትን ገድለናል፣" "የተላኩትን (ማለትም ሐዋርያትን) ወግረናል" (ማቴዎስ 23:37)።

እንግዲህ አሁን እነዚህን አገልግሎቶች በድጋሚ ስለተቀበልናቸውና አምስቱም የአገልግሎት ስጦታዎች

በክርስቶስ አካል ውስጥ ሙሉ በሙሉ ተፈጻሚነት እያገኙ ስለሆነ በምድር ላይ ሊከናወን የሚጠበቀውን የክርስቶስን ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ ከመቼውም ይልቅ በተሻለ አቋም ላይ እንገኛለን። የእግዚአብሔር ሞገስ በቤተክ-ርስቲያን ላይ የሚያርፍበት የተወሰነው ጊዜና የተቀጠረለት ቀን (the set time) መጥቷል። የመጨረሻው ጠላት (ሞት) ሊመታ የመጨረሻው ጦርነት ተከፍቷል። ትንቢት የተነገረለት ከሞት ኃይል አርነት የሚወጣ አንድ ትውልድ አለ።

> **" የምሕረትዋ ጊዜ ነውና ዘመንዋም ደርሶአልና ባሪያዎችህም ድንጋዮችዋን ወድደዋልና ለመሬትዋም አዝነዋልና እግዚአ-ብሔር ጽዮንን ይሠራታልና በክብሩም ይገለጣልና ይህ ለሚመጣ ትውልድ ይጻፍ የሚፈጠርም ሕዝብ ለእግዚአብሔር እልል ይላል እግዚአብሔር ከመቅደሱ ከፍታ ሆኖ ተመልክቶአልና ከሰማይ ሆኖ ምድርን አይቶአልና ሊገደሉ የተፈረደባቸውን ያድን ዘንድ የእግዚአብሔር ስም በጽዮን ምስጋና-ውንም በኢየሩሳሌም ይናገሩ ዘንድ"**
>
> ***መዝ* (102) ፥ 14፣16፣18፣19**

### ***★ ከሞተ ኃይማኖታዊ ወግ እና ከአጥቢያ ቤተክርስቲያን ውስንነት ሥር-ነቀል በሆነ እርምጃ እያንዳንዱን የሕይወት ክልል መውረር ወደሚችል የመንግስቱ እውነታ መሸገር።***

በሳል የሆነ የዳዊት አመለካከትና አስተሳሰብ በአለም አቀፉ ቤተክርስቲያን ላይ ሥር እየሰደደ በመምጣት ላይ ይገኛል። የክርስቶስን አካል በመከፋፈል የመንግሥቱ ዕድገት በአጥጋቢ ሁኔታ ወደፊት እንዳይገሰግስ የሚከለክል ማሕበረሰባዊ፣ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ጎሳዊ (ethnic)፣ ድርጅታዊ፣ ዲኖሚኔሽናዊ (denominational) ወ.ዘ.ተ መለያየቶች ትንቢታዊና ሐዋርያዊ ጥምረት በቤተክርስቲያን ላይ በለቀቀው እሳት ተበልተው እየፈራረሱ ናቸው። የ21ኛው ክፍለ ዘመን ቤተክርስቲያን የልብ ጩኸት





ዘሙታን የተነሳን ክርስቶስ ክብሩ አለምን አጥለቅልቆ ማየት ነው። ይህንንም ከመሆን የሚከለክል አንዳች ኃይል አይኖርም።

> **" በአንተ ኃይል በጭፍራ ላይ እሮጣለሁና፣ በአምላኬም ቅጥሩን እዘልላለሁና"**
>
> **2 ሳሙ 22:30**

ወደ ገርነትዋ እየገባች ያለችው ቤተክርስቲያን ዋነኛ አትኩሮት የእግዚአብሔርን መንግሥት በምድር ላይ ማዋቀር ነው። የ21ኛው ክፍለ ዘመን አማኞች በዲኖሚኔሽን ልዩነቶች ወይም የአገልግሎት መበላለጥ ግንቦች አይለያዩም። በዚህኛው የተሃድሶ እንቅስቃሴ እግዚአብሔር በልጆቹ ልብ ያኖረው ትልቅ ጥማት በጨለማው ግዛት ላይ አለም አቀፍ እና የተቀናጀ ጦርነት ከመጀመር ወደ እውነተኛ የእርስ በርስ አንድነት መምጣትን ነው። ይህ እንዳይሆን የልዩነት ግንቦች ሁሉ መፍረስ ይኖርባቸዋል።

> **"ከዳር እስከ ዳር ከተማው እንደተያዘች መልካምችዋም እንደተያዙ ቅጥርዋም በእሳት እንደ ተቃጠለ ሰልፈኞችም እንደደነገጡ ለባቢሎን ንጉሥ ይነግር ዘንድ ወሬኛው ወሬ-ኛውን መልእክተኛውም መልእክተኛውን ሊገናኝ ይሮጣል" ኤር 51 ፥ 31፣32**

### ***★ ሠፊውን ተራ አማኝ በአገልግሎት ውስጥ ብሩህ ወደ ሆነ ተሳትፎ በማምጣት በሁሉም የሕይወት አቅጣጫ በኩል ያለውን የሰይጣናት ምሽግ ለማፈራረስ አውደውጊያውን ሙሉ በሙሉ ማስፋት።***

በሁሉም የምዕተ ዓመቱ አማኞች (millenium belivers) ሕይወት ላይ እግዚአብሔር የሐዋርያትን መንፈስ እያካፈለ ይገኛል። አምስቱ የመግዛት አገልግሎት ስጦታዎች የተሰጡት ራሳቸውን ከፍከፍ ሊያደርጉበት ለአገልጋዮቹ ሳይሆን ከመጀመሪያው ጀምሮ የስጦታዎቹ

ዓላማ በውስጣቸው ያለውን ጸጋ በማካፈል ቅዱሳንን ለአገልግሎቱ ሥራ ለማስታጠቅ ነው። በሉቃስ ምዕራፍ 10 ኢየሱስ ሰባ አማኞችን ስትራቴጂካያዊ ስሆነ መንፈሳዊ ውጊያ አስታጥቆ በዙሪያው ወዳለው አገር ሲያስማራቸው እናያለን። "በሁለት በሁለት" አቀናጅቶ እርሱ ራሱ ሊሄድ ወዳለው ከተማ ሁሉ ላካቸው (ሉቃስ 10:1)።

እነዚህ ሰባዎቹ የተላኩት ቀድመዋቸው ወደዚያው በሄዱት በዋነኞቹ አሥራ ሁለት ሐዋርያት የሥልጣንና የብቃት ልክ ነው (ሉቃስ 10ን ከማቴዎስ 10 ጋር እናነጻጽር)። እነዚህ ሰባዎቹ የሚወክሉት ለፍሬያማ ጥርመሳ እንዲያመች ሆኖ በክርስቶስ አካል ላይ የተላለፈውን የሐዋርያዊ መንፈስ የጸጋ መላት ነው። እነዚህ ሰባዎቹ በዚያ ክልል ወዳሉት የጠላት ቀጠናዎች ሰብረው በመግባት አጋንንት ወደው ከተገዙላቸው በኋላ የድል ዜና ይዘው ወደ ኢየሱስ ሲመለሱና ኢየሱስም አንድም በመመለሳቸው ሁለተኛም ከቀደሙት ዘመናት ጥበበኞች ተሠውሮ የነበረ ጥበብ አሁን ግን በሐዋርያዊ መንፈስ ለታጠቁ "ሕፃናት" በመገለጡ ሀሴት እንዳደረገ እናያለን (ሉቃስ 10:17-24)።

ጥንታዊያን ታላላቅ አባት መሪዎችም ሁሉ በዚሁ ምሳሌ ቅዱሳንን ወደ በለጠ ተሳትፎና ኃይልን የመታጠቅ ከፍታ ለማድረስ እንደሞከሩ አንብበናል። በዘሁልቁ 11 ላይ ሙሴ ለሰባ የአይሁድ ሽማግሌዎች ከመንፈሱ ሲያካፍል እናያለን። ከነዚህ ሁለቱ በሠፈር ቢቀሩም እንኳ ያንን መንፈስ ሌሎቹ እየተካፈሉ ሳለ ለእነዚህም ድርሻቸው የነበሩበት ድረስ መጣላቸው። በወቅቱ ገና ብላቴና ለነበረው ለኢያሱ የተቃውሞ ስሞታ ሙሴ የሰጠው ምላሽ በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ የተሾመን የአንድን እውነተኛ የተሀድሶ መሪ ትክክለኛና ተገቢ የልብ ይዞታ ያሳያል።

> "ሙሴም የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ ነብያት ቢሆኑ እግዚአብሔርም መንፈሱን በእነርሱ ላይ ቢያወርድ አንተ ስለ እኔ ትቀናለህን? አለው"
>
> ዘሁ 11 : 29





***★ የመንግሥቱን የገንዘብ አቅርቦት የተሻለ ለማድረግ መዋቅራዊ ለወጥን መከተል የሚያስችል ነገሮችን ወደ ፍጻሜ ለማፋጠን በሚደረገው ግፊት ላይ አስተዋጽኦ ያለው ለመንግሥቱ ሥራ ታላቅ የገንዘብ አቅርቦትን ማስለቀቅ የሚችል እምነት ይከሰታል።***

ይህ ተሀድሶ በእግዚአብሔር አመለካከትና አስተሳሰብ የተሞሉ፣ ከአንደበታቸው በሚለቀቁት የአዋጅ ቃል በኩል በዛሬይቱ ምድር ላይ ታላላቅ ትንቢታዊ ትዕዛዞች ወደመተግበር እንዲያመጡ በመንፈስ ቅዱስ የተቀረጹ የነፍናለ ዘመኑ ትንቢታዊ የአማኞች ቡድን የሚወለድበት ነው። ኢሳያስ በትንቢቱ በዘመኑ ፍጻሜ ስለሚነሳ አንድ ደማቅና የሚያበራ ትውልድ ተናገረ፤ የጽልመቱ መጠን እየጨመረ በሚመጣ ድቅድቅ የክፋት ጨለማ መካከል ዘንይለኛ ብርሃን የሚያበራ ትውልድ። መንግሥቱ የሚስፋፋበትን ሀብት ተሸክመው አሕዛብ የሚጎርፉት ወደዚህ ብርሃን ነው።

> " ብርሃንሽ መጥቶአልና የእግዚአብሔርም ክብር ወጥቶልሻልና ተነሺ አብሪ። እነሆ ጨለማ ምድርን ድቅድቅ ጨለማም አሕዛብን ይሸፍናል ነገር ግን በአንቺ ላይ እግዚአብሔር ይወጣል ክብሩም በአንቺ ላይ ይታያል አሕዛብም ወደ ብርሃንሽ ነገሥታትም ወደ መውጫሽ ፀዳል ይመጣሉ። ዓይኖችሽን አንሥተሽ በዙሪያሽ ተመልከቺ እነዚህ ሁሉ ተሰብስበው ወደ አንቺ ይመጣሉ ወንዶች ልጆችሽንም ወደ አንቺ ስለሚመለሱ የአሕዛብም (አገሮች) ብልጥግና ወደ አንቺ ስለሚመጣ አይተሽ ደስ ይልሻል፣ ልብሽም ይደነቃል ይሰፋማል" ኢሳ 60 : 1-5

***★ እንደ ባሕር ሞገድ ያለ የጸሎት ጎርፍ እና በእምነት የሆነ መጠበቅ በዓለም ዙሪያ ያሉትን የዲያቢሎስ ይዞታዎች እያስጨነቀ በሚገኝበት ባሁኑ ወሳኝ የታሪክ ወቅት ላይ ትልቁን ሚና ለመጫወት በቁጣ የተሞላ***

ዓላማ ሊጠፋ የቀረበን እሳት መልሶ ማቀጣጠል እንጂ ማዳፈን ወይም በጡረታ ማግለል አይደለም (to refire, not to retire):: የእምነት አንድነት (Unity of the faith) (ኤፌሶን 4:13) ውስጥ ካሉት ሚስጥራት አንዱ በተከታታይ ትውልዶች መካከል መንፈሳዊ መወራረስና መደጋገፍ መኖሩን ያሳያል:: ለልጁ ለሰለሞን የወደፊት ስኬታማነት አባቱ ዳዊት የራሱንና የሕዝቡን ብልጽግና አሰባስቦ በውርስ ሲያስተላልፍ እናያለን (1ኛ ዜና 28:9-21፣ 1ኛ ዜና 29:1-9):: ንጉሥ ዳዊት ገና በሕይወቱ ሳለ ልጁን ሰለሞንን በዙፋኑ ላይ ካነገሠው በኋላ የተናገረው ቃል ንግሥናንና መንፈሳዊ አመራርን አስመልክቶ በጠቅላላው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተነገሩት ሁሉ እጅግ ጠለቅ ያለ ሐሳብ ታሽከሞአል::

> **" ዛሬ በዙፋኔ ላይ የሚቀመጠውን ወራሽ ዓይኔ እንዲያይ የፈቀደ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ምስጋና ይድረሰው አለ::"**
>
> **1ኛ ነገስት : 48 (ኢ.መ.ት)**

### ★ *ተሀድሶ ብልጫ ወዳለው ሥርአት የሚያደርሰውን መንገድ ያመለክታል*

> **" በዚያም ወራት መጥምቁ ዮሐንስ መንግስት ለማያት ቀርባለችና ንስሀ ግቡ ብሎ በይሁዳ ምድረበዳ እየሰበከ መጣ በነቢዩ በኢሳያስ፡- የጌታን መንገድ አዘጋጅ ጥርጊያውንም አቅኑ እያለ በምድረ በዳ የሚጮሀ ድምፅ የተባለለት ይህ ነውና::" ማቴ 3 : 1 - 3**

> **" እኔስ ለንስሀ በውሃ አጠምቃችኋለሁ ጫማውን እሸከም ዘንድ የማይገባኝ ከኔ በኋላ የሚመጣው ግን ከእኔ ይልቅ ይበረታል እርሱ በመንፈስ ቅዱስ በእሳትም ይጠምቃችኋል:: "**
>
> **ማቴ 3 : 11**





የዮሐንስ መልእክት የመንግሥቱ መልእክት ነው (መንግሥት ስንል ስለእግዚአብሔር መንግሥት ማለታችን ነው::) ታዋቂው የላቲን አሜሪካ ሐዋርያ ሮናልዶ ቱክሲዶር እንዲህ ብለው ነበር፡- "የመንግሥቱ መልእክት የ21ኛው ክፍለ ዘመን ወንጌል ነው":: ሊመጡ ወዳሉት አዳዲስ ነገሮች ብቸኛው መግቢያ ቁልፉ (ዮሐንስ እንደሚነግረን) "ንስሐ ግቡ" የሚለው መልእክት ነው:: ንስሐ መግባት ለሚለው ሐሳብ ያገለገለው ቃል ሜታኖያ (metanoeo) የሚባል ነው:: "ሜታ" ማለት በኋላ "ኖያ" ማለት ማሰብ ነው:: ይሄም የሚያመለክተው በአሠራራችን በባህሪያችን ላይ ለውጥን እስከሚያስከትል ሆኖ የውስጥ አመለካከታችን መለወጥ የሚያስፈልገው መሆኑን ነው:: ሁብለስሜታዊ (emotional) ወይም ምትሀታዊ (mystical) ልምምድ አይደለም:: የማሰቢያ አእምሮአችንን ፈቃደኝነታችንንና የሥራ ዝግጁነታችንን ሁሉ ያሳተፈ ቀጥተኛ ድርጊት ነው:: እግዚአብሔር በዚህ ዘመን ከእኛ የሚፈልገው ነገር ምን እንደሆነ ከላይ በተገለጠልን መረዳት ላይ ተመሥርቶ መካሄድ ላለበት የተራዘመና ዘላቂ ለውጥ የተቀነባበረ የእኛ ምላሽ ነው:: ለዚች ምድር ካለው የእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር በሳል የሆኑ ሰዎች የሚያደርጉት የቅርብ ግንኙነት ነው::

የዮሐንስ ቴክኖሎጂ ይሄ ነው:: ጌታ እየመጣ ነው የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያንም አቅኑ! አዲሱ ነገር ያለምንም እንቅፋት ወደዚህ እንዲመጣ ከተፈለገ ቀጥተኛና ቆራጥ እርምጃ መወሰድ አለበት:: ዮሐንስ እየነገረን ያለው የእግዚአብሔርን ኃይልና ብርሃን በመግለጥ በኩል "ከእኔ የበረታ" ኃይል በደጅ ቀርቧል የሚል መልእክት ነው:: ወደዚህም አዲስ ኃይል መቅረቢያ ዘዴው በመንፈሳዊው አመለካከትና አስተሳሰብ በኩል ፍጹም መታደስንና መለወጥን የሚያስከትል ታስቦበት የተቀናጀ ዝግጅት ነው::

ትክክል ወዳልሆኑ በምድር ላይ የሚከሰቱ የተለሳለሱ መነቃቃቶች የሚያመሩ አሳሳች ጎዳናዎችን አጥብቀን ልንቃወም ይገባል:: ራስን የሚያዘናጋና ሕብለ-ስሜታዊ (emotional) ልምምድ ቤተክርስቲያን ጠንካራ

ወደሆነ አስተማማኝ የእድገት ሥፍራ አያደርሳትም። ይህ አሁን በሥራ ላይ ያለው ተሀድሶ በሐዋሪያዊ ቅባት በኩል አሁን እየተነገረ ያለውን የጊዜውን ቃል በመቀበላችንና ወስኝ በሆነ የልባችን መለወጥ በኩል ሊነሳሳ እየተጠባበቀ ላለና ወደ ምድር የመጣ መሆኑ ለተረጋገጠ አንድ ኃይለኛ የእግዚአብሔር ዘመን የሚደረግ ዝግጅትና አወጃ ነው። በቤተክርስቲያን ላይ ወደፊት የሚታየው የእግዚአብሔር ንቅናቄ እስከዛሬ ከታዩት የእግዚአብሔር ኃይልና ሕልውና መገለጦች ሁሉ በዓይነቱ ተወዳዳሪ የማይገኝለት ይሆናል። የዚህ ንቅናቄ አንድ ልዩ ባህሪ የክርስቶስን አካል ማጠብና ማጥራቱ ከነገድና ከቋንቋ ለክርስቶስ የተመረጡትን ነፍሳት ማሰባሰቡና በሰማያዊ ሥፍራም ይሁን በምድር ላይ በተመሸጉ አጋንንታዊ ምሽጎች ላይ የመጨረሻ ፍርድ የሚሰጥበት መሆኑ ነው። የዚህ ተሀድሶ የልብ ጩኸት "አሁን ተዘጋጅ" የሚል ነው።

> " መንሹም በእጅ ነው አውድማውንም ፈፅሞ ያጠራል ስንዴውንም በጐተራው ይከታል ገለባውን ግን በማይጠፋ እሳት ያቃጥለዋል" ማቴ 3 ፡ 12

### ★ *ተሀድሶ አሁን ላለው የልብ አዝማሚያ አይገዛም*

> " እነዚያም ሲሄዱ ኢየሱስ ለህዝቡ ስለ ዮሐንስ ሊናገር ጀመረ እንዲህም አለ ምን ልታዩ ወደ ምድረ በዳ ወጣችሁ? ነፋስ የሚወዘውዘውን ሸምበቆን? ወይስ ምን ልታዮ ወጣችሁ? ቀጭን ልብስ የለበሰ ሰውን እነሆ ቀጭን ልብስ የለበሱ በነገስታት ቤት አሉ።" ማቴ 11 ፡ 7፣8

ተሀድሶ በብዙሀኑ ሰዎች ዘንድ በተለመዱ የአባባሎች ወይም የመንፈሳዊ መረዳቶች ነፋስ የሚወዛወዝ ሸንበቆ አይደለም። የእያንዳንዱ የእግዚአብሔር የተሀድሶ ንቅናቄ እንብርት ከሐዋርያዊ ትንቢታዊ ጸጋ የተካፈለ አዲስ አቋም ለሚይዘው የአእምሮ እንዲሁም የእግዚአብሔር መንፈስ ወደፊት በምድር ላይ ለሚያዘው ሥፍራ ተገቢ የሆን





የእግዚአብሔር ጸጋና ቁሳቁስ ነው። ስለዚህ ከዚህ ትርጓሜ አኳያ ስንመለከተው ተሀድሶ አሁን ባለችው የቤተክርስቲያን የጋራ አመለካከት ያልተደረሰበት ሲሆን መሠረታዊው ባህሪው ሽግግር የተከተለ የለውጥ ሂደት እንዲከሰት ማድረግና ማስተዋወቅ ነው።

ነቢዩ ሐጌ የእግዚአብሔር ቤት እንዳይሠራ የከለከለውን በእርሱ ዘመን የነበረ የሰዎች አመለካከትና አስተሳሰብ ጠርምሶ እንዲገባ እግዚአብሔር ያስነሳው ሰው ነበረ። የብዙሀኑን አእምሮ ተቆጣጥሮ የነበረው የጊዜው አመለካከት የራሳችንን ቤት እንሥራ፣ የእግዚአብሔርን ቤት ለመሥራት ጊዜው አይደለም የሚል ነበር። በሐጌ በኩል የመጣው የአዋጅ ቃል ግን ነባራዊውን አመለካከት ሰብሮ የእግዚአብሔርን መቅረብ በማብሠር ሕዝቡን ሁሉ ወደ አዲስ የትኩረት አቅጣጫ በመመለስ ትልቅን የሥራ ሂደት ሊያስጀምር ቻለ።

> " የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ይህ ሕዝብ ዘመኑ አልደረሰም የእግዚአብሔር ቤት የሚሠራበት ዘመን አልደረሠም ይላል ብሎ ተናገረ የእግዚአብሔር ቃል በሐጌ እጅ እንዲ ሲል መጣ በውኑ ይህ ቤት ፈርሶ ሳለ እናንተ ራሳችሁ በተሸለሙ ቤቶቻችሁ ለመኖር ጊዜው ነውን? አሁንም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ልባችሁን በመንገዳችሁ ላይ አድርጉ። " ሐጌ 1 ፡ 2፣5

> " የሠላትያልም ልጅ ዘሩባቤል ታላቁም ካህን የኢዩሴዴቅ ልጅ ኢያሱ የቀሩትም ህዝብ ሁሉ የአምላካቸውን የእግዚአብሔር ድምፅ የነቢዩ-ንም የሐጌ ቃል አምላካቸው እግዚአብሔር እንደላከው ሁሉ ሰሙ ሕዝቡም በእግዚአ-ብሔር ፊት ፈሩ የእግዚአብሔር መልክተኛ ሐጌ በእግዚአብሔር መልዕክት ሕዝቡን እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ ይላል እግዚአብሔር ብሎ ተናገረ። እግዚአብሔር የይሁዳን አለቃ የሠላቶያልን ልጅ የዘሩባቤልን መንፈስ

## ምዕራፍ 4

# የተሀድሶ ቴክኖሎጂ

## የቴክኖሎጂ ትርጉም

"ቴክኖሎጂ" የምንለው ቃል አንድ ገሀድ የሆነ መንፈሳዊ ክስተት እንዲመጣና በተግባር እንዲታይ የሚያደርጉ የውስጣዊ መንፈሳዊ መርሆችና ሕጎች ቅንጅት ነው። ይህንኑ መርህ በተፈጥሮአዊውም ተተግብሮ እናያለን። የቴሌቪዥኑን ሪሞት ኮንትሮል ወደ ቴሌቪዥኑ አነጣጥረህ ቁልፉን ስትጫን ያ ቁልፍ ሊያስከትል የታቀደለት ውጤት ያለምንም መዛባት በእርግጠኝነት ያከናውናል ከዚያ ውጪ የሆነ በፍጹም ያልተጠበቀ ነገር ሊሆንም ሊከሰትም በጭራሽ አይችልም። ከቴሌቪዥኑ ውስጣዊ ቴክኖሎጂ የተነሳ ያንን ቁልፍ መጫን የሚያስከትለው ነገር አስቀድሞ የታወቀና አስተማማኝ ነው። የቴሌቪዥኑ ውስጣዊ የኤሌክትሪክ ሽቦ አወቃቀር ለየት ያለና ለዚያ አሠራር የተመቻቸ በመሆኑ ውጤቱ የተጠበቀና አስተማማኝ ነው።

ተሀድሶ የዘመኑ ቤተክርስቲያን አውቃ ልትተገብ-ራቸው የሚገቡ አንዳንድ ልዩ ልዩ ፀባያት አሉት። ተሀድሶ ሰዎች የሚባረኩበት የእግዚአብሔር መንፈስ በሚያደርገው ድንገተኛ ንቅናቄ የሚከሰት ያልተጠበቀ ክስተት አይደለም። ተሀድሶ ከሰማይ የወረደ መገለጥ (እውነት) እንደሆነ የተረዱና በፈቃደኝነትና በእምነት በተሞሉ አማኞች ቀስ በቀስ በምድር ላይ የሚደረግ ግንባታ ነው። ስለአንድ የተሀድሶ ንቅናቄ ብስለትና እግዚአብሔር የወደደው ዓላማ መሳካት ሰዎች የእግዚአብሔርን ንቅናቄዎች ያለከልካይ ወደፊት የሚያስፈነጥሩ ውስጣዊ አሠራሮችን፣ ለዚያ ጉዳይ የሚበጁ ተገቢ የአስተሳሰብ ይዞታቸውንና አስፈላጊ እንቅስቃሴዎችን በቂጡ መረዳት ያስፈልጋል። የመንፈስ ቅዱስን የተረጋገጠና አስቀድሞ ሊተነበይ የሚችል በምድር

ላይ በአጥጋቢ ሁኔታ መንቀሳቀስ የሚችል ነገር ለማስገኘት ተገቢውን የተሀድሶ ቴክኖሎጂ ማወቅ ያስፈልጋል።

አሁን የምንገኘው ለየት ባለ የቤተክርስተያን ዘመን ውስጥ ነው። የእግዚአብሔርን ንቅናቄዎች ካሁን ወዲያ እንደቀደሙት ዘመናት ሁሉ በስው ሠራሽ ኃይማኖታዊ ወጎች፣ ደንቦች ሥርአቶችና ድንጋጌዎች ተተብትበው ፍሬ አልባ በመሆን ተቀብረው አይቀሩም። ዛሬ ቤተክርስቲያንን እየተቆጣጠረ ያለው ሐዋርያዊ (የተላከ) የአእምሮ ይዘት የእግዚአብሔርን ሥራ ለመፈጸም ተገቢውን የአስተሳሰብ ብቃት የታጠቀ አንድ ሕዝብ እንዲወለድ ይጠይቃል።

> " ኢየሱስም እንዲህ አላቸው የእኔስ መብል
> የላከኝን ፈቃድ አደርግ ዘንድ ሥራውንም
> እፈፅም ዘንድ ነው" (ዮሐ 4 : 34)

ኢየሱስ ውጥን ሥራውን ሁሉ ይፈጽም ዘንድ የምድር ዘመናት ወደሙላትና ወደፍጻሜ መምጣት አለባቸው። ከእግዚአብሔር ጋር አብሮ ሠራተኞች ስለሆንን (1ኛ ቆሮንቶስ 3:9) በእያንዳንዱ የእግዚአብሔር ንቅናቄ ውስጥ ያለውን የታመቀ በረከት በፍጥነት በምድር ላይ ለማስለቀቅ የራሳችንን ኃላፊነት መወጣት አለብን።

> ". . . በዘመን ፍጻሜ ይደረግ ዘንድ ያለው
> እሳቡም በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ
> በክርስቶስ ለመጠቅለል ነው" (ኤፌ 1 : 10)

## ተሀድሶና ትንቢታዊ እይታ

"ተሀድሶ" የተሰኘው ቃል ነገሮችን በቅጡ ማደራጀትን ትክክለኛ መልኩ የተዛባውን ወደነበረበት በመመለስና ስንኩሉን አሠራር በማቃናት ወደተሻለ አሠራር ማሻገር እንደሚያመለክት ቀደም ሲል ከተነጋገርንባቸው ሐሳቦች መገንዘብ ይቻላል።





በሐዋርያት ሥራ 24፣2 ላይ ትክክለኛ ተሀድሶ ምን መምሰል እንደሚገባው የሚያመለክቱ ሁኔታዎችን ማየት ይቻላል።

> " ጳውሎስ ተጠርቶ በቀረበ ጊዜ ጠርጡሉስ
> እንዲህ ሲል ክሱን አቀረበ፤ ክቡር ፊልክስ
> ሆይ በአንተ ዘመን ሰላም ለብዙ ጊዜ
> ለፍኖልናል፤ አርቆ አስተዋይነትህም ለዚህ
> ሕዝብ መሻሻል (ተሐድሶን reforms NIV)
> አስገኝቶለታል" (ሐዋ 24 : 2 ኢ.መ.ት)

በዚህ ሥፍራ ጳውሎስ ታስሮ የይሁዳ ገገር ወደ ነበረው ወደ ፊልክስ በሚቀርብበት ጊዜ ጠርጠሉስ የተባለ የአይሁድ ተሟጋች በጳውሎስ ላይ ማስረጃ ለማቅረብ ንግግሩን ሲጀምር እናያለን። ይህ ንግግር በዓለማዊ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ቢሆንም የተሀድሶን ሁኔታ በሚመለከት ግንዛቤአችንን የሚያሰፋ ቁም ነገር እናገኝበታለን። ጠርጠሉስ ከአርቆ አስተዋይነት የተነሳ ስለተገኘ አንድ ተሀድሶ ይናገራል። "አርቆ አስተዋይነት" (foresight) የተሰኘው ቃል ጊዜው ሲደርስ የሚገጥሙ ሁኔታዎችን ለመቋቋም ካሁኑ በመዘጋጀት መጪው ዘመን አሻግሮ የማየትን ችሎታ ያመለክታል። ያሁኑ ድርጊታችን ከሚመጡ ሁኔታዎች ጋር የተሣሠረ ስለሆነ አሁን ያለንን ኃይልና ችሎታ እንደሚገባ እንጠቀምበታለን ማለት ነው። ይሄም የሚያስረዳው የተሀድሶ ሥራ ሊንቀሳቀስ የሚችለው ወደፊት ሊመጡ ካሉ ነገሮች አንጻር ዛሬን መኖር በሚችል አንድ ትንቢታዊ ሕዝብ መሆኑን ነው።

የዛሬይቱ የተሀድሶ ቤተክርስቲያን የአእምሮ ይዘትና አቋም በከፊል ይህንን ይመስላል። ወደ ሐዋርያዊው መንፈስ የፍጻሜ ሥራ አመለካከትና አስተሳሰብ ተሻግረናል (ዮሐንስ 4:34)። አሁን በመንፈሳችን የነገሮችን ሁሉ ፍጻሜና መጨረሻ እያየን ነው። ስለዚህም ነገን በአጥጋቢ ሁኔታ መውረር የሚያስችለንን እየተገለጠ ባሉት የእግዚ-አብሔር ዓላማዎች የተጥለቀለቀ ኃይለኛ የአሁን ጊዜን እየደራጀን እንገኛለን።

አስረጅቶ ከአገልግሎት ውጪ የሚያደርገው ራሱ እግዚአብሔር ነው፡፡ አሮጌው (ብሉይ) ኪዳን ከእግዚአብሔር ነበር፣ አዲስ ኪዳንም እንደዚሁ፡፡ ለውጡ የተደረገው ከእግዚአብሔር ከነበረው የእግዚአብሔር ወደሆነው ነው፡፡ ጠቅላላ የተሀድሶ ቴክኖሎጂ ወሳኝ ማስተያያ የእግዚአብሔር እንቅስቃሴና አደራረጎች ናቸው፡፡ ማንኛውንም ሥጋዊ ነቀፋና ትችት ወይም ምኞትና ፍላጎት ጣልቃ ሊገባበት አይፈቀድለትም፡፡ ነቀፋ ማግኘታችን ከመንፈስ ቅዱስ ብቻ እንጂ ከሥጋ አይደለም፡፡

ስለዚህ መሠረቱ እየተጣለ ያለው አዲስ ነገር አስቀድሞ ከነበረው ላይ የሚነሳ ወይም በዚያ መሠረት ላይ የተመሠረተ አይደለም፡፡ ይሄ አባባል አሁን እኛ ከተያያዝነው ሁኔታ ጋር እንዴት አብሮ እንደሚሄድ መረዳት ወሳኝ ነገር ነው፡፡ ካለፉት ትውልዶች ለእኛ የተላለፉልን መጽሐፍ ቅዱሳዊ የመረዳት ቅርሶች ልናፈርስ ወይም እምነታችን ባለፉ ዘመናት የደረሰበትን የመጨረሻ ከፍታ ልናጣጥል አይገባንም፡፡ እግዚአብሔር ሁልጊዜ ቤተክርስቲያንን ወደነበረችበት ትክክለኛ ሥፍራ በመመለስ ሂደት ላይ ይገኛል ይሁን እንጂ ተሀድሶ ካለፉት የቤተክርስቲያን ልዩ ልዩ አሠራሮች አስተሳሰብ የማይነሳ ሙሉ በሙሉ አዲስ የሆነ የአስተሳሰብ ደረጃን መፍጠር የሚያስችል ነው፡፡

> **" ደግሞም ምሳሌ እንዲህ ሲል ነገራቸው፡- የአዲስ ልብስ እራፊ ባረጀ ልብስ ላይ የሚያኖር የለም ቢደረግ ግን አዲሱን ይቀደዋል ደግሞም አዲስ እራፊ ለአሮጌው አይስማማውም፡፡ ባረጀ አቁማዳም አዲስ የወይን ጠጅ የሚያኖር የለም ቢደረግ ግን አዲሱ የወይን ጠጅ አቁማዳውን ያፈነዳል እርሱም ይፈሳል አቁማዳውም ይጠፋል፡፡ አዲሱን የወይን ጠጅ ግን በአዲስ አቁማዳ ማኖር ይገባል ሁለቱም ይጠባበቃሉ፡፡ አሮጌ የወይን ጠጅ ሲጠጣ አዲሱን የሚሻ ማንም የለም አሮጌው ይጣፍጣል ይላልና፡፡"**
>
> ሉቃ **5: 36 -39**





> **" እነሆ አዲስን ነገር አደርጋለሁ እርሱም አሁን ይበቅላል እናንተም አታውቁትምን?. . . የመረጥሁትን ሕዝቤን አጠጣ ዘንድ . . ."**
>
> **ኢሳ 43 : 18 - 22**

አሁን በምድር ላይ እየተመሠረቱ ያሉት መንፈሳዊ የአመለካከት እርከኖች (perspectives) አዲስ ሥር ነቀልና የተለዩ ናቸው፡፡ የዳዊት ቤተመቅደስ በሙሴ ሥርአት ውስጥ ለነበሩት ሰዎች እንግዳ ነገር ነበር፡፡ እንዲያውም የሳኦል ልጅ የነበረች የዳዊት ሚስት ሚልኮል የባልዋን "ከንጉሥ - የማይጠበቀ" ተግባር ልትታገሰው አልቻለችም (2 ሳሙኤል 6:16)፡፡ የቤተመቅደሱ ሥርአት በተቀየረ ጊዜ ንግሥና የሚለካበት ሚዛኑም አብሮ የተቀየረ መሆኑን በጭራሽ አልተገነዘበችውም ነበር፡፡

## ★ *የተሀድሶ መርህ ቁጥር ሁለት*

## ሕጉ በአእምሮና በልብ ላይ ተጽፎአል (ቁጥር 10)

የተሀድሶ አቅጣጫ ሁልጊዜም ወደ ውስጥ ጠንካራ ወደ ሆነ የእግዚአብሔር ይዞታ ወደሰዎች ልብ ነው፡፡ የተሀድሶ ቀናት ታላላቅ የእግዚአብሔር ኃይል ምልክቶችን ቢያንጸባርቁም ምልክቶች ያለውስጣዊ መልሶ መታነጽ ፋይዳቢስ ናቸው፡፡ ተሀድሶ ከምንጊዜውም ይልቅ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወደ ሰዎች መቅረብን ያመለክታል፡፡ መጥምቁ ዮሐንስ ቀላልና ቀጥተኛ መልእክት ይዞ መጣ " የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለችና . . . " ከሰዎች የሚጠበቀውንም ምላሽ ለማመልከት ". . . ንስሐ ግቡ" አለ፡፡ ይሄም እግዚአብሔር ከልባችን ጋር ጉዳይ ያለው መሆኑን ያሳያል፡፡ እውነተኛው የመንግሥቱ ተጽእኖ ውጫዊ ሳይሆን ውስጣዊ ነው፡፡

> **" ፈሪሳውያንም የእግዚአብሔር መንግሥት መቼ ትመጣለች ብለው ቢጠይቁት መልሶ የእግዚአብሔር መንግሥት በመጠባበቅ አትመጣም ደግሞም እንኋት በዚህ ወይም እንኋት በዚያ**

**አይሉአትም፡፡ እነሆ የእግዚአብሔር መንግስት በመካከላችሁ ናትና አላቸው ”**

**ሉቃ 17 ፡ 20 - 21**

ይህ አይነቱ የተሀድሶ ውስጣዊ ትኩረት በንጉሥ ሕዝቅያስ ተሀድሶ ጊዜ ተንጸባርቆ እናያለን (2ዜና 29፣29)፡፡ በይሁዳ የነበረውን የሞራል (የሥነምግባር) ብልሹነት ለመዋጋት ቆርጦ ተነሳ (2ዜና 28፡19) የቤተመቅደሱን ውስጣዊ ሥፍራ ዘመናትን ካስቆጠረ የቆሻሻ ክምር ማጽዳትን እንደ ቀዳሚ ተግባሩ አድርጎ ሥራውን ጀመረ፡፡ የማጽዳት አቅጣጫው ከውስጥ ወደ ወጪ ነበር፡፡

> **“ ካህናቱም ያነጹት ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ቤት ወደ ውስጥ ገቡ በእግዚአብሔር መቅደስ ያገኙትን ርኩስ ነገር ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ቤት አደባባይ አወጡት ሌዋውያንም ወስደው ወደ ሜዳ ወደ ቄድሮን ወንዝ ጣሉት፡፡ በመጀመሪያውም ወር በመጀመሪያውም ቀን ይቀድሱ ጀመር በዚያውም ወር በስምንተኛው ቀን ወደ እግዚአብሔር ቤት ወለል ደረሱ”**
>
> **2ኛ ዜና 29 ፡ 16-17**

የሕዝቅያስ ተሀድሶ ከሁለት በጣም አስፈላጊ አንጻሮች መታየት ይችላል፡፡

> **“ ንጉሱም አካዝ ነግሶ ሳለ በመተላለፍ ያረከሰውን ዕቃ ሁሉ አዘጋጅተናል ቀድሰናልም እነሆም በእግዚአብሔር መሰዊያ ፊት ሆነዋል አሉት” 2ኛ ዜና 29 ፡ 19**

“መቀደስ” ማለት ለእግዚአብሔር አገልግሎት ለይቶ ማለቀመጥ ሲሆን ይሄም በልብ ውስጥ የሚካሄደውን ውስጣዊ ሥራ ያመለክታል፡፡ ከሁሉ የበለጠ የቅድስና ደረጃ ከውስጥ ሊኖር ይገባል፡፡ “ማዘጋጀት” ማለት ማረጋጋትን፣ ቀጥ ብሎ ተደራጅቶ እንዲቆም ማድረግን፣ ማስተካከልን፣ ማጽናትን ያሳያል፡፡ ይሄም የሚናገረው በአእምሮ ውስጥ





ያለውን የስንፍናና የድካም ስሜት አጥፍቶ ፍጹም መታዘዝ እስኪገኝ ድረስ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ቅኝት እንዲታነጽና እንዲመሠረት ስለማስቻል ነው፡፡

በአሁኑ ዘመን የእግዚአብሔር መንግሥት በልብና በአእምሮ ላይ ሊጸና ይገባዋል፡፡ አሁን የተገለጠውን የእግ-ዚአብሔር ነገሮች ሚስጥር አምኖ ለመቀበልና ለመታዘዝ ውጫዊ ግዴታ ወይም ተጽእኖ አያስፈልግም፡፡ ከውስጥ ከሚመነጭ እግዚአብሔርን የመፈለግ ጠንካራ ጥማት ብቻ መነሳት አለበት፡፡ በቀላል አባባል ለመናገር እግዚአብሔር በዚህ ተሀድሶ ከገዛ ሕዝቡ ጋር በልባቸው በኩል እንደገና ሊገናኝ ይፈልጋል፡፡

## *★ የተሀድሶ መርህ ቁጥር ሦስት መለኮታዊ መዋደድን በእግዚአብሔርና በሰው መካከል እንደገና መልሶ ማጽናት (ቁጥር 10)*

“የሕጉ” ከሰው ልብ ጋር መልሶ መጣበቅ በሰውና በእግዚአብሔር መታዘዝ ምክንያት ፈርሶ የነበረ ከሁሉ በፊት ቀዳሚ የነበረ ዕውነታ ነው፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ዐይን ለዐይን መተያየት አቅቶት ራሱን ለመደበቅ እንደሞከረ እናውቃለን፡፡ እምነት በፍርሀት ተተካ፣ በራሱ ላይ ሲያተኩር በእግዚአብሔር ላይ የነበረ ትኩረቱ ፈረሰ፡፡ የራሱን ራቁትነት በመሸፈን ላይ ተውጦ ከእግዚአብሔር ሸሽቶ በቁጥቋጦ ውስጥ ተደበቀ፡፡ በትውልዶች መካከል ያላቋረጠ የእግዚአብሔርን ጥያቄ ዛሬም “እራቁትህን እንደሆንክ ማነገረህ?” የሚለው ነው (ዘፍጥረት 3፡11)፡፡

አዳም ወደራቁትነት የመጣው እግዚአብሔርን ባለመታዘዙ አልነበረም ሁልጊዜም ራቁቱን ነበር፣ ትኩረቱን ከእግዚአብሔር ላይ አንስቶ በራሱ ላይ ባደረገ ጊዜ ብቻ ነበር ይሄንን ያወቀው፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ያለ የመዋደድ ግንኙነት (intimacy) በምድር ላይ እያለን እንኳ ምድራዊ የግንኙነት ሞገዶችን ሁሉ አፍርሶ እግዚአብሔር ብቻ ወደሚታይበት በጥራቱ እጅግ ላቅ ወዳለ የግንኙነት አካባቢ (environment) ያስገባናል፡፡

ተሀድሶ እንደገና ወደ እግዚአብሔር ያቀርበናል:: በዚህ ሂደት ውስጥ ሥጋዊ አመለካከቶቻችን ይፈርሱና የእግዚአብሔር ፈቃድ ወዳለበት አካባቢ እንገባለን:: በሥጋዊና ምድራዊ ምኞት ላይ የተመሠረተች ቤተክር-ስቲያን ተወግዳ የእግዚአብሔርን ዓላማ በማራመድ ላይ የተገነባች ቤተክርስቲያን ትነሳለች፤ ከባዶ ኃይማ ኖተኝነት ወደ እውነተኛ የመዋደድ ግንኙነት እንሻገራለን:: እርሱም አምላካችን እኛም ሕዝቡ እንሆናለን::

ተሀድሶአዊ የቅርብ ግንኙነት (መዋደድ) በጣም ኃይለኛ ነገር ነው:: እኛን ከእርሱ ከሚያርቁ እንቅፋቶችና ውስንነቶች ወጥተን ተስፋ መቁረጥና መካንነት በሌለበት ፍሬያማነትና ወላድነት በበዛበት የቁርዬው (መንፈስ ቅዱስ) ዝማሬ ባለበት የተለየ ዓለም መኖር እንጀምራለን::

> **" እነሆ የውዴ ቃል በተራሮች ላይ ሲዘልል በኮረብቶችም ላይ ሲወረወር ይመጣል:: ውዴ ሚዳቋን ወይም የዋላን እምቦሳ ይመስላል፤ እነሆ በመስኮቶች ሲጐበኝ በዓይነ ርግብም ሲመለከት እርሱም ከቅጥራችን በኋላ ቆሞአል:: ውዴ እንዲህ ብሎ ተናገረኝ ወዳጄ ሆይ ተነሽ ውበቴ ሆይ ነይ እነሆ ክረምት አለፈ ዝናቡም አልፎ ሄደ፣ አበቦች በምድር ላይ ተገለጡ የዜማም ጊዜ ደረሰ የቁርዬውም ቃል በምድራችን ተሰማ:: በለሱ ጐመራ ወይኖችም አበቡ መዓዛቸውንም ሰጡ ወዳጄ ሆይ ተነሺ፤ ውበቴ ሆይ ነይ"**
>
> **መኃ 2 : 8 - 13**

## ★ *የተሀድሶ መርህ ቁጥር አራት*

## የመገለጥ መስተካከሎች ጉዳይ (ቁጥር 11)

የተሀድሶ ሂደት አንዱ አላማ ከሰማይ የተገለጠ ምስጢራትን በተመለከተ በሕዝቦች መካከል ያለውን የመረዳት መበላለጦች ማስተካከልና እኩል የሆነን እድል ለሁሉም ማዳረስ ነው:: የመንግሥቱን ምስጢራት ዘልቆ





በመረዳት በኩል በምድር ላይ የትኛይቱም ሀገር የትኛውም ባህል ሆነ ሕዝብ ከሌሎች ይልቅ የታደለና የተሻለ ሊሆን አይችልም:: በኢየሱስ የተወሰነው ወደ ምስጢራት ዘልቆ የመግባት ዕድል በቤተክርስቲያን ውስጥ ላሉት ሁሉ የተከፈተ እንጂ በአንድ ቡድንና በሌላ መካከል መበላለጥ እስኪኖር ድረስ አንዱን ጠቅሞ ሌላውን የሚያሳንስ አይደለም:: መግባት የተከለከለው በውጪ ላሉት እንጂ ለቤተክርስቲያን አይደለም::

> **" እርሱም መልሶ እንዲህ አላቸው ለእናንተ የመንግሥተ ለማያትን ምሥጢር ማወቅ ተሰጥቶአችኋል ለእነርሱ ግን አልተሰ ጣቸውም"**
>
> **ማቴ 13 : 11**

በፕሮቴስታንት የተሀድሶ ንቅናቄ ጊዜ ሰዎች ሁሉ ከተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል ጋር እንዲገናኙ ማርቲን ሉተር መጽሐፍ ቅዱስ በብዛት እንዲታተም ጠየቀ:: ይህ ጥያቄ ሕዝቡን በውሱን እውቀትና ይባስ ብሎም ድፍን ባለ ድንቁርና ውስጥ በማኖር መንፈሳዊ ገገርዎችና አለቆች ሆነው በኖሩ የኃይማኖት ባለሥልጣናት ዘንድ ከፍተኛ ጩኸትና ተቃውሞን አስነሳ:: በዘመናችንም "የኢምፔሪያ ሊስት ክርስትና" ተብሎ ሊታወቅ የሚችል ነገርና ራሳቸውን ሊቀ-ሊቃውንት አድርገው ከሾሙት የቤተክህነት አለቆች አልተማሩም በሚባሉት ላይ የሚሰነዘር የአውቅ-ልሀለሁ ተጽእኖ በቤተክርስቲያን ውስጥ ሰፍኖ መኖሩን እናውቃለን:: በሉተር ዘመን እንደሆነ ዛሬም በእኛ ዘመን ተሀድሶ የሚመጣው በሰዎች መካከል የሚኖረውን የመረዳት መበላለጥ ለማፍረስ ነው:: "ከታናሹ ጀምሮ እስከ ታላቁ ድረስ ሁሉም ያውቁኛል::"

ያለምንም ጥርጥር ዛሬ ከምንጊዜውም ይልቅ በተለምዶ "ሦስተኛው ዓለም" ተብሎ በሚታወቀው የዓለም ክፍል ትንቢታዊ የሆነ የመንፈስ ቅዱስ አትኩሮቶች (focus) አሉ:: በእነዚህ የሦስተኛ ዓለም አገሮች ከዘረኝነት ስሜት ተነሳስተው የመንፈስ ቅዱስን አትኩሮት በተሳሳተ መንገድ

በመተርጎም ኢየሱስ ካሁን ወዲያ ጥቁሮችን እንጂ ማንንም አይጠቀምም እስከማለት የደረሱ አንዳንዶች አሉ፡፡ ይሄ እንግዲህ የመንግሥተ ወንጌል ሊባል በጭራሽ አይችልም፡፡ በዓለም ላይ ልዩ ልዩ ዓይነት ሕዝቦች መኖራቸው ሲታወቅ ይህ በይነቱ አባባል ጠባብና አድሎኛ ከመሆን አይዘልም፡፡ ያም ሆኖ ኃይለኛ የሆነ የመጨረሻው ዘመን ተሀድሶ ግፊት በሦስተኛው ዓለም እየፈነዳ መሆኑንና ይሄም ግፊት በሌሎች አገሮች ካለው የእግዚአብሔር ንቅናቄ ፍንዳታ ጋር የሚወራረስ መሆኑን ማስተዋል ይቻላል፡፡

> " በዚያም ቀን እንዲህ ይሆናል፡- ለአሕዛብ ምልክት ሊሆን የቆመውን የእሰይ ስር አሕዛብ ይፈልጉታል ማረፊያውም የተከበረ ይሆናል፡፡ በዚያም ቀን እንዲህ ይሆናል፡- የቀረው የሕዝቡ ቅሬታ ከአሦርና ከግብጽ ከጳትሮስና ከኢትዮጵያ ከኤላምና ከሰናአር ከሐማትም ከባህርም ደሴቶች ይመልስ ዘንድ ጌታ እንደገና እጁን ይገልጣል፡፡ ለአሕዛብም ምልክት ያቆማል ከእስራኤልም የተጣሉትን ይሰበስባል ከይሁዳም የተበተኑትን ከአራቱ የምድር ማዕዘኖች ያከማቻል" ኢሳ 11 ፡ 10 - 12

" ለአሕዛብም ምልክትን (banner) ያቆማል" (ቁጥር 12)፡፡ ከዚህ ከፍ ብሎ በቁጥር 11 ላይ ለአብነት የተጠቀሱት አሕዛብ መንፈስ ቅዱስ በሦስተኛው አለም የምድር አካባቢ ላይ ስለሚኖረው ትኩረት ጠንካራ ምልክቶች ናቸው፡፡ በያንዳንዱ የዓለም ሕዝብና ሕብረተሰብ መካከል ትክክለኛና የተሟላ የክርስቶስ መልክ መገለጥ እስኪመጣ ድረስ በየትኛውም የዓለም ክልል ያለች ቤተክርስቲያን በሰላ ለፍሬ እስክትበቃ በርትተን መሥራት ያለብን መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

### *★ የተሀድሶ መርህ ቁጥር አምስት*

## የትንቢታዊ እወጃ ኃይል (ቁጥር 13)<br>አዲስ በማለቱ ፊተኛውን አስረጅቷል፡፡





አዲሱን ማስተዋወቅ ነው አሮጌውን የሚያስረጀው፡፡ "ማለት" (መናገር) ነው አዲሱን የሚገነባው፡፡ ተሀድሶን በምድር ላይ ለማምጣት ወሳኙ ነገር ሊመጡ ስላሉት ነገሮች አስቀድሞ (በትንቢት) መናገር ነው፡፡ በትንቢት ቃል የተሞሉ የእግዚአብሔር ሕዝቦች አሁን በዚህ ዘመን እግዚአብሔር ሊያደርግ ያላቸውን ንቅናቄዎችና የመንፈስ ቅዱስ ትኩረት አሁን ያለበትን ሥፍራ ተግተው በምድር ላይ ሲናገሩ ትልቅ የሆነ መንፈሳዊ የለውጥ ንቅናቄ ይፈጠራል፡፡

ለባ የባርነትና የመገዛት ዘመናትን አሳልፎ በዘለዓለማዊ ዓላማው ላይ ወደ አዲስ የግንባታ ዘመን ሊያስገባቸው እግዚአብሔር ሕዝቡን ከባቢሎን ማስወጣት ባሰበ ጊዜ ወደ አዲሱ ዘመን ሽግግር የሚያደርግበትን ቴክኖሎጂ የሚጠቁም መመሪያ በነብዩ ኤርሚያስ በኩል ሲሰጣቸው እናያለን፡፡

> " በአሕዛብ መካከል ተናገሩ አውሩም አላማ-ውንም አንሡ አውሩ አትደብቁ ባቢሎን ተወሰደች ቤል አፈረ ሜሮዳክ ደነገጠ ምስሎችዋ አፈሩ ጣኦታትዋ ደነገጡ በሉ ሕዝብ ከሰሜን ወጥቶባታል ምድርዋንም ባድማ ያደርጋል የሚቀመጥባትም አይገኝም ከሰው ጀምሮ እስከ እንስሳ ድረስ ሸሽተው ሄደዋል፡፡ በዚያም ወራት በዚያም ጊዜ ይላል እግዚአብሔር የእስራኤል ልጆችንና የይሁዳ ልጆች በአንድነት ሆነው ይመጣሉ፤ አምላካቸውንም እግዚአብሔርን ይፈልጋሉ"
>
> ኤር 50 ፡ 2 - 4

የእግዚአብሔር ሕዝብ በትንቢት መንፈስ እየተናገሩ ቤልና ሜሮዳክ አፍረው መዋረዳቸውን ማጽናት ነበረባቸው፡፡ እግዚአብሔር ሊያደርግ ያለውን ሳይደብቁ መናገር እንዳለባቸው ያሳስባል፡፡ ያንን ትንቢት እንዲናገሩ በታዘዙበት ሰዓት የባቢሎን ሥርአት የሚወድቅ ስለመሆኑ ምንም ዐይነት ተስፋ ሰጪ ምልክት አለመኖሩን ማስተዋል ጠቃሚ ነው፡፡ ከአንደበታቸው የሚወጣው የትንቢት ቃል

ነበር መጨረሻ ላይ የባቢሎን የፖለቲካ ችግር ሆኖ የሚገለጠውን መንፈሳዊ አንቀሳቃሽ ኃይል (dynamic) የሚፈጥረው::

ስለተሀድሶ ከዚህ የምንማረው ኃይለኛ መርህ በአሮጌው ውስጥ እያለን የምናደርገው አዲሱን የሚጋብዝ ትንቢታዊ አወጃ አሮጌውን ፈረካክሶ የእግዚአብሔርን ዓላማ በምድር ላይ እንዲለቀቅ ያደርጋል:: ዛሬ በምድር ዙሪያ በተለያዩ አገሮችና ማኅበረሰቦች ዘንድ ትንቢታዊ ሕዝቦች ለተሀድሶ ያላቸውን ፍላጎት በሐዋርያዊ ዶክትሪን ሞልተው እንዲመሠረት የሚመኙትን የተሀድሶ ሥርአት በሐዋርያዊ የመረብ አሠራር (apostolic network) በኩል እየገለጹ ናቸው:: ንግግራቸውም ድርጊታቸውም ሁሉ ትንቢታዊ ነው:: በ21ኛይቱ ክፍለ ዘመን ቤተክርስቲያን አዲስ ሥርአት ኃይለኛ በሆነ ተሀድሶ በኩል በምድር ዙሪያ እየተገለጸ ነው:: ለዚህም ምክንያቱ መናገራችን (ማወጃችን) ነው::

## ★ *ተሀድሶ መርህ ቁጥር ስድስት*

## ለእርጅና ምክንያት የሚሆኑ ነገሮች (ቁጥር 13)

ከብሉይ ኪዳን ወደ አዲስ ኪዳን በተደረገው በታላቁ ሽግግር አሮጌው (ብሉይ) ኪዳን እንዲያረጅ ተደረገ:: መጽሐፍ ቅዱስ ማርጀትን አስመልክቶ በዚህ ሥፍራ መጀመሪያ የተጠቀመበት ቋንቋ ከጊዜና ከአገልግሎት ብዛት ማለቅን የሚያመለክት ነው:: ከሰማይ የተለቀቀን አንድ አሠራር አሁን ላሉት የምድር ወራት ሊያገለግል እንደማይችል አድርጎ ማስወገድን ያሳያል:: ዘላቂ የመሰለው ውስብስብ ኃይማኖታዊ የአምልኮና መስዋዕት የማቅረብ ሥርአቶች "ግልባጭና ጥላ" መሆናቸው ታወቀ:: ይኼ ሁሉ ለሙሴ በተሰጠ የእግዚአብሔር መለኮታዊ መመሪያ መሠረት በምድር ተገልጦ ነበር:: ተሀድሶ በመጣ ጊዜ ግን ለዘመናቸው መለኮታዊ መመሪያ የነበሩ ነገሮች ለዚህኛው ዘመን የማይጠቅሙ ሆነው ተገኙ::

በአሮጌ የአመለካከት አወቃቀሮች ውስጥ ለለተቆለፉና ድልና ጥርመሳ የተገኘባቸው የአለፉ ዘመናት





ተአምራት ትዝታ በአእምሮአቸው ለላለ ሰዎች ብዙውን ጊዜ ያንን ትተው መንፈስ ቅዱስ ወደሚለቅቃቸው አዳዲስ ነገሮች መግባት ይፈራሉ:: በዘመኑ ሕይወት ለጨ ሆኖ ያገኙትን ያንን ነገር ለቅቀው ወደ ሌላ ነገር ቢሸገሩ እግዚአብሔር በሕይወታቸው ውስጥ አንድ ጊዜ ሠርቶት ለነበረው ነገር ታማኞችና ባለውለታ ሳይሆኑ እንደመቅረት አድርገው ይቆጥሩታል፤ ለአሮጌው ያላቸው ፍቅር የማይነቀነቅ ይሆንባቸዋል::

> " አዲሱን የወይን ጠጁ ግን በአዲስ አቁማዳ ማኖር ይገባል ሁለቱም ይጠባበቃሉ አሮጌ የወይን ጠጅ ሲጠጣ አዲሱን የሚሻ ማንም የለም አሮጌው ይጣፍጣል ይላልና"
>
> ሉቃ 5 : 38፣39

ለተሀድሶ ሽግግር ቁልፍ የሆነው ሃሳብ አዳዲስና ከበፊቱ ይልቅ የተሻለ ውጤታማ ነገሮችን በመካከላችን እየለቀቀ እግዚአብሔር ራሱ አሮጌ መንፈሳዊ ይዞታዎችን አሮጌና ከጥቅም ውጪ እንደሆኑ ትንቢት የሚናገርባቸው መሆኑ ነው:: ለውጤታማና በዓላማ ለሚንቀሳቀሱ የቃልኪዳን (covenant) ግንኙነቶች ልባችንን ልንከፍት ይገባናል:: በቤተክርስቲያን እየተገለጡ ላሉ አዳዲስ መዋቅራዊ ሥርአቶች፣ አዲስ የቋንቋ አጠቃቀሞች፣ ወደ 21ኛው ክፍለ ዘመን ትውልድ የአመለካከት ሞገድ (frequencey) ውስጥ ለሚያስገባ አዲስ ቅኝት፣ ለአዲስ የባህሪ አመራር ዘይቤዎች፣ በመዘናዊቱ ቤተክርስቲያን ውስጥ አዲስ ለሚሆኑ አስተዳደራዊ ስልቶች እንዘጋጅ፤ ታይቶና ተሰምቶ ወዳልታወቀ የኃይልና ምድርን የመግዛት ከፍታ እየገባን እንጓዛለን::

በትንቢት ቃል አዲሱ ከመታወጁ የተነሳ እግዚአብሔር ከሰማይ አሮጌ ያደረገው ነገር ተጠርጎ ይወገዳል:: ከዚያ በኋላ በዚያ በአረጀውና እንዲወገድ በተፈረደበት አሮጌ መሠረት ላይ ለመገንባት መታገል ሞኝነት ነው:: ለዘመኑ የሚስማማውን የእግዚአብሔር ትኩስ ነገር ያልያዙ መዋቅሮች፣ አመለካከቶችና መንፈሳዊ

ይዞታዎች ሁሉ ቀስ በቀስ እያረጁ ሄደው በመጨረሻም ተፈረካክሰው ይጠፋሉ፡፡

## የተሀድሶ ተጨማሪ መርሆች

አሁን ደግሞ ይበልጥ ወደተወሳሰቡ የተሀድሶ ቴክኖሎጂ ገጽታዎች ተመልሰን ለዘመናችን የሚጠቅሙ ትምህርቶችን ለመቅሰም ራሱን የሙሴን ቤተመቅደስ የአሠራር ስልቶች እናጠናለን፡፡

> " ይህም እንደዚህ ተዘጋጅቶ ሳለ ካህናት አገልግሎታቸውን እየፈፀሙ ዘወትር በፊተኛ ይቱ ድንኳን ይገቡባታል፡፡ በሁለተኛይቱ ግን ሊቀካህናት ብቻውን በአመት አንድ ጊዜ ይገባበታል እርሱም ራሱና ስለ ሕዝቡ ስህተት የሚያቀርበውን ደም ሳይዝ አይገባም ፊተኛ ይቱም ድንኳን በዚህ ገና ቆማ ሳለች ወደ ቅድስት የሚወስደው መንገድ ገና እንዳል ተገለጠ መንፈስ ቅዱስ ያሳያል፡፡ ይህም ለአሁኑ ዘመን ምሳሌ ነው እንደዚህም መባና መስዋዕት ይቀርባሉ እነዚህም እስከ መታደስ ዘመን ድረስ የተደረጉ ስለ ምግብና ስለመጠጥም ስለ ልዩ ልዩ መታጠብም የሚሆኑ የሥጋ ሥርዓቶች ብቻ ናቸውና የሚያመልከውን በሕሊና ፍጹም ሊያደርጉት አይችሉም፡፡ ነገር ግን ክርስቶስ ይመጣ ዘንድ ሳለው መልካም ነገር ሊቀካህናት ሆኖ . . ."
>
> ዕብ 9 : 6 - 11

### ★ የተሀድሶ መርሆች ቁጥር ሰባት

**የአሠራሩ (የሲስተሙ) ድክመት (ቁጥር 9 - 10) ". . . የሚያመልከውን በሕሊና ፍጹም ሊያደርጉት አይችሉም፡፡"**

ችግሩ እንዲህ ነበር፡፡ በሙሴ ድንኳን ሥርአት የቱንም ያህል ተጠንቅቆ መሥራት ቢሞከር፣ እያንዳንዱ





መመሪያ ውልፍት ሳይባል በተቻለ ብቃትና ጥንቃቄ ቢተገበር ሥጋን ብቻ ሊያነጻ ይችል ይሆናል እንጂ ወደ ውስጥ ዘልቆ የሰውን ህሊና ሊዳስስና ሊያነጻ ፈጽሞ አይችልም፡፡ ተፈላጊው ደግሞ ሕሊናን ማንጻት ማስቻል ነበር፡፡ እንግዲህ አንድ ሥርአት የቱንም ያህል ተነፍቶ በሥርአቱ ተገልጋይ የሆኑትን ሰዎች ውጤት ማግኘት ወደሚችሉበት ብቃት ማድረስ ካልቻለና መንፈሳዊ ጥማታቸውን ሊያረካ ከተቸገረ ያለው ብቸኛ አማራጭ የተሀድሶ ንቅናቄ እና ተፈላጊውን ውጤት በቀላሉ ማስገኘት የሚችልን አዲስ ሥርአት ተግባራዊ ማድረግ ብቻ ነው፡፡

እንደ ገናም የአንድ ተሀድሶ ውጤታማነት አቅጣጫ ሁልጊዜ ወደ ውስጥ ነው፡፡ በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል የተደረገው የመንፈስ ቅዱስ ንቅናቄ ሁሌም የሕዝቡን ልብ ለመቆጣጠር ነበር፡፡ የእግዚአብሔር ንቅናቄ የሰውን ውስጣዊ ማንነት ለማግኘት የሚደረግ ንቅናቄ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ክብር በውስጣዊ ቤተመቅደስ ማደሪያን እስካላገኘ ድረስ እረፍት የለውም፡፡ ሥጋ ማንጻት በውጫዊ ነገሮች ተወስኖ መቅረትን ያመለክታል፡፡ የሕሊና ማንጻት ግን ወደልብ ዘልቆ በመግባት አዲስን ኃይል ያስለቅቃል፡፡ የተሀድሶ ዘመን ሕዝቦች የሥጋን ጩኸትና ልቅሶ ቸል በማለት የልብን ጥያቄ ለመመለስ ቅድሚያ የሚሰጡ ሕዝቦች ናቸው፡፡ ውጫዊ ለሆኑ ሥጋዊ ምልክቶች ዋጋ ባለመስጠት ውስጣቸውን በመንፈስ ቅዱስ ለመሥራት ራሳቸውን በትህትና የሚያቀርቡ ሰዎች ናቸው፡፡

መንፈሳዊ ፍላጎት ሊደናቀፍና ከታለመለት ግብ ሳይደርስ ሊቀር ይሄ ሁኔታ ለተሀድሶ ንቅናቄ ዋና የልብ ትርታ ነው፡፡ ልንደርስበት የተፈለገውን መንፈሳዊ ብቃት አሁን በተግባር ሳይ ያለው ሥርአት ሊመልሰው የማይችለው ጥያቄ መሆን አለበት (Demand must be greater than supply) መንፈሳዊ ረሀብ በሥራ ላይ ካለው መንፈሳዊ አቅራቦት መብለጥ ይኖርበታል፡፡ ወደምድር የተለቀቀው እግዚአብሔር ለዘመኑ የወሰነው መንፈሳዊ በረከት ተትረፍርፎ ቤተክርስቲያን አሁን ያለችበት ሥርአት ሊቀበልና ሊያስተናግድ ከሚችለው በላይ መሆን አለበት፡፡ ተሀድሶን እንዲመጣ የሚያንቀሳቅሰው ኃይል (dynamics) ይሄ ነው፡፡

## ★ የተሀድሶ መርሆች ቁጥር ስምንት

### ሥፍራን የመረካከብ ኃይል (ቁጥር 8)

**" ፊተኛይቱም . . . በዚህ ገና ቆማለች ወደ . . . የሚወስደው መንገድ ገና እንዳልተገለጠ መንፈስ ቅዱስ ያሳያል:: "**

በሙሴ ድንኳን ሥርአት ሊቀካህናቱ ደም ይዞ በአመት አንድ ቀን ወደ ውስጠኛይቱ ክፍል (ወደ ቅድስተ ቅዱሳን) ይገባ ነበር:: ይሄም የሚያመለክተው ውስን የሆነ የመግባት ብቃት ነው:: ይህ አሠራር በሙሴ ሕግ ተዋቅሮ ሰነበረው ሥርአት የሚያገለግል ነበር:: ይህ ውስንነት እንኳ በራሱ በጣም አስፈላጊ የሆነን አንድ የተሀድሶ ቴክኖሎጂ ያመለክታል:: እየሰጠ ያለው ተናጋሪው መንፈስ ቅዱስ ራሱ ነው:: በቀጥታ ከሰማይ የሆነ ምልክት:: የመጀመሪያይቱ ድንኳን ተግባር ላይ እስከሆነች ድረስ ወደ እውነተኛይቱ ድንኳን (ከሁሉም ይልቅ ወደምትበልጠዋ ቅድስት) የሚያስገባው መንገድ ሊገለጥ በጭራሽ አይችልም::

"ተገለጠ" (ቁጥር 8) ማለት እውን ሆነ፣ ታየ፣ ታወቀ፣ ሰዎች ሊገነዘቡት ቻሉ እንደማለት ነው:: ተግባራዊ መሆንን ብቻ ሳይሆን ሰማያዊ መገለጥንም የሚያመለክት ቃል ነው:: አሁን በሥራ ላይ ያለው የደካማው አሮጌ ሥርአት መርሆችንና አመለካከቶችን በሰዎች አእምሮ ላይ የያዙት ሥልጣንና ቁጥጥር በሥፍራው እስካለ ድረስ የአዲሱ ሥርአት መርሆችና አመለካከቶች እንዲሁም የአሠራር ዘይቤዎችና ሰማያዊ መገለጦች ወደመታየት ሊመጡ አይችሉም:: መንፈስ ቅዱስ እንደሚያሳየው (ቁጥር 8) አሮጌው በሚገባ ተገፍቶ እንዲፈራርስ ካልተደረገ አዲሱ ሊገለጥ አይችልም::

ይህ ወሳኝ ለውጥ የተሀድሶ ሂደት አካል ሲሆን ሁለቱም ሂደቶች በአንድ ላይ የሚከናወኑ ናቸው:: አንድ ሥርአት እየደከመ እየደከመ ሲሄድ ሌላ ሥርአት እርሱን ለመተካት እየጎለበተ እየፈረጠመ ይገለጣል:: ተሀድሶ በነበሩ





ሥርአቶች ላይ ለውጥን በማምጣት እንቅሳቃሽ ኃይል ያለው ግጭት (መናጋት) ያስከትላል::

**" በሳኦል ቤትና በዳዊት ቤት መካከል ብዙ ዘመን ጦርነት ሆነ የዳዊት ቤት እየበረታ የሳኦል ቤት ግን እየደከመ የሚሄድ ሆነ"**

**2ኛ ሳሙ 3:1**

እያንዳንዱ ተሀድሶ የራሱን አዲስ የአእምሮ ይዞታ እና አዲስ የአሠራር ስልት ይዞ ይመጣል:- የራሱን ዐይነት ዝማሬ፣ ጸሎት፣ የአኗኗር ዘይቤ፣ ሰብአዊ መለያና አዲስ የመንፈስ ቅዱስ አሠራር ችሎታን በምድር ላይ ገልጦ ያሳያል:: አሮጌ አመለካከቶችና እስተሳሰቦች ተወግደው በአዲሱ አስተሳሰቦች በመተካት አዲሱ ሥርዓት በምድር ላይ መገለጥ ይገባዋል::

## ★ የተሀድሶ መርሆች ቁጥር ዘጠኝ

### ነፃነትን የሚያመለክቱ ጉዳዮች (ቁጥር 10)

**" እነዚህም እስከመታደስ (ተሀድሶ) ዘመን ድረስ የተደረጉ (የተጫኑ) . . ."**

በተሀድሶ ዘመን አሮጌው ሥርአት ጭነት (imposition) ሆኖ መታየት ይጀምራል:: በዘመኑ ሕይወት አምጪ የነበረው ነገር አሁን ባርነት ቀርቧል የሚል አዋጅ ነጋሪ ይሆናል:: "imposed" የሚለው ቃል ከላይ ወደታች መጫንን፣ በላዩ ላይ መጋደምን፣ ሸክም መሆንን አመልካች ነው::

ዮሴፍ አባቱንና ወንድሞቹን ወደግብጽ ምድር ያመጣቸው ትልቅን በረከት ሊያወርሳቸውና ሕይወታቸውን ሊታደግ ነበር::

**" እስራኤልም በግብፅ ምድር በጌሤም አገር ተቀመጠ ገዙአትም ረቡ እጅግም በዙ"**

**ዘፍ 47 : 27**

ነው። ካይሮስን በውስጡ ከያዛቸው እርሱን ከሚወስኑት ባህሪያት ነጥሎ ማየት አይቻልም። ጊዜው ራሱ (የካይሮስ ጊዜ) የተወሰኑ ድርጊቶች አውቀው እንዲከሰቱ ያስገድዳል።

ካይሮስ ትኩረት የሚሰጠው በወራቱ አመቺነት ላይ ሳይሆን ጊዜው ተስማሚ ሆነ አልሆነ መሠራት ያለበት የወቅቱ ተግባር በወቅቱ መሠራቱ ላይ ነው። ስለዚህ በዘመነ ተሀድሶ ለሥራ የሚያንቀሳቅስ አስተሳሰብ ሥጋ ለምቾትና ለእረፍት የሚያቀርባቸውን ጥያቄዎች ጸጥ በማሰኘት የእግዚአብሔርን ፈቃድ በምድር ላይ እንዲገለጥ ከሚተጋ አመለካከት ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ሆኖ እናገኘዋለን።

በዚህ ምክንያት ተሀድሶ በጊዜው ከሚገኝ የመዘናጋት ሕይወት ተገንጥሎ ለሥራ በሚተጋ የሀላፊነት ስሜት በተሞላ መንፈሳዊ አካባቢ ይገኛል። የተሀድሶ ሠራተኞች ሌሎች ሊያስተውሉ ያልቻሉትን እየመጣ ያለ የፈተና ሰዓት (crisis) አስቀድመው በማሸተት ሕዝቡ ወደሚቀጥለው የእግዚአብሔር የሥራ ደረጃ እንዲመጣ በትንቢታዊ አዋጅ (prophetic declaration) የሚቀሰቅሱናቸው። ተሀድሶ አደናቃፊዎችንና ኃይማኖተኛ ተቃዋሚዎችን መታገስ የማይችል ጤናማ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ነው። የራስን ጊዜያዊ ምቾት በሚያስጥል፣ መስዋዕትነትን በሚጠይቅ እንቅስቃሴ የተሞላና ፍጻሜን (destiny) ትኩር ብሎ ለማየት ዐይኖችን የሚገልጥ ነው። ተሀድሶ ሲመጣ ተራ ቅዱሳን እንኳ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ጠንቅቀው ወደሚያውቁበት ደረጃና በምድር አቀፉ (global) መለኮታዊ ፕላን ውስጥ የራሳቸው ሥፍራ የቱ እንደሆነ ወደ ሚያስተውሉበት የአእምሮ ሥፍራ ይደርሳሉ።

የእግዚአብሔር ኃይልና የእግዚአብሔር መገለጥ (revelation) ሁለቱም ካይሮስ ውስጥ ተቆልፈው ይገኛሉ። ሙሴ በከፍተኛ የመጠበቅና (expectation) የመጓጓት ስሜት እየተቃጠለ ለነፃነት ከተመደበው ትክክለኛ ጊዜ (ካይሮስ) በፊት በመንቀሳቀስ ግብጻዊውን ገደለ። መሻቱ ትክክል ነበር፣ ጊዜው ግን ትክክል አልነበረም። በእግዚአብሔር ካይሮስ ውስጥ ገና ትክክለኛ ሥፍራውን ስላልያዘ





መንግሥትን የሚያናውጠው ኃይል በውስጡ መፈሰስ አልጀመረለትም ነበር። ተሸንፎ፣ ፈርቶና ሸሽቶ ራሱን ለመሸሸግ አርባ ዓመት በምድረ በዳ ኖረ።

## የተሀድሶ ቁልፎች

### ★ አንደኛ ቁልፍ ወደ አዲስነት መግባት አለብን

" ሙሴም አለ፡- ይህን ሥራ ሁሉ አደርግ ዘንድ እግዚአብሔር እንደ ላከኝ እንጂ ከልቤ እንዳይደለ በዚህ ታውቃላችሁ። እነዚህ ሰዎች ሰው እንደሚሞት ቢሞቱ ወይም እንደ ሰው ሁሉ ቢቀሠፉ እግዚአብሔር አልላከኝም። እግዚአብሔር ግን አዲስ ነገር ቢፈጥር ምድርም አፍዋን ከፍታ እነርሱን ለእነርሱም ያለውን ሁሉ ብትውጣቸው በሕይወታቸውም ወደ ሲኦል ቢወርዱ ያን ጊዜ እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔርን እንደናቁ ታውቃላችሁ"

**ዘሁ 16 : 28-30**

የአዲስነት ነፋስ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላከ አንድ ነገር አካባቢውን የሞላው ለመሆኑ ጥሩ ምልክት ነው፡ አዲስነት የዚያን የነበሩን የተለምደውን (traditional) እና የተዘወተረውን አሮጌ ነገር መፈራረስ ያከትታል። ሕብረተሰቡ ያልጠበቃቸውን አዳዲስ ውጤቶች ማስገኘት ያስችላል- "እግዚአብሔር አዲስን ቅኔ ተቀኙለት" የሚል ቃል ተደጋግሞ ይገኛል (መዝሙር 144:9፣ 96:1፣ 98:1)። እግዚአብሔር ትኩስ በሆነና ከአሁን ጊዜ ውስጥ በሚፈልቅ የምስጋና ቃል ከፍከፍ ይላል። "አዲስ ቅኔ" የፈጠራን አቅጣጫና አፋኝ ከሆነው ባህላዊ ምላሽ አሰጣጥ ጋር ያልተገናኘ ለእግዚአብሔር ምላሽ የሚሰጥበትን ለየት ያለ ወቅታዊ መንገድ አመልካች ነው።

" እነሆ የቀድሞው ነገር ተፈፀመ አዲስ ነገርንም እናገራለሁ አስቀድሞም ሳይበቅል

ለመመልከት እንሞክራለን። ነገር ግን ዳዊት ባሳነጸው ድንኳን ምሳሌ የተገለጠውን ሥርነቀል የአደናደር ዘይቤ አመንጪ የሆነ መንፈሳዊ ሥርአት (system) በዘመኑ ፍጻሜ ላይ በምትገኘዋ ምድር ውስጥ ተመልሶ እንደገና ይገነባል። የዳዊት ድንኳን አሁን ምድር ላይ ባሉት ልማዳዊ እና ኃይማኖታዊ ሥርአቶች ውስጥ የተሸጋገሩ (advanced) መንፈሳዊ ከፍታዎችን (positions) ለማነጽ የሚያስችለውን ቴክኖሎጂ ይሰጠናል። ይህም አሠራር በእግዚአብሔር የተጠሩ ሕዝቦችን ሁሉ መንፈሳዊ ውርሶቻቸውን ለመቀበል ያንቀሳቅሳቸዋል። ባለፉት የእግዚአብሔር ንቅናቄዎች (Past moves of God) ጊዜ ከቤተክርስቲያን ጡጫ ያመለጡ መንፈሳዊ ጠላቶችን ሁሉ ባሁኑ ጊዜ ግን እንደገና ታድሳ በተሠራችው የዳዊት ድንኳን መርህ ሥር ለሚተዳደሩ ተሀድሶን አንቀሳቃሽ ለሆኑ ሕዝቦች ተላልፈው ይሰጣሉ።





## ምዕራፍ 5

# በተሀድሶ ውስጥ ጥርመሳን የሚያስገኙ ስልቶች

### ኢሳያስ 61ን እና 62ን አንብብ።

እነዚህ ሁለት ምዕራፎች በስፋት ስለተሀድሶ የሚያወሱ ሲሆኑ በጥንቃቄ ብንመረምራቸው ተሀድሶን ውጤታማ ሊያደርጉ የሚችሉ ጠቃሚ ስልቶችን ልናገኝባቸው እንችላለን። ኢሳያስ በእግዚአብሔር ስለተቀባው ስለ "መሲሁ" እና መሲሁ ስለሚገለገልባቸው መንፈሳዊ መሣሪያዎች ይናገራል። "መሲህ" የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን "ክርስቶስ" (Christos/Christ) በሚል ትርጓሜ ቀርቧል። ይህም "እግዚአብሔር ለክብሩ የተከላቸው የጽድቅ ዛፎች" የሚባልን አንድ ልዩ ሕዝብ ፈጥሮ ለዚህ ለእኛ ዘመን በመስጠት በውስጡ የተሸከመውን ቅባትና ክርስቶስ የሆነ መንፈሳዊ ጉልበት በማሳየት ላይ ይገኛል።

### የተሀድሶ ሕዝብ ባህሪ

በተሀድሶ መካከል እግዚአብሔር ያስነሳቸው ሰዎች በኢሳያስ 61:9 ላይ "እግዚአብሔር የባረካቸው ዘር" በመባል ይታወቃሉ። እስቲ የእነዚህን ወገኖች አንዳንድ ባህሪ እንመርምር።

***★ እግዚአብሔር የባረካቸው ዘር የሚባሉት በተወደደችው የእግዚአብሔር ዓመት (acceptable time) እና አምላካችን በሚበቀልበት ቀን (the day of vengence) ወደ ገሀድ የሚወጡ የተሀድሶ ሕዝቦች ናቸው።***

**" የተወደደችውን የእግዚአብሔርን ዓመት አምላካችንም የሚበቀልበትን ቀን እናገር ዘንድ የሚያስቅሱትንም ሁሉ አፅናና ዘንድ"**

**ኢሳ 61 : 3**

እነዚህ ሁስት ወቅቶች የዚያው የአንድ የተሀድሶ ዘመን ሁለት ገጾች ናቸው። ተሀድሶ ባንድ በኩል በእግዚአብሔር የተወደደ ዓመት ሲሆን በሌላው ደግሞ የእግዚአብሔር የበቀል ቀን ነው። እንግዲህ ለወራቱ የሚገባውን አጥጋቢ የተሀድሶ አስተሳሰብ ለማስገኘት እነዚህን ሁለቱን እውነታዎች ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልጋል።

"የተወደደ" የሚለው ቃል በዕብራይስጥ "ራትሶን" (ratson) ለሚለው የተሰጠ ትርጉም ነው። እግዚአብሔር የሞገሱን ሙላት በሕዝቡ ላይ እንዳፈሰሰ የሚያመለክት ቃል ነው። እግዚአብሔር በቃል ኪዳኑ የገነባቸውን ተስፋዎችና የፀጋ ስጦታዎች ሁሉ ወደ አንድ ኃይለኛ የመታዘዝና የዝግጁነት የጊዜ ክልል ውስጥ በገባ አንድ ሕዝብ ላይ በሙላት ለማፍሰስ የተዘጋጀበትን ወራት ያመለክታል። በዚህም ወቅት በአፋቸው ምድር አቀፍ የነፃ አውጪነት ቃል (word of global deliverance) ታጥቀው በአሕዛብ ላይ ትንቢታዊ ኃይለ ቃል በሚናገሩ ሕዝቦች መንፈሳዊ ባድማነት ተወግቶ ይደረመሳል።

**" እግዚአብሔር እንዲህ ይላል: - በተወደደ ጊዜ ለምቼሀለሁ በመድሀኒትም ቀን ረድቼሀለሁ እጠብቅሀማለሁ ምድርንም ታቀና ዘንድ ውድማ የሆኑትንም ርስቶች ታወርስ ዘንድ የተጋዙትንም ውጡ በጨለማም የተቀመጡትን ተገለጡ ትል ዘንድ ቃል ኪዳን አድርጌ ለህዝቡ ሠጥቼሀለሁ። በመንገድም ላይ ይሰማራሉ ማሰማሪያቸውም በወና ኮረብታ ላይ ይሆናል" ኢሳ 49 : 8 - 9**

የእግዚአብሔርን "ሞገስ" ከሚቀበለው ሕዝብ የሚጠበቀው ዋና ነገር መንፈሳዊ ችሎታ ዝግጁነትና





በሥፍራቸው ጸንቶ መቆም ነው። የእግዚአብሔር "ሞገስ" የሚሰቀቀው "ለጠቢባን" ብቻ ነው።

**" አስተዋይ አገልጋይ በንጉስ ዘንድ ይወደዳል በሚያሳፍር ላይ ግን ቁጣው ይሆናል"**

**ምሳ 14:35**

የተሀድሶ ሌላው ገጽታ በቀል መሆኑን ከዚህ በላይ ተመልክተናል እግዚአብሔር ሕዝቡን በሞገስ የሚያጥ-ሰቀልቅበት ጊዜ መንግሥቱን በሚቃወሙና ፍጻሜ ያስው ዓላማውና ሃሳቡ በሰዎች ልብ ውስጥ ስፍራ አግኝቶ እንዳይሠራና እንዳይንቀሳቀስ በሚያደናቅፉ ሰዎችም ሆነ ነገሮች ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ የሚፈነዳበት ጊዜ ነው።

**" ጽድቅን እንደጥሩር ለበሰ በራሱም ላይ የማዳንን ራስ ቁር አደረገ የበቀልንም ልብስ ለበሰ በቅንዓትም መጐናፀፊያ ተጐናፀፈ። እንደሰራቸው መጠን እንዲሁም ቁጣን ለባላጋራዎቹ ፍዳንም ለጠላቶቹ ይከፍላል ለደሴቶችም ፍዳቸውን ይከፍላል። "**

**ኢሳያስ 59 : 17-18**

የእግዚአብሔር ክብር ከእግዚአብሔር በቀል ጋር ሊለያይ አይችልም። በዘመነ ተሀድሶ የሚገለጠው የታላቅነቱ ግርማ ከታላቅ ፈራጅነቱ ተነጥሎ የሚታይ አይደለም።

**" ይሄ ከኤዶምያስ ልብሱም የቀላ ከባሶራ የሚመጣ አሰባበሱ ያማረ በጉልበቱ ጽናት የሚራመድ ማነው? . . . የምበቀልበት ቀን በልቤ ነውና የምቤዥበትም ዓመት ደርሷልና"**

**ኢሳ 63 : 1-4**

***★ እግዚአብሔር የባረካቸው ዘር የተበላሸውን ሥሪ እና የፈረሰውን ገንቢ ትውልድ ናቸው።***

የሚያተኩሩ ግርግሮችን ወደሚንቅ ትክክለኛ እምነት የተመሰሰች ናት። ያ አይነቱ ግርግር ወደ ጸረክርስቶስ አሠራር ያዘነብላል። ጳውሎስ "እውነትን" በማያጎሉ የአገልግሎት ትርኢቶች ዙሪያ ስለሚያተኩረው አመጸኛ (The Lawless one) ይናገራል።

> "የዓመፀኛው አመጣጥ በሰይጣን አሠራር ላይ የተመሠረተ ሲሆን ይህም በሐሰተኛ ተዓምራት በምልክቶች እና በድንቅ ነገሮች ሁሉ ይሆናል፤ እንዲሁም ይድኑ ዘንድ እውነት ባለመውደድ የሚጠፉት ሰዎች በሚያታልል በተለያየ የክፋት ሥራ ይመጣል።" 2ኛ ተሰሎንቄ 2:9-10 (አ.መ.ት.)

በመጨረሻ ቀናት እንደሰደድ እሳት ከሚገለጠው የሐሰት አሠራር ለመጠበቅ እውነትን የሚፈልግና የሚወደድ የልብ አቋም ጽኑ ለሆነ ሕዝብ አስፈላጊ ነው። የሚወደድ የልብ አቋም ጽኑ ለሆነ ሕዝብ አስፈላጊ ነው። ትክክለኛ ናቸው የምንላቸው ይዞታዎች ሁሉ በ "በክርስቶስ ትምህርት" (2ኛ ዮሐንስ 9) እውነት ላይ የተመሠረቱ ብቻ እንጂ ስጦታዎችን በመግለጥና ተዐምራዊ ምልክቶችን በማሳየት ዙሪያ ተወስነው የሚቀሩ መሆን የለባቸውም። ወደ ምልክቶች ብቻ የሚያደሉ ይዞታዎች ቤተክርስቲያንን በማዘናጋት ወደ እግዚአብሔር ጥልቅ ነገር በማያደርሱ ነገሮች ዙሪያ ተወስና ለመቅረት ያስገድዷታል። የተሀድሶ ሕዝቦች ቤተክርስቲያን ያጣችውን ጠንካራ ይዞታዋን ያስመልሱላታል።

## ★ የተሀድሶ ውጤታማነት አንቀሳቃሽ ኃይል

> "ምድርም ቡቃያዋን እንደምታወጣ ገነትም ዘሩን እንደሚያበቅል ጌታ እግዚአብሔር ፅድቅንና ምሥጋናን በአሕዛብ ሁሉ ፊት ያበቅላል።" ኢሳያስ 61:11

ጽድቅና ምስጋና በአሕዛብ ሁሉ ፊት ይበቅላል። ይህ ለእኛ የተሰጠ ትንቢታዊ የተስፋ ቃል ተግባራዊ እንዲሆን





ግን በተዘዋዋሪ የተነገረ ግዴታ አለ። እነዚህን መንፈሳዊ እሴቶች በአሕዛብ መካከል የማንቀሳቀስን ሥራ በአትክልት ሥፍራ (ገነት) መስሎታል። በዚህ ሥፍራ ሊበቅል የሚችለው አስቀድሞ የተዘራው ብቻ ነው። እግዚአብሔር በአሕዛብ ውስጥ የኃይሉንና የዕውነቱን አንዳንድ ምልክቶች ሊያበቅል ከተፈለገ በትንቢታዊ ተስፋዎች መሠረት እርምጃ ለመውሰድ ችሎታው ያላቸው የተሀድሶ ሰዎች ሊኖሩ ይገባል።

ይህ አባባል ብዙ ሐሳብ ተሸክሟል። የተሀድሶ ሕዝብ ኃላፊነት በሚሰማው ሁኔታ የሚንቀሳቀስ ሕዝብ ነው። የትንቢታዊ ተስፋዎች ባለአደራ ነው። በምድር ላይ የሚሆነው የዚህ ሕዝብ እንቅስቃሴ ትንቢታዊ ተስፋዎች ወደሚታይ ተጨባጭ ዕውነት እንዲመጡ ወሳኝ ነው። የተሀድሶ ሕዝቦች በሐዋሪያዊና ትንቢታዊ መንፈስ የተሞሉ በመሆናቸው የእግዚአብሔርን የፍጻሜ አለማዎች በመንፈ-ሳቸው አይተው በትክክል ማቀድና መገንባት ይችላሉ። አስቀድሞ የተተከለው ብቻ ነው ከጊዜ በኋላ በአሕዛብ ፊት ሊበቅል የሚችለው።

የተዘራው ነገር ለዚያ ሊመጣ ላለው ነገር ዘር ነው። ዘመብቀል ጊዜ የመጀመሪያው ፍሬ በመጠንም በብዛትም ይጨምራል። በዚሁ መርህ መሠረት እግዚአብሔር በተሀድሶ ቤተክርስቲያን ውስጥ ያለውን የሐዋርያዊና ትንቢታዊ እንቅስቃሴ ዘር እንዲፋጠንና እንዲበዛ ያደረገ-ዋል። ኢሣያስ እንዳለው በአሕዛብ ሁሉ ፊት ይታያል።

## ★ አምስት የጥርመሳ ስልቶች

> "እለፉ በበሮች በኩል እለፉ የሕዝብንም መንገድ ጥረጉ፣ አዘጋጁ፣ ጎዳናውን አዘጋጁ፣ ድንጋዮቹንም አስወግዱ፣ ለአሕዛብም አላማ አንሱ" ኢሣያስ 62:10

## ★ አንደኛ ስልት፡- በበሮች በኩል አለፉ

በልማዳዊ መረዳት "በሮች" የጠላትን ስይጣናዊ ምሽጎች ያመለክታል። በዚህ ጥቅስ ግን የእግዚአብሔርን በሮች ለማለት ነው። ሊያጸኑን የሚችሉ አምባዎች ማለትም የብርታትና የኃይል ሥፍራዎች ፈጣሪ እግዚአብሔር ነው።

> "የፅድቅን ደጆች ክፈቱልኝ ወደ እነርሱ ገብቼ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። ግንበኞች የናቁት ድንጋይ፣ እርሱ የማዕዘን እራስ ሆነ ይህች ከእግዚአብሔር ዘንድ ሆነች፣ ለዓይና-ችንም ድንቅ ናት። እግዚአብሔር የሰራት ቀን ይህቺ ናት ሐሴትን እናድርግ፣ በእርሷዋም ደስ ይበለን። አቤቱ እባክህ አሁን አድን፣ አቤቱ እባክህ እሁን አቅና። በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ብሩክ ነው። ከእግዚአብሔር ቤት መረቅናችሁ" መዝሙር (118)፡19-26

ይህ መዝሙር "ኃሜል" ተብለው ከሚታወቁት መካከል የመጨረሻው ሲሆን ሕዝቦች በሰልፍ አምልኮ ወደ ቤተመቅደሱ ደጆች በመጓዝ ላይ ሳሉ በተለምዶ የሚዘ-ምሩት ዝማሬ ነው። የሰልፉ ጊዜ የተቀናበረው ምናልባትም ሕዝቡ ልክ ወደ መቅደሱ ሲቀርቡ የመቀደሱ ደጆች እንዲከፈቱላቸው ያንን መዝሙር ከፍ ባለ ድምጽ እንዲዘምሩት ታስቦ ነው። ስለዚህ አምላኪዎቹን ለማስገባት ብርግድ ብለው የሚከፈቱት ደጆች ወደራሱ ወደ እግዚአ-ብሔር መገኛ ዘልቆ ከመግባት ጋር ተመሳሳይ ናቸው። እግዚአብሔር የሠራው ያ ቀን ወደ እግዚአብሔር የመግቢያ ትክክለኛ ቀን ሆኖ የተወሰነ ነበር። ለአዲስ የመግባት ዕድል በሮቹ ወለል ብለው የተከፈቱበት ቀን ነበር።

ድንቅ የሆነውን ትዕይንት ማለብ እንችላለን። ሕዝቡ የዳዊትን የምስጋና መዝሙራት እየዘመሩ ወደ ፊት ይጓዛሉ። በሮቹ እንዲከፈቱ የሚጠይቀውን የዳዊት የመጨ-ረሻ መዝሙር በመጮህ የሚጠናቀቅ ወደ እግዚአብሔር





መቅረቢያ የተቀደሰ ጉዞ ነው። በሮቹ በገ/ግታ እየተበረገዱ ሳለ ሕዝቡ በሙሉ ኃይላቸው "በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው" እያሉ ይጮሀሉ። ይሄም በመግቢያ መዳረሻ ላይ የሚሆን ቃላቸው ነው።

ይሄ ቃል ትልቅ ሚስጥር ያዘለና ለዛሬው የተሀድሶ ትውልድ ትንቢታዊ መልእክት ያለው ነው። በማቴዎስ 23 ላይ ኢየሱስ ፈሪሳውያንን አስመሳይና ሞኞች እያለ ይቃወማቸዋል። የፈሪሳዊነት መንፈስ ትዕቢትና ውጫዊ (አስመሳይ) ትርኢቶች በለፈኑበት ሥፍራ ይሠለጥናል። በማታለል (duplicity) እና መንፈሳዊ ሞት የተሞላ ነው። ትንቢታዊው አሠራር በእግዚአብሔር ሕዝብ ዘንድ እውቅና እንዳይኖረው በማድረግ አሁን እየተለቀቀ ያለውን የእግዚአብሔር ድምጽ በቤተክርስቲያን ይቃወማል (ቁ.29-31) ነገር ግን ከሁሉ የበለጠ ገዳይ አሠራሩ የመንግሥቱን በሮች በመዝጋት ላይ ያተኮረ ነው። ለመግባት እምቢ ብሏል። ሌሎችንም ከልክሏል። ጉዳዩ የመግባት ጥያቄ ነው። የእግዚአብሐር ደጆች (የቃሉ መገለጥ ደጆች) ተዘግተዋል።

> " እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፣ መንግሥተሰማያት በሰው ፊት ስለምትዘጉ ወዮላችሁ። እናንተ አትገቡም የሚገቡትንም እንዳይገቡ ትከለክላላችሁ።" ማቴዎስ 23፡13

ፈሪሳዊነትን በሚያወግዝ በዚህ ሁሉ ንግግሩ መካከል ኢየሱስ ድምጹን አንስቶ ስለ ኢየሩሳሌም የሚሰማውን የልቡን ሀዘን ይገልጣል። በትንቢታዊ አግባቡ ይሄን መሰል ቃሉ ለቤተክርስቲያንም መልእክት አለው።

> " ኢየሩሳሌም ኢየሩሳሌም ሆይ ነቢያትን የምትገድል ወደ እርስዋ የተላኩትንም የምትወግር ዶሮ ጫጩቶችዋን ከክንፎችዋ በታች እንደምትሰበስብ ልጆችሽን እሰበስብ ዘንድ ስንት ጊዜ ወደድሁ ! አልወደዳችሁም። እነሆ ቤታችሁ የተፈታ ሆኖ ይቀርላችኋል።

> እላችኋለሁና በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው እስክትሉ ድረስ ከእንግዲህ ወዲህ አታዩኝም፡፡” ማቴዎስ 23:37-39

ቤተክርስቲያን ትንቢታዊውን የአገልግሎት ፀጋና አሠራር ከመካከልዋ ስለገደለችና መልእክት ይዘው ወደ እርስዋ የተላኩትንም ሐዋርያዊ ወገኖች ስላሳደደች ዛሬ በመንፈሳዊ ምድረበዳ ውስጥ ትገኛለች፡፡ ይሄ ዓይነቱ አቋም ቤተክርስቲያንን ወደ ጌታ እንዳትሰበሰብ ከለከላት፣ ምክንያቱም ለመሰብሰብ አመቺ ባልሆነ ሥፍራ ላይ ተገኝታለችና ነው፡፡

የእግዚአብሔር ሕዝብ መዝሙር (118) ላይ እንደ ተመለከትነው ባለ ታላቅ ጩኸት በማወጅ በበር አልፎ ወደ ሚገባበት ሥፍራ እስካልመጣ ድረስ ቤተክርስቲያን እግዚአብሔርን ማየት አይፈቀድላትም፡፡ አሁንም እንደገና “በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው” ወደሚያሰኝ ሁኔታ ልትገባ ትጠበቃለች፡፡

በዚህ አባባል የጌታን ወደ ቤተክርስቲያኑ የመምጣት ተስፋ ከማሰብ የጠለቀ ነገር እናያለን፡፡ ቁጥር 39 ላይ ያለው ስለ “ማየት” የተነገረ ቃል (አታዩኝም) “Oida” አይዳ የሚለውን የግሪክ ቃል ወክሎ የገባ ነው፡፡ ትርጉሙም ጥልቅ ከሆነ ማስተዋል የሚገኝን የዕውቀት ሙላት ያመለክታል፡፡ ስለዚህ “በበሮቹ በኩል መግባት” የሚያመለክተው የእግዚአብሔር ሕዝብ ሐዋሪያዊና ትንቢታዊ የጸጋ መካፈልን ለመቀበልና የራሱ ለማድረግ ከዚያም የተነሳ ጠንካራ አዋጆችን ከአንደበቱ አውጥቶ መናገርንና ጥልቅ በሆነ ማስተዋል እግዚአብሔርን ሙሉ ለሙሉ ወደማወቅ ደረጃ መሻገርን ነው፡፡ በዚህ ተሀድሶ ታላላቅ አዋጆችን እየተናገርን በበሮቹ በኩል አልፈን በመንግሥቱ ውስጥ ወዳሉ አዳዲስ ይዞታዎች ልንደርስ ያስፈልጋል፡፡

በሮቹ እንዲከፈቱላት በምትጣራበት በዚያን ዕለት ቤተክርስቲያን “እውነትን የሚጠብቅ ጻድቅ ሕዝብ” ልትሆን ይጠበቅባታል፡፡



የአሁኑ ዘመን የቤተክርስቲያን ተሃድሶ

> “ በዚያም ቀን ይህ ቅኔ በይሁዳ ምድር ይዘመራል፣ የጸናች ከተማ አለችን ለቅጥርና ለምሽግ መድኃኒትን ያኖርባታል፡፡ እውነትን የሚጠብቅ ጻድቅ ሕዝብ ይገባ ዘንድ በሮችን ክፈቱ” ኢሳያስ 26:1-2

ይህ መዝሙር የሚዘመርበት ቀን የተሀድሶ ቀን ይሆናል፡፡ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ድካምን ወደዚያ አሽቀንጥረው ጥለው “የጸናች ከተማ” ሆነው የሚገለጡበት ቀን ነው፡፡ እግዚአብሔር በሕዝቦች አእምሮ ላይ ጠላት የጋረደውን የሞት መጋረጃ ለመቀደድ ፍልሚያ የሚያፋፍምበትና ሞትን ለዘላለም ሊደመስስ ጦርነት የሚከፍትበት ቀን ይሆናል፡፡

> “ በዚህም ተራራ ላይ በወገኖች ሁሉ ላይ የተጣለውን መጋረጃ በአሕዛብ ሁሉ ፊት የተዘረጋውን መሸፈኛ ያጠፋል፡፡ ሞትን ለዘላለም ይውጣል፣ ጌታ እግዚአብሔርም ከፊት ሁሉ እንባን ያብሳል፡፡ የሕዝቡንም ስድብ ከምድር ሁሉ ላይ ያስወግዳል፣ እግዚአብሔር ተናግሮአልና፡፡” ኢሳያስ 25:7-8

እግዚአብሔር ለአሕዛብ ወዳዘጋጃቸው የፍጻሜ ዓላማዎች በበሮች በኩል ለመግባት ቁልፉ የሆነው መርህ የእግዚአብሔር “ጻድቅ ሕዝብ” ዕውነትን መጠበቅ ያለበት መሆኑ ነው፡፡ መጠበቅ ማለት መከላከል መጋረድ ወይም ትኩር ብሎ ማየት ነው፡፡ አንድ የተሀድሶ ሕዝብ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥልቅ ዕውነታዎችን ለመያዝ በአዲስ ትኩረት መንቀሳቀስ እንዳለበትና እነዚህም ዕውነቶች ከጠላት የማምታታት አሠራሮች በልዩ ጥንቃቄ ሊጠበቁ እንዳለባቸው ማወቅ ያስፈልጋል፡፡

## * ሁለተኛ ስልት፡- ለሕዝቡ መንገድን አዘጋጁ

ይሄ በኢሳያስ 40:3-5 እንዳለው የኤልያስ አይነቱ ለጌታ መንገድን የማዘጋጀት ጥሪ አይደለም፡፡ እዚህ ላይ

እየተነገረን ያለው መንገድን ለሕዝቦች እንድናዘጋጅ ሲሆን ይሄም ለዘመናችን ጥርመሳን የሚያስገኝ ግልጽ የተሀድሶ ስልት ነው። በኢሳያስ 61፡9 ያለው ትዕዛዝ በኢሳያስ 57፡14 ላይ ካለው የተሀድሶ እውነት ፍሰት ጋር የሚጣመር ነው።

> " እርሱም ጥረጉ መንገዱን አዘጋጁ፣ ከሕዝቤም መንገድ ዕንቅፋትን አውጡ ይላል።" **ኢሳያስ 57፡14**

ከሕዝቡ መንገድ ላይ እንቅፋትን ለማስወገድ እውነትን በመረዳት በኩል ያለውን ጎድንዳነት መደልደልና የመረዳት ደረጃን ከፍ ማድረግ ነው። በዘመነ ተሀድሶ ይሄ አሠራር እጅግ አስፈላጊ ነው። "እርሱም...ይላል"፡- በአንድ ወደፊት በሚገሰግስ ተራማጅ ሕዝብ መካከል የአዲስን መንፈሳዊ እንቅስቃሴ በሥራ ላይ መዋል መናገር፣ በትንቢት ቃል ማስተጋባት የግድ ነው። ትንቢታዊ የማስተዋወቅ ሥራ ለሕዝቡ መንገድን በማዘጋጀት እንቅ-ስቃሴ ወሳኝ የሆነ ስልት "Technology" ነው። "አዘጋጁ" የሚለው ቃል ትርጉም ሙሉ በሙሉ አዲስ ወደሆነ መስመር መግባትን ያመለክታል። በዘመነ ተሀድሶ ሕዝቡን ወደ አዲስ ነገሮች ሲያስገባ የሚያስችስውን የዚያን ትንቢ-ታዊ ንግግር ውስጣዊ አሠራር ስልት እንመርምር።

> **" በኃይልህ ጩኽ፣ አትቆጥብ ድምፅህን እንደ መለከት አንሣ፣ ለሕዝቤ መተላለፋቸውን ለያዕቆብም ቤት ኃጢአታቸውን ንገር"**
> **ኢሳያስ 58፡1**

ትንቢታዊው ድምጽ እንደመለከት ወደላይ ከፍ ሊል ይገባል። ይሄም ለተሀድሶ የሚገባውን የልብ ሰውጥ ለማምጣት በሚደረገው ሂደት ላይ ቁልፍ ሚና አለው። መለከት ትንቢታዊ ንግግርን ለማመልከት በተደጋጋሚ የተጠቀሰ ምሳሌያዊ ቃል ሲሆን የተለያዩ ትርጉሞችን መሸከም ይችላል። እስቲ አንዳንድ የመለከት መርሆችን እንመልከት።





## የመለከት መርህ ቁጥር አንድ መግባትና መንቀሳቀስ

> **" ወሰንም ለሕዝቡ በዙሪያው አድርግላቸው፡- ወደ ተራራው እንዳትወጡ ጫፉንም እንዳትነኩ ተጠንቀቁ ተራራውንም የነካ ፈጽሞ ይሞታል። የማንም እጅ አይንካ ነገር ግን የሚነካ ሁሉ ይወገራል ወይም በፍላጻ ይወጋል አይድንም በላቸው። ሳያቋርጥ የመለከት ድምጽ ሲነፋ በዚያን ጊዜ ወደ ተራራ ይውጡ። የቀንደ መለከት ድምፅ እጅግ በበረታና በጸና ጊዜ ሙሴ ተናገረ እግዚአ-ብሔርም በድምጽ መለሰለት።"**
> **ዘፀአት 19፡12-13 እና 19**

በዚያን ቀን እግዚአብሔር ከነሙሉ ክብሩ በሲና ላይ ወረደ። ሕዝቡ የተራራውን ጫፉን እንኳ እንዳይነኩና ቢነኩት እንደሚሞቱ ማስጠንቀቂያ ተሰጣቸው። በተራራው ላይ የወረደው መንፈስ አስፈሪነቱ እጅግ ታላቅ ነበር። መለከቱ በተነፋ ጊዜ ብቻ ነበር ወደ ተራራው ወደ እግዚአ-ብሔር ክብር መቅረብ እንኳ የሚፈቀድላቸው። እዚህ ላይ ያለው ቁልፍ ነገር የመግባት "ዕድልን የማግኘት" ጉዳይ ነው። የመለከቱ ድምጽ ከልካይ ከሆነው የእግዚአብሔር ትዕዛዝ አልፎ መግባት የተፈቀደ መሆኑን የሚያሳይ ምልክት ነው።

መለከት በሌላ በኩል በምድርና በስማይ መካከል ውይይት መንቀሳቀስ የጀመረ ለመሆኑ ምሳሌያዊ አመልካች ነው። የመለከቱ ድምጽ ይበልጥ በጨመረ መጠን ወይም በመንፈሳዊ ትርጉሙ ትንቢታዊ አዋጅ በምድር ላይ ጥልቅነትን፣ ግልጽነትንና ኃይልን በጨመረ ጊዜ ሙሴ እግዚአብሔርን ማነጋገር ይጀምር ነበር። እግዚአብሔርም ሊያስተውሉት በሚቻል መንገድ ለሙሴ ይመልስለት ነበር። ሦስተኛውን ሺህ ዓመት እየቀረብነው በመምጣት ላይ ባለንበት ጊዜ በቤተክርስቲያን ውስጥ ያለው የትንቢት ድምጽ ረጅምና ጩኸት የተሞላ ፍንዳታን የመሰለ ሲሆን በስማይ ካለው የእግዚአብሔር ዓላማ ጋር አዲስን

የግንኙነት ደረጃዎች ክፉች ነው፡፡ የእግዚአብሔር ድምጽ ከዚህ በኋላ የማይሰማና የተከለከለ ሊሆን አይችልም፡፡ ዓላማዎቹ በምድር ግልጽ ሆነው እያበሩ ሲሆኑ የተሀድሶ ሕዝቦች ደግሞ በግልጽ ለሚሰሙት “መለኮታዊ ቋንቋ” የመግቢያ ፈቃድ (Access) አላቸው፡፡

## የመለከት መርህ ቁጥር ሁለት ነፃነትና መልሶ መውረስ

**“ ከዚህም በኋላ በሰባተኛው ወር በአሥረኛው ቀን በቀንደመለከት ታውጃለህ በማስተሰረያ ቀን በምድራችሁ ሁሉ በቀንደመለከት ታውጃ ላችሁ፡፡ አምሳኛውንም ዓመት ትቀድሳላችሁ በምድሪቱም ለሚኖሩባት ሁሉ ነጻነትን ታውጃላችሁ እርሱ ለእናንተ ኢዮቤልዩ ነው፡፡ ሰው ሁሉ ወደርስቱና ወደ ወገኑ ይመለስ”**

**ዘሌዋውያን 25:9-10**

የኢዮቤልዩ ቀንደመለከት (ኢዮቤልዩ - የተወደደችው የእግዚአብሔር ዓመት) (ኢሳያስ 61:2) “በምድራቸው ሁሉ” የሚታወጅ ቃል ነበር፡፡ ለሕዝቡ የመፈታትና ከተጽእኖ ነፃ የመውጣት ጊዜ የመምጣቱን የምሥራች ከመስማት ሊያመልጥ የሚችል የምድሪቱ ክፍል አይኖ-ርም፡፡ ስለዚህ ቀንደመለከት ከነፃ መውጣት ጋር የተቆራኘ ነው፡፡ ንብረታቸው የተወሰደባቸውና የተሰደዱ ሁሉ ወደ ቀደመው ርስታቸው ሙላት የመመለሻ ቀናቸው ነበር፡፡ ቀንደመለከቱ በእሥራኤል መለኮታዊ ሥርዓት መመለሻ ብቻ ሳይሆን ሕብረተሰቡን ከተመስቃቀለ የችግር ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ትክክለኛ መለኮታዊ ዓላማ የሚመልስ ነበር፡፡ ባለዕዳዎች ከገቡበት ግዴታ ሁሉ ነፃ ወጥተው ጭቆናና ግፍ ሁሉ በእግዚአብሔር የማስተካከያ አስተዳደር ሥር በመዋሉ የቤተሰብ ንብረቶች ለባለመብቶቹ የሚመለሱበትና ያለፉ ጊዜያት ስሕተቶች የሚታረሙበት ነበር፡፡

እዚህ ላይ አንድ ኃይለኛ የሆነ ትንቢታዊ አሠራር አለ፡፡ ተሀድሶን በምድር ላይ የሚያስተዋውቀው ቀንደ





መለከት የፈሪሳዊ መናፍስተንና የኃይማኖተኛ አመለካከት ጭቆናዎችን ሰብሮ ቅዱሳንን አስቀድሞ የቤተክርስቲያን ወደነበረው የኃይልና መጽሐፍቅዱሳዊ የእግዚአብሔር ዓላማ ውርሳቸው (ርስታቸው) ይመል ሳቸዋል፡፡

## የመለከት መርህ ቁጥር ሦስት ኃላፊነትና ትክክለኝነት

**“ የሰው ልጅ ሆይ ለሕዝብህ ልጆች ተናገር እንዲህም በላቸው፡- ሰይፍን በምድር ላይ ባመጣሁ ጊዜ የምድር ሕዝብ ከምድር ሕዝብ ከመካከላቸው ሰው ወስደው ለራሳቸው ጉበኛ ቢያደርጉ እርሱም በምድር ላይ የመጣውን ሰይፍ ባየ ጊዜ መለከትን ቢነፋ ሕዝቡንም ቢያስጠነቅቅ የመለከቱንም ድምጽ የሚሰማ ሰው ባይጠነቀቅ ሠይፍ መጥቶ ቢወስደው ደሙ በራሱ ላይ ይሆናል፡፡ የመለከትንም ድምጽ ሰምቶ ስላልተጠነቀቀ ደሙ በራሱ ላይ ይሆናል ቢጠነቀቅስ ኖሮ ነፍሱን ባዳነ ነበር፡፡”**

**ሕዝቅኤል 33:2-5**

እዚህ ሥፍራ ላይ “ጉበኛ” የሚለው ቃል በቤተክርስቲያን ላይ እየመጣ ያለውን ሁኔታ ከሩቅ አይተው የሚያሳውቁ እግዚአብሔር በአመለካከት ከፍታ ላይ ያስቀመጣቸው ናቸው፡፡ ጉበኛው እየመጣ ያለውን ችግር መመልከት ይችላል፣ የተመዘዘውን “ሰይፍ” ያያል፡፡ በችግሮች መካከል ቁልፍ የሆነው የሞትና ሕይወት ጥያቄ የቀንደ መለከቱ ድምጽና ለድምጹ የሚሰጠው ምላሽ ዐይነት ነው፡፡

ቀንደ መለከቱ ችል ተብሎ ጥፋት ቢከተል አልታዘዝ ባዩ ኃላፊነቱን ይሸከማል፡፡ ማስጠንቀቂያውን የለማ የራሱን ነፍስ ይታደጋል፡፡ ስለዚህ ቀንደመለከቱ ወይም ትንቢታዊው የማስጠንቀቂያ ቃል በመከራ ሰዓት ትክክለኛ እርምጃ እንዲወስድ ያንቀሳቅሳል፡፡

በተሀድሶ ዘመን ለወራቱ የሚገባውን ትንቢታዊ ቃል ከፍ አድርገው የሚነግሩ ሰዎች የቃላቸው ጥራትና ትክክለኛነት ወይም ሊያድን አለዚያም ጉዳት ለማድረስ ችሎታ እንዳለው ሊያውቁት ይገባል።

*መጀመሪያ "ማየት" ከዚያም መለከቱን "መንፋት"* የግድ ነው። ቃልን ከእግዚአብሔር አፍ ሊሰሙ ከዚያም ሕዝቡን ሊያስጠነቅቁ ይገበል (ሕዝ. 33:7)።

### *★ ሦስተኛ ስልት፦ አውራ ጎዳናውን (high way) ሥሩ*

በጎዳና መሄድ በእግዚአብሔር ዓላማዎች ትክክለኛ መስመር ላይ መራመድ ነው። ከጎዳናው መልቀቅና ባልተሠራው ጠማማ መንገድ መራመድ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ስቶ ወደጥፋት መውረድ ነው።

> **" ሕዝቤ ግን ረስተውኛል ለከንቱ ነገርም እጥነዋል ከመንገዱም ተሰናክለዋል ከቀድሞ ውም ጎዳና ርቀው ወዳልተሰራው ወደ ጠማማው መንገድ ፈቀቅ ብለዋል። ምድራቸ-ውም ለመደነቂያና ለዘላለም ማፍዋጫ እድርገዋል የሚያልፍበት ሁሉ ይደነቃል ራሱንም ያነቃንቃል በጠላት ፊት እንደ ምሥራቅ ነፋስ እበትናቸዋለሁ በጥፋታቸውም ቀን ጀርባዬን እንጂ ፊቴን አላሳያቸውም። "**
> **ኤርምያስ 18:15-17**

ጎዳናዎቹ በሕዝቦች መንፈሳዊ የጉዞ ሂደት ላይ ካልተመሠረቱ እነዚያ ሕዝቦች ይሰናከላሉ ምድራቸውም ምድረበዳ ይሆናል። "ምድራቸው" በመንፈሳዊ ክልል ሰብስበውት የነበረውን የበረከት ድምር የሚወክል ቃል ነው። በሕይወት ልምዳቸው ውስጥ ሊንጸባረቁ የሚገባቸውን መለኮታዊ ሥርዓትና አደረጃጀት በቃለ መርህ ላይ የተመሠረተውን የኑሮ ዘይቤአቸውንና ባሕሩ ማንነታቸውን ይወክላል። ጎዳናውን ሲለቁ ሕዝቦች የውጊያ ብቃታቸውን ይጥላሉ። ጠላት እንዲበትናቸው ተላልፈው ይሰጣሉ፣ ከእግዚአብሔርም ሞገስ ተለይተው ይሰደዳሉ።





በጥፋት ቀን የእግዚአብሔርን ጀርባ እንጂ የሞገስና የበረከት ፊቱን ሊያዩት አይችሉም። ስለዚህ በምድር የነውጥ ሰዓት እነዚህ ወገኖች የመቋቋምና የማምለጥ ጉልበት አይኖ-ራቸውም።

የጎዳናው (የትክክለኛው የጉዞ መንገድ) ልምምድ ቸል በተባለበት ዘመን ቤተክርስቲያንን በተሀድሶ አመለካ-ከትና አስተሳሰብ ጸጋ መካፈል በኩል ወደዚያው ወደ ቀደመው የጎዳና የኑሮ ዘይቤ ለመመለስ የተለየ ዐይነት አገልግሎት ይጠይቃል።

> **" በዓናት ልጅ በሰሜጋር ዘመን በኢያዔል ዘመን መንገዶች ተቋረጡ መንገደኞች በስርጥ መንገድ ይሄዱ ነበር። አንቺ ዲቦራ እስክትነሺ ድረስ ለእሥራኤልም እናት ሆነሽ እስክትነሺ ድረስ ኃያላን በእሥራኤል ዘንድ እነሱ እሰቁም።" መሳፍንት 5:6-7**

ዲቦራ ተፈረካክሶ ወደነበረ አንድ ሕብረተሰብ እድገ-ትንና ብርታትን ለማምጣት በእሥራኤል ላይ የተቀጣጠለን አንድ ሐዋርያዊ ተሀድሶ ትወክላለች። ጎዳናዎቹ ተረስተ-ዋል፣ መንገደኞቹም በጎደሎና ባለቀ ደካማ ልምምድ ይሄዱ ነበር። የመጨረሻ ውጤቱ ማሕበራዊው ሥርዓት ወይም የከተማ ኑሮአቸው እጅግ አጠያያቂ ሁኔታ ውስጥ ሊወድቅ መገደዱ ነበር። የከተማ ኑሮ ስንል የጋራ ልምምዳቸውን፣ መንፈሳዊ መዋቅሩንና በተስተካከለው የእግዚአብሔር እቅድ መሠረት ወደ ፍጽምና የሚያደርጉትን ጉዞ ለማመልከት ነው።

ይሄ ሁኔታ ዲቦራ እስከተነሳችበት ጊዜ ድርስ ሰፍኖ ቆየ። "ተነሺ" የሚለው ቃል ሌላ ትርጉም ደግሞ አስቀድመው የተወሰኑና የታቀዱ ነገሮችን ወደተግባር ማምጣት ያንጸባርቃል። ጥንካሬው የሚመነጨው ሊገታ (ሊያስቆሙት) የማይቻል ከመሆኑ ላይ ነው።

ጎዳናዎቹ እስከ ሰሜጋር ዘመን እንኳ ቸል ተብለው እንደቆዩ ማስተዋል አስፈላጊ ነው። ሰሜጋር በእሥራኤል ውስጥ ታዋቂ ጦረኛ ነበር።

> " ከእርሱም በኋላ የዓናት ልጅ ሰሜጋር ተነሣ፣ ከፍልስጤማውያንም ስድስት መቶ ሰው በበሬ መውጊያ ገደለ፣ እርሱም ደግሞ እሥራኤልን አዳነ" መሣፍንት 3:31

ሰሚጋር የእግዚአብሔር ጠንካራ ምልክቶች ማሳየት የሚችል ነገር ግን ባለው የቤተክርስቲያን አመለካከትና አስተሳሰብ ላይ ለውጥ ለማስከተል የተሀድሶ ብቃት የሚጎድለውን በቤተክርስቲያን ያለ ኃይለኛ የአገልግሎት ቅባት ይወክላል። ይህ ሊገባን እጅጉን አስፈላጊ ነው። በተአምራትና በምልክቶች ላይ ያነጣጠረችን ቤተክርስቲያን ይዘን ወደ እግዚአብሔር የፍጻሜ ዓላማዎች መገስገስ አንችልም። እነዚህ ነገሮች ቅዱሳንን ለማሳደግና የእግዚአ-ብሔርን ኃይል ለመግለጥ ወሳኝና ጠቃሚዎች ቢሆኑም የሕዝቡን ልብ ለመመለስ እግሮቻቸውንም እንደገና በጎዳናው ላይ ለማጽናት የዲቦራን ጸጋ በማካፈል ውስጥ ያለውን ኃይል ልናቀጣጥልባቸው ይገባናል።

ጎዳናዎችን እንደገና መገንባት የተሀድሶንና የመልሶ ማቋቋምን ዘመን ያመለክታል።

> " እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በተወደደ ጊዜ ሰምቼሃለሁ፣ በመድኃኒትም ቀን ረድቼሃለሁ፣ እጠብቅህማለሁ፣ ምድርንም ታቀና ዘንድ ውድማ የሆኑትንም ርስቶች ታወርስ ዘንድ የተጋዙትንም፦ ውጡ በጨለማም የተቀመጡ ትንም፦ ተገለጡ ትል ዘንድ ቃል ኪዳን አድርጌ ለሕዝቡ ሰጥቼሃለሁ። በመንገድም ላይ ይሰማራሉ፣ ማሰማርያቸውም በወና ኮረብታ ሁሉ ላይ ይሆናል። የሚራራላቸው ይመራቸ-ዋልና በውኃ ምንጮች በኩል ይነዳቸዋልና አይራቡም፣ አይጠሙም፣ ትኩሳት ወይም ፀሐይ አይጉዳቸውም። ተራሮቼን ሁሉ መንገድ አደርጋለሁ። ጎዳኖቼም ከፍ ከፍ ይላሉ።" ኢሳያስ 49:8-11





> ላይ የወይን ቦታ ነበረው። በዙሪያው ቆፈረ፣ ድንጋዮችንም ለቅሞ አወጣ፣ ምርጥ የሆነ-ውንም አረግ ተከለበት፣ በመካከሉም ግንብ ሠራ፣ ደግሞም የመጥመቂያ ጉድጓድ ማሰበት ወይንም ያፈራ ዘንድ ተማመነ ዳሩ ግን ሆምጣጣ ፍሬ አፈራ" ኢሳያስ 5:1-2

ድንጋዮችን ለቅሞ ማውጣት የአንድ ረጅም ሂደት አካል ነው። ድንጋዮቹ እንዲወገዱ የሚደረጉት ምርጥ የሆነውን ወይን ለመትከል ነው። ወይኑ የሚወክለው እጅግ የጠራውን (ያልተበከለውን) የእግዚአብሔርን ዓላማና ፈቃድ ነው። በዚህ ዘመን እግዚአብሔር በሌላ በየትኛውም ዘመን ታይቶም ተሰምቶም ያልታወቀ የመልካም ፈቃዱን የወንዝ ሙላት በቤተክርስቲያኑ በኩል ማፍሰስ ጀምሮአል።

በሂደቱ መካከለኛ ሥፍራ ላይ የእግዚአብሔር መጠበቅ (expectation) አለ። መልካምን ወይን ያፈራለት ዘንድ ተማመነ። መልካም ወይን የሚወክለው ለዚህ የመጨረሻው ዘመን ትውልድ የተጠበቁ ታላላቅ የእውነቱ መገለጦችና የክብሩ መንጸባረቆችን ነው። እዚህ ላይ የሚታየው አቢይ ቁም ነገር የአገልግሎትን ባህሪ ከመለወጥ በጣም ያለፈ ነገር ነው። ከእግዚአብሔር የሆነ ተሀድሶ የአንዲትን አጥቢያ ቤተክርስቲያን የአምልኮ አገልግሎት ከማሻሻል ወይም በቤተክርስቲያኒቱ ዓመታዊ መርሀግብር ላይ ለውጦችን ከማድረግ በእጅጉ የተሻለ ነገር ነው። በዚህ ዘመን በዚች ምድር ላይ ልናከናውናቸው እግዚአብሔር ከእኛ የሚጠብቅብንን ነገሮች ጠልቆ ለማየት የሚያስችል ውስጣዊ የሆነ የአስተሳሰብ ለውጥ ይጠይቃል።

> " የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን አለም አትምሰሉ" ሮሜ 12:2

በአእምሮ መታደስና በመንፈሳዊ አስተሳሰብ መለወጥ በኩል ብቻ ነው ደረጃ በደረጃ የሚገለጠውን

የዳዊትን የመግዛት መንፈስና የአእምሮ በምድር ላይ የምታንጸባርቅ የመጨረሻው ዘመን ቤተክርስቲያን ይገልጣል። ከእንግዲህ ወዲህ ተዋጊና ታማኝ (የምትታዘዝ) በሆነች ቤተክርስትያኑ በኩል የሚኖረው የክርስቶስ መገለጥ እንጂ ኃይማኖት አሕዛብን ሊስባቸው አይችልም። ቤተክርስቲያን ምልክቱ (ባንዲራው) (በምትሆንበት ወቅት አሕዛብ እርሱን ፈልገው ይመጣሉ (ምልክቱ ባለበት እርሱ አለ)።

ባንዲራው ወይም ምልክቱ ከፍ ብሎ በሚውለበለብበት ለዓት "የሕዝቡን ቅሬታ" "ከአራቱም የምድር ማዕዘናት" (ቁ.12) ለማስባለብ ከጌታ ዘንድ ትልቅ መነሳሳት ይኖራል። የተሀድሶ ፍጻሜ ውጤቱ ለእግዚአ- ብሔር የተመረጡትን ከአጋንንት የባርነት አገዛዝ ነፃ አውጥቶ ከየአሕጉሩ የማሰባበብ ታላቅ ምስክርነት ነው።

አንዲት ኃይለኛ የተሀድሶ ቤተክርስቲያን በምድር ላይ ስትተከል በአጋንንታዊ የአገዛዝ ክልሎች ላይ አስጨናቂ ተጽእኖ ስለምታመጣ የሉሲፈር ሀሰተኛ የሥልጣን ካባ ተቀድዶ ይወድቅና በሰዎች ሕይወት የፊት መስመር ላይ የተሰለፉት ጭፍሮቹ ሽሽታቸውን ይጀምራሉ (1ኛ ሳሙኤል 17:51)።

> " አምባው ከፍርሃት የተነሣ ያልፋል መሳፍንቱም ከዓላማው የተነሣ ይደነግጣሉ፣ ይላል እሳቱ በጽዮን እቶኑም በኢየሩሳሌም የሆነ እግዚአብሔር" ኢሳያስ 31:9

ለዚህ ሁሉ ቁልፍ አዲስ የመስጠት (Commitment) እሳት በጽዮን፣ የመታዘዝና የተሀድሶ እቶን በቤተክርስቲያን መኖሩ ነው።





## ምዕራፍ 6

# ተሀድሶን ማቀጣጠል ከኢዮስያስ ጠቃሚ መርሆች

የኢዩስያስ አያት በከፋቱ አስገራሚነት ስመጥር የነበረው ንጉሥ ምናሴ ነበር። ከይሁዳ ነገሥታት ምናሴ አስራ አራተኛው ሲሆን ለኃይማኖታዊ ዝቅጠትና በምድር ላይ ፍጹም ለሆነ አጋንንታዊ አሠራር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረገ ነበር (2ኛ ዜና 33:1-9)። ለይሁዳ ታላቅን ተሀድሶ አስገኝቶ የነበረውን የጠላጅ አባቱን የንጉሥ ሕዝቅያስን መንፈሳዊ ትርፎች አፈራረሰ። ምናሴ ለሀሰተኛ አማልክት በምድራቱ ሁሉ መሰዊያን ማዘጋጀት ብቻ ሳይሆን እርሱም ራሱ በጥንቆላ፣ በሞራ ገላጭነትና በመተት ሥራ ዋነኛ ተዋናይ ሆነ። በእርሱ የአስተዳደር ዘመን የከፋትና ሰይጣናዊነት ማንሠራራት ነበር። በሄኖም ልጅ ሸለቆ ውስጥ የገዛ ልጆቹን በእሳት አሳለፈ። ይባስ ብሎም ለጣኦት የተቀረጸ ምስል በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ተከለ፣ የይሁዳንና የኢየሩሳሌምንም ሕዝብ ሕሊና አቆሸሸ።

አስቀድሞ የነበረው የሕዝቅያስ ተሀድሶ ትኩረቱ የእግዚአብሔርን ቤት የማጽዳት ዘመቻ ነበር። የዚህም ነገር ምሳሌነት የሕዝቡን የውስጥ ሕይወትና ሕሊና መጽዳት ይመለከታል። ምናሴ ግን የከፋትን ተመልሶ ማንሠራራት የሚያመለክትን ከዚህ ተጻራሪ የሆነ ነገር በማድረግና መንፈሳዊ አመጽ በመፈጸም የሕብረተሰቡን ጠቅላላ የአምልኮ ሥርዓት አረከሰ። በመጨረሻም የእግዚብሔር ፍርድ አገኘችው። ተጸጽቶም ራሱን አዋረደ። ነገር ግን በምድሪቱ ላይ ከበስተኋላው ትቶት የሄደው የከፋት መዘዝ ተወዳዳሪ ያልተገኘለት ነበር።

በፊንታው ልጁ አሞን ነገሠ። አሞን ወደዙፋን በመጣ ጊዜ የሃያ ሁለት ዓመቾ ወጣት ነበር። እርሱም

የዳዊትን የመግዛት መንፈስና የአሳምሮ በምድር ላይ የምታንጸባርቅ የመጨረሻው ዘመን ቤተክርስቲያን ይገልጣል:: ከእንግዲህ ወዲህ ተዋጊና ታማኝ (የምትታዘዝ) በሆነች ቤተክርስትያኑ በኩል የሚኖረው የክርስቶስ መገለጥ እንጂ ኃይማኖት አሕዛብን ሊስባቸው አይችልም:: ቤተክር- ስቲያን ምልክቱ (ባንዲራው) (በምትሆንበት ወቅት አሕዛብ እርሱን ፈልገው ይመጣሉ (ምልክቱ ባሰበት እርሱ አለ)::

ባንዲራው ወይም ምልክቱ ከፍ ብሎ በሚውለበ- ለብበት ሰዓት "የሕዝቡን ቅሬታ" "ከአራቱም የምድር ማዕዘናት" (ቁ.12) ለማሰባሰብ ከጌታ ዘንድ ትልቅ መነሳሳት ይኖራል:: የተሀድሶ ፍጻሜ ውጤቱ ለእግዚአ- ብሔር የተመረጡትን ከአጋንንት የባርነት አገዛዝ ነፃ አውጥቶ ከየአሕጉሩ የማሰሳበብ ታላቅ ምስክርነት ነው::

አንዲት ኃይለኛ የተሀድሶ ቤተክርስቲያን በምድር ላይ ስትተከል በአጋንንታዊ የአገዛዝ ክልሎች ላይ አስጨናቂ ተጽእኖ ስለምታመጣ የሉሲፈር ሀሰተኛ የሥልጣን ካባ ተቀድዶ ይወድቅና በሰዎች ሕይወት የፊት መስመር ላይ የተሰለፉት ጭፍሮቹ ሽሽታቸውን ይጀምራሉ (1ኛ ሳሙኤል 17:51)::

> " አምባው ከፍርሃት የተነሣ ያልፋል መሳፍንቱም ከዓላማው የተነሣ ይደነግጣሉ፣ ይላል እሳቱ በጽዮን እቶኑም በኢየሩሳሌም የሆነ እግዚአብሔር" ኢሳያስ 31:9

ለዚህ ሁሉ ቁልፍ አዲስ የመስጠት (Commitment) እሳት በጽዮን፣ የመታዘዝና የተሀድሶ እቶን በቤተክርስቲያን መኖሩ ነው::





## ምዕራፍ 6

# ተሀድሶን ማቀጣጠል ከኢዮስያስ ጠቃሚ መርሆች

የኢዩስያስ አያት በከፋቱ አስገራሚነት ስመጥር የነበረው ንጉሥ ምናሴ ነበር:: ከይሁዳ ነገሥታት ምናሴ አስራ አራተኛው ሲሆን ለኃይማኖታዊ ዝቅጠትና በምድር ላይ ፍጹም ለሆነ አጋንንታዊ አሠራር ክፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረገ ነበር (2ኛ ዜና 33:1-9):: ለይሁዳ ታላቅን ተሀድሶ አስገኝቶ የነበረውን የወላጅ አባቱን የንጉሥ ሕዝቅያስን መንፈሳዊ ትርፎች አፈራረሰ:: ምናሴ ለሀሰተኛ አማልክት በምድሪቱ ሁሉ መሰዊያን ማዘጋጀት ብቻ ሳይሆን እርሱም ራሱ በጥንቆላ፣ በሞራ ገላጭነትና በመተት ሥራ ዋነኛ ተዋናይ ሆነ:: በእርሱ የአስተዳደር ዘመን የክፋትና ሰይጣናዊነት ማንሠራራት ነበር:: በሄኖም ልጅ ሸለቆ ውስጥ የገዛ ልጆቹን በእሳት አሳለፈ:: ይባስ ብሎም ለጣኦት የተቀረጸ ምስል በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ተከለ፣ የይሁዳንና የኢየሩሳሌምንም ሕዝብ ሕሊና አቆሸሸ::

አስቀድሞ የነበረው የሕዝቅያስ ተሀድሶ ትኩረቱ የእግዚአብሔርን ቤት የማጽዳት ዘመቻ ነበር:: የዚህም ነገር ምሳሌነት የሕዝቡን የውስጥ ሕይወትና ሕሊና መጽዳት ይመለከታል:: ምናሴ ግን የክፋትን ተመልሶ ማንሠራራት የሚያመለክትን ከዚህ ተጻራሪ የሆነ ነገር በማድረግና መንፈሳዊ አመጽ በመፈጸም የሕብረተሰቡን ጠቅላላ የአምልኮ ሥርዓት አረከሰ:: በመጨረሻም የእግዘብሔር ፍርድ አገኘችው:: ተጸጽቶም ራሱን አዋረደ:: ነገር ግን በምድሪቱ ላይ ከበስተኋላው ትቶት የሄደው የክፋት መዘዝ ተወዳዳሪ ያልተገኘለት ነበር::

በፊንታው ልጁ አሞን ነገሠ:: አሞን ወደዙፋን በመጣ ጊዜ የሃያ ሁለት ዓመት ወጣት ነበር:: እርሱም

በዚያው በተጠናከረው የቤተሰብ ልማድ መሠረት የአባቶቹን አምላክ እግዚአብሔርን ተወ (2ኛ ዜና 33:21-25):: አባቱ አላንጿቸው የነበሩትን ወራዳ ጣኦታት መልሶ በመገንባት ራሱን በእግዚአብሔር ፊት ሊያዋርድ እምቢ አለ:: ለሁለት ዓመት ከነገሠ በኋላ የገዛ አሽከሮቹ በመፈንቅለ መንግሥት ገደሉት:: በዚህ ጊዜ ነበር ኢዮስያስ በይሁዳ ላይ ወደንግሥና የመጣው::

የኢዮስያስን የሥራ ከንውን ታላቅነት ምን ያህል እንደሆነ ለመረዳት እርሱ በነገሠ ጊዜ ሁኔታዎች ምን ይመስሉ እንደነበረ ማወቅ ያስፈልጋል:: በውርስ የቀረለት ለሃምሣ ሰባት ዓመት የዘለቀ የክፉትና እግዚአብሔርን የሚቃወም የአምልኮ ሥርዓት ቅርስ ብቻ ስለነበረ እግዚአብሔርን ያገለግልበትና ደስ ያለኝበት ዘንድ ወይም መንግሥቱን ያስተዳድር ዘንድ ሊከተለው የሚገባ የአሠራር ስልትና ልምድ በቅርብ ሊያገኝ አይችልም ነበር:: በተጨማሪም አሞን ተገድሎ እርሱ ዙፋኑን በተረከበ ጊዜ በዕድሜው ገና የስምንት ዓመት ብላቴና ነበር:: በራሱ ላይ ያነገሠው ሕብረተሰብም ያንኑ የተለመደ የቤተሰብ የአምልኮና የአስተዳደር ሥርዓት አሁንም በኢዮስያስ ዘመን እንዲቀጥል የሚመኝ ነበር:: ባጭሩ በይሁዳ ያለው መንፈሳዊና ሥነምግባራዊ ሕይወት ከምንጊዜውም ይልቅ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ነበር:: ነገሮች ሁሉ በኢዮስያስ ላይ በተቃውሞ ይሠሩ ነበር:: ሆኖም ኢዮስያስ የሰው ልጆች ክፋትና የእግዚአብሔር ትንቢታዊ ፈቃድ በሚለያዩበት መካከለኛ ነጥብ ላይ በመገኘት የተሀድሶ መንፈስ በሕይወቱ ላይ በዝምታ ነገር ግን በኃይል መሥራት ጀምሮ ነበር:: ከመወለዱ በፊት ነብይ ስለእርሱ እንዲህ ተናግሮ ነበር::

> **" በመሰዊያ ላይ መሠዊያ ሆይ፣ መሠዊያ ሆይ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ እነሆ ስሙ ኢዮስያስ የሚባል ልጅ ለዳዊት ቤት ይወለዳል...." 1ኛ ነገሥት 13:2**

ተሀድሶ በማናቸውም ሥርዓት ውስጥ ገብቶ የተደጋገሙ የተጠበቁ ውጤቶችን መለወጥ ይችላል:: የጉልበቱ ምንጭ የእግዚአብሔር ትንቢታዊ ፈቃድና





ፍላጎት እንጂ የሰው ልጆች ምድራዊ፣ ኃጢአተኛና ራስወዳድ ፍላጎት ስላልሆነ በቤተክርስቲያን ተደላድለው ሥፍራ የያዙ የተለምዶ አሠራሮችን ይለውጣል:: ኢዮስያስ ከመወለዱ ሦስት መቶ ዓመታት አስቀድሞ አንድ በስም ያልታወቀ ነብይ ይህንን ተሀድሶ በምድር ላይ የሚያስለቅቁ የትንቢት ቃሎችን ተናገረ:: ቃሉ በትክክለኛነት በጥልቅ ስሜትና በመለኮታዊ ጉልበት ተነገረ:: ከብዙ ዓመት በኋላ አሁን በክፋት መካከል የተወለደና በተነገረለት ትንቢታዊ ቃል የተቀረጸ (Configured) አንድ ሕፃን ለውጥ በሚወለድበትና የሰዎች ፍጻሜ በሚስተካከልበት የታሪክ ወቅት ላይ ቆሞ ተገኘ::

የኢዮስያስ ታሪክ ከእግዚአብሔር የተላከን የአንድ ተሀድሶ የማይገታ ጉልበትና እንቀሳቃሽ ኃይል (momentum) ያሳያናል:: በትክክለኛ መንገድ ምድር ላይ እንዲወለድ የተደረገን አንድን የተሀድሶ ንቅናቄ የሰዎች ልማድ፣ ታሪክ፣ ኃይማኖታዊ ዝቅጠትም ሆነ ማናቸውም ምድራዊ እንቅፋት ሊያስቆመውና ከትክክለኛው ግቡ ሊመልሰው ምንም ዐይነት ኃይል የለውም::

እስቲ እንግዲህ አሁን የኢዮስያስን ተሀድሶ በቅርብ ተመልክተን በዘመኑ ለነበሩት የእግዚአብሔር ሕዝቦች ለውጥ ያስገኙ ጠቃሚ ባህሪዎችን እናጥና::

### ★ *ከገዛ ራሱ የጊዜ ክልል ወጥቶ የሩቅ አባቶቹን የፍጻሜ (destiny) ፈለግ ተከተለ*

> **" ኢዮስያስም መንገስ በጀመረ ጊዜ የስምንት ዓመት ልጅ ነበረ፣ በኢየሩሳሌምም ሰላሳ አንድ ዓመት ነገሰ:: በእግዚአብሔርም ፊት ቅን ነገር አደረገ፣ በአባቱም በዳዊት መንገድ ሄደ፣ ወደቀኝም ወደግራም አላለም::"**
>
> **2ኛ ዜና 34:1-2**

"ቅን" ወይም "መልካም" (right) የተሰኘው ቃል በመጀመሪያው ቋንቋ ትርጉሙ "ቀጥ ያለ፣ የተደላደለ፣

ተስተካክሎ ወደ ላይ የቆመ" ማለት ሲሆን ቃሉ የተገኘበት ምንጩ ነገሮች በመልክ በመልካቸው መደራጀታቸውን የሚያመለክት ቃል ነው። በኢዮስያስ ሕይወት ውስጥ ኃይለኛ የሥነምግባር መርሆች ለለመደራጀታቸው ለማመልከት ነው። እነዚህ መርሆች ተሀድሶ የሚበቅልበትን ተስማሚ መሬት ይወክላሉ። ውስጣቸው የጎበጠና የተጣመመ ሰዎች ፍጹም የሆነውን የእግዚአብሔር ሥርዓት ሊያሳይ የሚችልን ነገር ሊያመነጩ ፈጽመው አይችሉም።

ኢዮስያስ የገዛ ሕይወቱን የለካበትና የእለት ተለት ኑሮውን ያስተካከለበት ብቸኛ ሚዛኑ "የእግዚአብሔር ራት" ነበር። የተሳሳቱ ድምጾችም ሆኑ የተሳሳቱ መሬት በቀል አልፈቀብልሀቶች ከትኩረት አቅጣጫው ሊማርኩት አልቻሉም። ሀሳብ ደላቸውም። ወደ ቀኝም ወደ ግራም አላለም። ሀሳብ ጽኑነትና አልበገሬነት የባህሪው ዋነኛ መታወቂያ እስኪሆኑ ድረስ ራሱን አሳደገ። ሙሉ ትኩረቱን ለመንግሥቱ በነበረው ዓላማ ላይ አደረገ። የቆሸሸ የቤተሰብ ታሪክና ለምች ከእርሱ የሚጠብቁበት ነገር (ሰዎችን እንዴት ደስ ላለኞቸው የሚለው ጥያቄ) ተጽእኖ ሳያሸንፈው እግዚአብሔርን በታማኝነት ሊያገለግለው ቆርጦ ተነሳ። ምንም ሰበብ፣ ምንም ዐይነት ማወላወልና ቸልተኝነት ከቁርጥ ውሳኔው ሊገታው አልቻለም። የዕለት ተለት የሕይወት ምልልሱን ይለካበት የነበረው ብቸኛ ማስተያያው እግዚአብሔር ነበር።

ኢዮስያስ ጥራትን የሚያመዛዝንበት መለኪያ በማጣቱና ስለእግዚአብሔር ዓላማና ፈቃድ ምንነት ከወላጆቹም ሆነ በቅርብ ጊዜ ታሪክ ውስጥ ከነበሩት መንፈሳውያን አባቶች የነገረው ማንም ስላልነበረ ወደሩቅ የታሪክ ዘመን ተጉዞ ይሁዳ ላይ ተቀምጦ ዳዊት እሥራኤልን በእግዚአብሔር ትንቢታዊ ኃይል ይገዛ የነበረበትን ወርቃማ ዘመነመንግሥት እንደሞዴል ማጥናቱን ተያያዘው። የዳዊትን መንፈሳዊ የጉዞ አቅጣጫ እንደራሱ አድርጎ ተቀበለው ዳዊትን ለይሁዳ ነገሥታት ሁሉ ሞዴል እንዲሆን ያስቻሉትን የአእምሮ ዝንባሌዎች (attitudes) እና ጸጋ ወደራሱ መንፈስ በትጋት አንቆረቆረ።





ከገዛ ራሱ ትውልድ ጎደሎነት በመውጣት በሩቅ ያለውን ዳዊትን አባትና መንፈሳዊ መምህሩ፣ ምሳሌውና መነቃቂያው (inspiration) አድርጎ ወሰደው።

የ21ኛው ክፍለ ዘመን የተሀድሶ መርሆችና የአማኞች የወቅቱ አመለካከትና አስተሳሰብ ይህንን የመሰለ ነው። እግዚአብሔር ለዘመናችን ያለውን ፈቃድ በሕይወታችን እንዲገለጥ በማድረግ በኩል እኛን የቀደሙ አባቶች ድክመት እንደሰበብ ሆኖ አለመቻላችንን ሊነግረንና ሊያዳክመን አይገባም። በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱ የእምነትና የድል አባቶች በኩል የተገቡልን ተስፋዎችና እነዚሁ አባቶች ተተውልን የሄዱት የሥነባህሪ ሞዴል ቅርሶች ዛሬም በመንፈሳዊው ዓላም ውስጥ የሚንጸባረቁና በእግዚአብሔር ቃል በኩል እያስተማሩንና እያገለገሉን ያሉ ናቸው። የኢዮስያስን ተሀድሶ ወደፊት ያሽከረከሩ መርሆች እኛንም ያገለግሉ ዘንድ ያኔ ከነበረው እምቅ ጉልበታቸው ጋር ዛሬም ሕያው ሆነው በእጃችን ውስጥ ናቸው።

አንድ ትክክለኛ ተሀድሶ ሊመሠረት የሚገባው በሰዎች ፍላጎት ዙሪያ ሳይሆን በጠንካራ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ ላይ ነው። የተስተካከለ ባህሪ ሊኖረንና በጥንቱ መንፈሳውያን አባቶች መንገድ ልንሄድ ይገባናል። ልንደርስበት መሞከር ያለብን ከመጀመሪያው አንስቶ የነበረውን የእግዚአብሔርን መንፈሳዊ ቴክኖሎጂ ነው። ልናገኘውና ልንመላለስበት የሚገባን የእግዚአብሔርን የመጀመሪያውን አላማና እቅድ ነው።

## *★ ወደ አንድ እግዚአብሔርን የመፈለግ ጠንካራ ረሀብ ውስጥ ይግባል*

**" በነገሰም በስምንተኛው ዓመት ገና ብላቴና ሳለ የአባቱን የዳዊትን አምላክ ይፈልግ ጀመር በአሥራ ሁለተኛውም ዓመት ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን ከኮረብታው መስገጃዎችና ከማምለኪያ ዐጸዶች ከተቀረጹትና ቀልጠው ከተሠሩት ምስሎች ያነጻ ጀመር"**

**2ኛ ዜና 34:3**

ለአራት ዓመታት ኢዮስያስ ሁሉን ነገር ትቶ በአባቱ በዳዊት ምሳሌ እግዚአብሔርን በመፈለግ ሥራ ላይ ተሠማራ:: ይህንን ሲያደርግ በዕድሜው ገና ልጅ ነበር:: ለተሀድሶ ንቅናቄ ዛሬ እጅግ ጠቃሚው መንፈሳዊ መርህ እግዚአብሔርን መፈለግና እግዚአብሔርን መራብ ለዘመነ ተሀድሶ ከሁሉም የበለጠ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ነገር መሆኑን ማወቅ ነው:: የእውነተኛ ተሀድሶ ቀዳሚ ተግባር ቅዱሳንን መልሶ በተቆጣጠረ እግዚአብሔርን የመፈለግና የመጠማት መንፈስ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር እንደገና መጣበቅ ነው::

ዳዊት የእግዚአብሔርን ፊት በመፈለግ ተወዳዳሪ ያልተገኘለት ሰው ነበር::

> " እምላኬ እምላኬ ወደ አንተ እገሰግሳለሁ ነፍሴ አንተን ተጠማች፣ ስጋዬ እንዴት አንተን እንዴት ናፈቀች እንጨትና ውሃ በሌለበት በምድረ በዳ:: ኃይልህን ክብርህን አይ ዘንድ እንዲሁ በመቅደስ ውስጥ ተመለከት-ሁህ" መዝመር (63) : 1-2

ኢዮስያስ ደግሞ የእግዚአብሔርን ኃይልና ክብር ከመቅደሱ አየወጣ ሲፈስስ ለማየት ባለታላቅ ጉጉት በመሆኑ እነዚህን መንፈሳዊ ሞዴሎች ለሕይወቱ ተቀበላቸው::

እግዚአብሔርን መፈለግ ሕብለሰሜታዊ (emotional) ሥራ አይደለም:: ቃሉ ዘረፈ-ብዙ ትርጉም አዝሏል:: ተግቶ ማጥናትን፣ መሞከርን ያካተተ ጠንቃቃ ፍለጋ፣ ተከታትሎ ማግኘትን የሚያጠቃልል ሐሳብ ይዟል:: ይሄም የሰው ሁለንተና ክፍሎች (faculties) ሁሉ ተነቃቅተው ወደ እግዚአብሔር በሚቀረብበት አዲስ መንገድ ላይ እንዲያ-ነጣጥሩ የሚያደርግ ኃይለኛ እንቅስቃሴ ነው:: በእንዲህ ዓይነት የተራዘመ ጥረት ታጅቦ ነበር ወጣቱ ንጉሥ ኢዮስያስ ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን ለማጥራት ወደሚያስ-ችሰው እርግጠኝነትና የዓላማ ጽናት ደረጃ ሊደርስ የቻለው::





## ★ በምድሪቱ ላይ ተንሰራፍቶ በቆየው የኃይማኖተኝነት መንፈስ ላይ ጦርነት ከፈተ

> " የበአሊምንም መሠዊያዎች በፊቱ አፈረሱ፣ በላዩም የነበሩትን የፀሐዩን ምስሎች የማምለኪያ አፀዶች ቆረጠ፣ የተቀረፁትንና ቀልጠው የተሠሩትን ምስሎች ሠባበረ፣ አደቀቃቸውም ይሠውላቸው በነበሩት ሰዎች መቃብርም ላይ በተናቸው የካህናቶቻቸውንም አጥንት በመሠዊያቸው ላይ አቃጠለ:: ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን አነፃ የምናሴንና የኤፍሬምንም የስምዖንና የንፍታሌምንም ከተሞች በዙሪያቸው ያለውን ቦታ እንዲሁ አነፃ"
>
> 2ኛ ዜና 34:4-6

ኢዮስያስ በምድሪቱ ሁሉ ላይ ተመቻችተው በተከፈሱ ሀሰተኛ የኃይማኖት ምሽጎች ላይ ጠንካራና የተራዘመ ዘመቻ ከፈተ:: ይሄም አንድ ሌላ የእውነተኛ ከእግዚአብሔር የመጣ ተሀድሶ ንቅናቄ አስፈላጊ አካል ነው:: ጠላት በእግዚአብሔር ሕዝብ አእምሮ ላይ ካኖራቸው ዋነኛ የማደናገሪያ ስልቶቹ መካከል አንዱ የራስዋን የቤተክርስቲያንን አመሰካከትና አስተሳሰብ በመውረር ሊያጠፋ በቆረጡ ጨካኝ የአጋንንት ስልፎች መካከል የምንመላለስ መሆናችንን ለመረዳት አሻፈረኝ ማለት ነው:: የኃይማኖተኝነት መናፍስት የቤተክርስያንን መንፈሳዊ መዋቅሮች መውረር እንደሚችሉ ማስተዋል ያስፈልጋል::

> " ጠላት በቅዱሳንህ ላይ እንደከፉ መጠን ሁልጊዜም ትዕቢታቸው ላይ እጅህን አንሳ:: ጠላቶችህ በበዓልህ መካከል ተመኩ የማያ-ቁትንም ምልክት ምልክታቸው አደረጉ:: እንደላይኛው መግቢያ ውስጥ፣ በዱር እንዳለም እንጨቶች በመጥረቢያ በሮችዋን ሠበሩ:: እንዲሁ በመጥረቢያና በመዶሻ ሠበሩአት:: መቅደስህን ከእሳት አቃጠሉ፣

**የለምህንም ማደሪያ በምድር ውስጥ አረከሱ፤ አንድ ሆነው በልባቸው በየሕዝባቸው፦ ኑ የእግዚአብሔርን በዓሎች ከምድር እንሻር አሉ፤ ምልክታችንን አናይም ከእንግዲህ ወዲህም ነቢይ የለም፤ እስከመቼ እንዲኖር የሚያውቅ በእኛ ዘንድ የለም"**

**መዝሙር (74):3-9**

ጠላቶች በእግዚአብሔር ቤት መካከል መንፈሳዊ ግዴታ (መፈንቅለ መንግሥት) ለመፈጸም እየሞከሩ ናቸው:: በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ የሚከናወነውን ነገር ሁሉ ለመቆጣጠርና በቤቱ ውስጥ ያለውን እንቅስቃሴ ሁሉ ድብቅ ዓላማቸውን ማስፈጸሚያ አድርገው ሊቀለብሱት (to manipulate) አርማቸውን (ስንደቅ ዓላማቸውን) ለምልክት ከፍ አድርገው ሰቅለዋል:: ሥራቸው ማፍረስና ማቆሸሽ ነው:: ሾልከው መግባት ከተፈቀደላቸው በመቅደስ ውስጥ ያለ የትኛውንም የእግዚአብሔር የመገናኛ ሥፍራ ከማበላሸት አይመለሱም:: ይህ መዘዘኛ የጠላት ጥቃት ከመዝሙረኛው ዘንድ በዚህ የቤተክርስቲያን የፈተና ሰዓት "እውነተኛውን ስንደቅዓላማ ይተከሉልን ዘንድ ነቢያት ወዴት አሉ?" ብሎ የሚያስጮህ የቁጭት ጥሪ ያነሳሳል:: ይህም በመሠረቱ የእግዚአብሔር የተሀድሶ ንቅናቄ እንዲመጣ የተደረገ ጩኸትና ልመና ነው::

ኢዮስያስ በኃይማኖታዊ ዝቅጠት ላይ ያካሄደው ዘመቻ በአንድ የኃይማኖት ተቋምና በሌላው መካከል የተደረገ ፉክክር አልነበረም:: ይሠራ የነበረው በትንቢታዊ ትክክለኛነት ላይ ተመርኩዞ ነበር::

> **" በመሰዊያ ላይ፦ መሠዊያ ሆይ፤ መሠዊያ ሆይ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እነሆ ኢዮስያስ የሚባል ልጅ ለዳዊት ቤት ይወለዳል፤ እጣንም የሚያጥኑብህን የኮረብታ መስገጃዎቹን ካህናት ይሠዋብሃል፤ የሠዎቹንም አጥንት ያቃጥልብሃል ብሎ በእግዚአብሔር ቃል ጮኸ" 1ኛ ነገሥት 13:2**





በሀሰተኝነት ላይ የተካሄደው የማጥፋት ዘመቻ በእግዚአብሔር አፍ አስቀድሞ የተነገረ (Prescribed) እና ለኢዮስያስ ዘመን የተወሰነ ትንቢታዊ ተልእኮ ነበር:: ጭካኔው እውነትን ከመያዝ የሚመነጭ ነበር:: የግልሙትናን ይዞታዎች በ"መጥረቢያ" ይጨፈጭፍ ነበር:: "መጥረቢያ ለማለት ያገለገለው ቃል "ቸረብ" (Chereb) የሚልና "ሰይፍ" ተብሎ ሊተረጎም የሚችል ነው:: ይሄም የእግዚአብሔርን ቃል ጉልበት እንደ እግዚአብሔር ሰይፍነቱ (ዕብራውያን 4:12) ተጠቅሞ በጠላቶች ላይ ፍርድን ስለማምጣት የተነገረ ግልጽ ትንቢታዊ መልእክት ይዟል::

> **" ሠይፌ (ቸርብ) በሰማይ ሆና እስክትረካ ድረስ ጠጥታለች እነሆ በኤዶምያስና በረገምኩት ሕዝብ ለፍርድ ትወርዳለች::"**
>
> **ኢሳያስ 34:5**

## ★ *የእግዚአብሔርን ቤት መልሶ ገነባ*

> **" በነገሰም በአሥራ ስምንተኛው ዓመት ምድሪቱንና የእግዚአብሔርን ቤት ካነፃ በኋላ የኤዜልያስ ልጅ ሳፋን የከተማይቱን አለቃ መዕሴያ ታሪክ ፀሐፊውም የኢዮአካዝ ልጅ ኢዮአክ የእግዚአብሔር የአምላኩን ቤት ይጠግኑ ዘንድ ለደዳቸው::" 2ኛ ዜና 34:8**

> **" የእግዚአብሔር ቤት በሚሰሩት ላይ ለተሾሙት ሰጡ፤ እነሱም ይጠግኑና ያድሱ ዘንድ የእግዚአብሔር ቤት ለሚሰሩ ሠራተኞች ሰጡ" 2ኛ ዜና 34:10**

ኢዮስያስን በተመሰከተ የቤቱ መልሶ ግንባታ እምነት በሚጣልባቸውና የራስ በሆኑ ሰዎች የበላይ ተቆጣጣሪነት መካሄድ እንደነበረበት ግልጽ ነው:: እዚህ ሥፍራ ላይ በስም የተጠቀሱት ሰዎች በሀዤቱ አስተዳደር መዋቅር

ውስጥ ከፍተኛ ቦታ የያዙ ባለሥልጣኖች ብቻ ሳይሆኑ ጠንካራ የንጉሡ ደጋፊዎችና ራዕይ ተካፋዮቹ ናቸው።

ተሀድሶን በመምራት ውስጥ ጠቃሚ ስለሆነው መንፈሳዊ ስልት (Technology) ጥሩ ግንዛቤ እንዲኖረን የሚያደርጉ ሁለት ቃላት በዚህ ምዕራፍ ተጠቅሷል። በመጀመሪያው ጥቅስ ላይ "መጠገን" የሚለው ቃል "ቻዛክ" (Chazaq) ነው። ክፍተት እንዳይኖረው ማድረግ፣ በዓላማው የጸና አድርጎ ማጠንከር፣ የማያወላውል ብርቱና የማይበገር ማድረግ፣ ደፋርና የማይፈራ ማድረግ ሰማስት ያገለግላል። "መጠገን" የሚሰው ይሄው ቃል በሁለተኛው ጥቅስ ውስጥ "ባዳክ" (Badaq) በሚል ቃል ተገልጾ እናገኘለን። ይሄ ደሞ "ቸል ተብለው ለነበሩ" ነገሮች ዳግመኛ ትኩረት ስለመስጠትና ክፍተትን ስለመዝጋት የሚናገር ቃል ነው። የነዚህ ሁለት ቃላት ጥምረት በተሀድሶ ጊዜ የሚኖረውን ኃይለኛ የግንባታ ሂደት አመልካች ነው።

እነዚህ ቃላት አንድ የተሀድሶ ንቅናቄ የሚያስከትላቸውን ዘርፈ ብዙ ተጽእኖዎች የሚያሳዩ ናቸው። በቤተክርስቲያን አሠራር ውስጥ ያሉት ክፍተቶችና ጉድለቶች በሚገባ ይስተካከላሉ። በቤተክርስቲያን በኩል ክርስቶስ በሙሉ ድምቀቱ ለምድር እንዳይገለጥ ትክክለኛ መልኩን የሚበርዙ ቁስሎችና ስብራቶች ሊጠገኑ ይገባል። ቤተክርስቲያን ውስብስብ በሆኑ ችግሮች እጅግ እየተዳከመ ባለ የሰው ዘር መካከል ጥብቅ ትሥሥር ያላት የተዋሀደች የእግዚአብሔርን ግርማዊነትና ገናና ክብር በማንጸባረቅ በኩል ብቻዋን የቆመች ኃይል የመሆንዋ እውነታ በሁሉም ዘንድ መታወቅ አለበት።

በኃይማኖታዊና ሥጋዊ አስተሳሰብ ወረራ ተገድዶ ወደ ደካማነት ወደ መቻቻልና መፈራራት ያዘመመው የቤተክርስቲያን ሥነምግባር በመጽሐፍ ቅዱሳዊ መለኪያዎች እንደገና ተቃኝቶ ወደቀደመ ሐዋሪያዊ ጥንካሬው ሊመለስ ይገባል። በጴንጤቆስጤ ዕለት ቤተክርስቲያን ወደ ምድር በተወለደችበት ዘመን ትታወቅ የነበረችበት ያ ቁርጠኝነት፣ ጥንካሬ ድፍረትና ጉብዝና ወደ ቅዱሳን ልብ





ተመልሶ መግባት አለበት። እነዚህ ነገሮች የተሀድሶ ወሳኝ ገጽታዎች ናቸው።

## ★ መሳውን አካል የሚያስታጥቅ ጸጋ ያካፍላል

> " የእግዚአብሔር ቤት በሚሰሩት ላይ ለተሾሙት ሠጡ፣ እነሱም ይጠግኑና ያድኑ ዘንድ የእግዚአብሔር ቤት ለሚሰሩ ሠራተኞች ሰጡ፣ የይሁዳ ነገሥታት ሳፈረሱት ቤት ሠረገሎች ያደርጉ ዘንድ ለማጋጠሚያም እንጨት የተጠረበውንም ድንጋይ ይገዙ ዘንድ ለአናጢዎችና ለጠራቢዎች ሰጡ"
>
> **2ኛ ዜና 34:10-11**

በዚህ ክፍል የተዘረዘሩት በተለያየ ደረጃ የሚገኙ ሠራተኞች በቤተክርስቲያን ውስጥ ያለውን የተለያየ የአገልግሎት ዘርፍ የሚወክሉ ናቸው። ኢዮስያስ የዚህ ተሀድሶ ፊርቀዳጅ ድምጽ ያከፋፈለው ገንዘብ ደግሞ ሰማያዊ አቅራቦቶችንና የተጠናከሩ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረዳቶችን፣ እንደሞዴል የሚያገለግሉ የሕይወት ዘይቤዎችን፣ ትንቢታዊ ግልጽነትን እና ሐዋርያዊ መገለጥን፣ የተሀድሶን ሂደት በኃይል ወደፊት ሊያስፈንጥሩ የሚችሉን የእግዚአብሔር ትክክለኛ ወራትና ዘመናት ይወክላል። ተሀድሶን የሚያንሳሳ ግፊት መፍሰስ ይጀምራል። በይሁዳ ውስጥ ሲከናወን ሳለው ነገር ሁሉ የእንቅስቃሴው ማዕከል ንጉሡ ነው።

ስራውን በዋናነት ለመስራት የተሾሙት የሚያመለክቱን ፓስተሮችና ሌሎች የቤተክርስቲያን አመራርን ነው። የእነርሱ አገልግሎት በምድሪቱ ዙሪያ ላሉት አጥቢያ የእግዚአብሔር ቤቶች የበላይ አመራር መስጠት ነው። ሠራተኞቹ (የስራው ቀጥተኛ ተሳታፊዎች) የመንግሥቱን ሥራ ለመሥራት ልባቸው የተነሳሳ ቅዱሳን ናቸው። ግንበኞቹና የእጅ ባለሙያዎቹ ደግሞ ድምጻቸው ምድርን እየሞላ ባሉት የተሀድሶ መሪዎች በኩል ወደ የአህጉራቱ እየገባ ወደ ሙሉ ግንዛቤና መገለጥ እየመጣ ያለውን ሐዋርያዊና ትንቢታዊ አቅራቦት ይወክላሉ።

አንድ ተሀድሶ ፍሬያማ እንዲሆን ከተፈለገ የቤተክርስቲያኒቱ የተሰያዩ የአገልግሎት ዘርፎች ብሎም የየአጥቢያው ማህበረ ምዕመናን በዕውቀትና በግንዛቤ መሞላት አለባቸው። የአንድ ተሀድሶ በሳል መግለጫ ከማዶ ወደ እኛ የሚመጣ የአንድ ነብይ ብቸኛ ጩኸት ሳይሆን ወደሚቀጥለው የመንግሥቱ የእድገት ደረጃ አቅጣጫን የሚያስይዝ የመላይቱ ቤተክርስቲያን ሠፊ የአባላት የጋራ እንቅስቃሴ ነው።

ሙሴ ሕዝቡን ወደ አንድ ወደማይታወቅ እውር የወደፊት ዓላማ የሚመራ የሕዝብ አለቃ አልነበረም። የእግዚአብሔርን ያለማቋረጥ ሕግን እየሰጣቸው ነበር። የእግዚአብሔርን ፈቃድና ከሕዝቡ የሚጠበቀውን ምላሽ አስመልክቶ ሳይታክት ያስተምር ነበር። የእግዚአብሔርን ነገሮች ይበልጥ አውቀው ይበልጥ እንዲጠቀሙባቸው የባህሪ ለውጥ ሊያመጣባቸው በተሰያየ መንገድ ያስተምራቸው ነበር። ወደተስፋይቱ ምድር መግባት ምን እንደሆነና እንዴት ሊመላለሱ እንደሚገባቸው ደጋግሞ እየመከረ ወደቀደመው የባርነትና የግዞት ድንቁርናቸው ከማፈግፈግ ተከታታይ ትውልዶችን ለመታደግ ልጆቻቸውንም እንዲያስተምሩ ያስጠነቅቅ ነበር።

የቤቱ "ወሰል" ወደ ሥፍራው መመለስ ነበረበት። ወሰል የሚያመለክተው የቤተክርስቲያንን መንፈሳዊ መሠረቶች ነው። "የይሁዳ ነገሥታት" በመጥፎ አመራራቸውና ትክክለኛነትን በሳተ የመንፈስ ቅዱስ በሚመስል አካሄድ የሕንፃውን ወሰል አፍርሰውት ነበር። በአንድ አቅጣጫ ብቻ የተሞላ አስተሳሰብ፣ ጠባብ የሆነ እምነትና ኋላቀር የሕይወት ዘይቤ ይዘን ወደ 21ኛው ምዕተ ዓመት በመግባት ላይ ነን። በሽሽት ምሽጎች ውስጥ ተጠፍንገን ታስረን የቀደሙትን አባቶቻችንን እስከሞት ድረስ የማያወላውል የሰማዕትነት መንፈስ ጥሰናል። በቤተክርስቲያን ያሉ "ኮከብ" የካርዝማቲክ ትርኢት ተዋንያንን ደማቅ የማዝናናት ሚቶዶሎጂ እያጣጣምን ተቀምጠናል። የቀደሙትን ትንቢታዊ እሴቶችና የመጀመሪያዎቹ የእምነት አባቶች የአዕምሮ ዝንባሌ ከመጣላችን የተነሳ ሁሉን እየሰባበረ የእግዚአብሔርን





መንግሥት ወደፊት የሚያስገሰግሰውን በውስጣችን ያለ ገዢ ጸጋ አጠያያቂ አድርገነዋል።

መንፈሳዊ ጥማትንና መፈለግን እንደገና በማነቃቃት የተጠረበን ድንጋይ ለወሰል፣ ዝግባን ደግሞ ለምሰሶ መግዛት ይኖርብናል። ከመንፈስ ቅዱስ አሁን ለቤተክር-ስትያን በሰጠው የእውነት መገለጥ ይዞታ ላይ በጽናት በመቆምና ለሰራውም ግንባታ በጠነከረ የእውነት አዋጅ በማፋጠን በምድር ላይ እየተገለጠ ባሉ አስጨናቂና አሳሳቢ ችግሮች መካከል ከሚኖር ትውልድ ጋር በአጥጋቢ ሁኔታ መግባባት የሚችሉ አዳዲስና ለችግሩ መፍትሄ የሆኑ አጥቢያ አብያተክርስቲያንን በመንፈስ በመገንባት ሀንጻው ሊታነጽ ይገባል። "ቶሎ ብለን ወደ መንግሥተ ለማያት እናምልጥ!" እንዲህ ዓይነቱ አስተሳሰብ ካሁን ወዲያ በቂ አይደለም።

## ★ የአምልኮን ምንነት እንደገና አሻሽሎ በመተርጎም ከዓላማ ጋር ያቆራኘዋል

"...ከሌዋውያንም ወገን በዜማ ዕቃ አዋቂዎች የነበሩ ሁሉ በተሸካሚዎችና ልዩ ልዩ ሥራ በሚሠሩ ላይ ተሾመው ነበር፤ ፀሐፊዎቹና አለቆቹም በረኞቹም ከሌዋውያን ወገን ነበሩ።"
2ኛ ዜና 34:12-13

ኢዮስያስ በመራው ተሀድሶ አምልኮ ከተራ ሙዚቃዊ ማስተዋወቂያነት ጥርት ወዳለ የገገርነት ከፍታ ተሻግሯል። በግንባታው ሂደትና ሥራውን መርቶ በመቆጣጠር ወቅት ሸክምን ለማቃለል ከሙዚቃ መሣሪያዎቹ ጋር ቀልጣፋ ሙዚቀኞችን መደበ። ይሄም በዛሬው ዘመን ቤተክርስቲያን ያለውን የተሀድሶ ሂደት ለማራመድ ሙዚቃ፣ ዝማሬ፣ አምልኮ ያላቸውን ከመጠን በላይ የሆነ ትንቢታዊ አስፈላጊነት ይገልጣል።

በያንዳንዱ ተሀድሶ ሙዚቃና ዝማሬ ትልቅ ሥፍራ ነበረው። ከሙሴ ውጪ በሆነ አሠራር የእግዚአብሔርን

ድንኳን በጽዮን ሊመሠረት ዳዊት የወሰደው ሥር ነቀል እርምጃ ሃያ አራት ሰዓት ሙሉ በተካሄደ እጅግ የተቀነባበረ ትንቢታዊ ምስጋናና አምልኮ መካከል ነበር የተከናወነው (1ኛ ዜና 25)። በነህምያ ዘመን ደግሞ የግንቡ ሥራ ፍጻሜና የአዲሱ የሰውጥ አራማጅ ሕብረተሰብ ምረቃ በዓል በእግዚአብሔር ፊት የተከናወነው በሁለት ታላላቅ የመዘምራን ቡድኖች (ኳየሮች) ጣዕመ ዜማ ደምቆ ነበር። በግንቡ ላይ ቆመው ከተማይቱን በመከበብ ያሰሙት የዝማሬ ጩኸት የኢየሩሳሌምን ታላቅ ደስታ ከሩቅ እንዲሰማ አድርጎ ነበር (ነህምያ 12:27-43)። በእዝራ ተሀድሶ ጊዜ የቤተመቅደሱ መሠረት ግንባታ በአምቢልታዎች ድምጽና በአሳፍ ልጆች የዝማሬ ቃና የታጀበ ነበር።

እሥራኤል ወደ ጉዞአቸው ፍጻሜ እየተቃረቡ ሳሉ ከዚህ በታች ያለው አስደናቂ ሁኔታ ሲገጥማቸው እናያለን።

> " ከዚያም ወደ ብኤር ተጓዙ፣ ይኸውም እግዚአብሔር ሙሴን ሕዝቡን ሰብስብ ውኃንም እሰጣችኋለሁ ብሎ የተናገረለት ጉድጓድ ነው። በዚያም ጊዜ እሥራኤል ይህን መዝሙር ዘመረ አንተ ምንጭ ሆይ ፍለቅ፣ እናንተ ዘምሩለት፣ በበትረ መንግሥት በበትራቸውም የሕዝብ አዛውንቶች ያጐደጐዱት አለቆችም የቆፈሩት ጉድጓድ"
>
> **ዘኁልቁ 21:16-18**

ሕዝቡ በጉዞአቸው ተስፋ እየቆረጡና ወደፊት ለመቀጠል ያላቸው ተነሳሽነት በምድረበዳ መካከል ከውስጣቸው እየተሟጠጠ ይመጣል። በእግዚአብሔር ላይ ተናግረው የእግዚአብሔርም ፈጣን ፍርድ በእባብ እንዲነደፉ አድርጓቸው ነበር። ብኤር ወደተባለ ሥፍራ ይደርሱና የሚጠጡትን ውሃ ይሰጣቸው ዘንድ እንዲሰባሰቡ እግዚአብሔር ያዝዛቸዋል። ይህ ሥፍራ ለቀሪው ጉዞአቸው የሚጠቅም አዲስን ሕይወት፣ ወደ እግዚአብሔር መመለስን፣ የአእምሮ ተሀድሶንና አንድነትን የተካፈሉበት ጣቢያ ነበር ሊባል ይችላል። ከሕግ ሰጪው ከሙሴ ዘንድ





አዲስ ድንጋጌ ይወጣል። የሕዝብ አዛውንቶችና አለቆች በበትረ መንግሥታቸውና በበትራቸው ደረቁን ምድረበዳ ይቆፍራሉ።

የአንድን ተሀድሶ ጊዜና ሥፍራ ለማመልከት እንዴት ያለ ጠንካራ ምሳሌ ነው። ይህም በክርስቶስ አካል ውስጥ በሚለቀቅ መለኮታዊ ድንጋጌና አዲስ የመንግሥቱ ሥርዓት በኩል ተስፋ አስቆራጩ ምድረበዳ ብርታት ወደሚታደስበት የእፎይታ ሥፍራ ሲለወጥ መቻሉን ያሳያል።

ታዲያ ይሄ ሕይወት ሰጪ መንግሥታዊ እንቅስቃሴ የሚከናወነው በሕዝቡ የአንድነት ዝማሬና አምልኮ መካከል ነው። ሕዝቡ እየዘመሩ ከምተው ሁኔታቸው ላይ ሕይወት እንዲፈስስ ያዝዛሉ።

## ★ የእግዚአብሔርን ቃል ቀዳሚነት እንደገና ያረጋግጣል

> " ወደ እግዚአብሔርም ቤት የቀረበውን ገንዘብ ባመጡ ጊዜ ካህኑ ኬልቅያስም በሙሴ እጅ የተሰጠውን የእግዚአብሔርን ሕግ መጽሐፍ አገኘ። ኬልቅያስም ጸሃፊውን ሳፋንን፣ የሕጉን መፅሐፍ በእግዚአብሔር ቤት አግኝቻለሁ ብሎ ተናገረው። ኬልቅያስም መፅሐፉን ለሳፋን ሰጠው። ሳፋንም መፅሐፉን ወደ ንጉሡ አመጣ ለንጉሡም ባሪያዎችህ የተሰጣቸውን ትዕዛዝ ሁሉ ያደርጋሉ። በእግዚአብሔርም ቤት የተገኘውን ገንዘብ አፈሰሱ። በሥራውም ላይ ለተሾሙትና ለሠራተኞቹ ሰጡ ብሎ አወራለት። ጸሐፊውም ሳፋን ለንጉሡ፣ ካህኑ ኬልቅያስ መፅሐፍ ሰጠኝ ብሎ ነገረው። ሳፋንም በንጉሡ ፊት አነበበው። ንጉሡም የሕጉን ቃል በሰማ ጊዜ ልብሱን ቀደደ።"
>
> **2ኛ ዜና 34:14-19**

## ★ ሕዝቡን በእግዚአብሔር ፊት ወደ አዲስ የቃል ኪዳን ሥፍራ ያመጣል

> " ንጉሡም ላከ የይሁዳንና የኢየሩሳሌምንም ሽማግሌዎች ሁሉ ሰበሰበ። ንጉሡም የይሁዳም ሰዎች ሁሉ በኢየሩሳሌምም የሚኖሩና ካህናቱ፣ ሌዋውያኑም፣ ሕዝብም ሁሉ ከታናሹ ጀምሮ እስከ ታላቁ ድረስ ወደ እግዚአብሔር ቤት ወጡ። በእግዚአብሔር ቤት የተገኘውን የቃል ኪዳኑን መጽሐፍ ቃል ሁሉ በጆሮአቸው አነበበ። ንጉሡም በስፍራው ቆሞ እግዚአብሔርን ተከትሎ እንዲሄድ ትዕዛዙንና ምስክሩን ስርዓቱንም በፍጹም ልብና በፍፁም ነፍሱ እንዲጠብቅ በዚህም መፅሐፍ የተፃፈውን ቃል ኪዳን እንዲያደርግ በእግዚአብሔር ፊት ቃል ኪዳን አደረገ። በኢየሩ ሳሌምና በብንያምም የተገኙትን ሁሉ በእዚህ ነገር አማለ፣ በኢየሩሳሌምም የሚኖሩት የአባቶቻቸው አምላክ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን እንደአዘዘ አደረጉ።"
>
> 2ኛ ዜና 34:29-32

የአንድ ተሀድሶ ብስለት የሚመጣው ቃልኪዳናዊ አቋሞች ከበላይ ሥልጣን ወደ ሕዝቡ መፍሰስና የሁሉንም ልብ አንድ አድርገው ለጋራ ዓላማ ማስተሣሠር ሲጀምሩ ነው። ኢዮስያስ እዚህ ሥፍራ ላይ የተሀድሶውን ሙሉ ለሙሉ የተስጠ አመራርን ይወክላል። ከጥያቄ ከጥርጣሬና ከውስጣዊ ፍጭት (ሙግት) ተላቅቆ ወደ ዋስትናና ከእግዚአብሔር ጋር ተገቢ ሥፍራን ከመያዝ አኳያ እርግጠኝነትን ወደ መቀዳጀት የተሸጋገረን አመራር ይወክላል። እያንዳንዱን የእግዚአብሔር ዓላማና ትዕዛዝ "በፍጹም ልቡና በፍጹም ነፍሱ" ሲጠብቅ በእግዚአብሔር ፊት ቃል ኪዳን አደረገ።

በክርስቶስ አካል ውስጥ አመራር እንዲህ ዓይነቱን ሥፍራ ሲይዝ በፊቃደኝነት የተሞላችውን ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ዓላማ ለመታዘዝ በቃል ኪዳኑ





ውስጥ እስከ ዛሬ ተደርሶ ወዳልታወቀ ከፍታ የሚያመጣ ወደታች ወደሚገኘው አካል ሁሉ የሚፈስ የመንግሥቱ የአገዛዝ ኃይል ይለቀቃል። ንጉሥ ኢዮስያስ ሕዝቡን ሰብስቦ ለእግዚአብሔር ቃል ያላቸውን የማያወላውል ቀጥተኛ አቋማቸውን እንዲያረጋግጡ አደረገ። ምክንያት የለሽ በራስ ደስ መሰኘትና በሁለት ሐሳብ ማነከስ ሁለቱም ተደምስሰው ሰው ሁሉ አንድ አቋም ብቻ በመያዝ የዓላማ ደብዛዛነትና አለመስተካከል በቃልኪዳኑ እውነታ ጥርት ያለ መረዳት ተውጦ ይወገዳል።

የዚህ ሁሉ ድምር ውጤት ሀገሪቱን ዳር እስከዳር ተብትቦ ከያዛት እርግማን ነፃ ማውጣትና ሕዝቡ በኢዮስያስ ዘመን ሁሉ ከቃልኪዳን ይዞታቸው ወደቀኝም ወደግራም እንዳይሉ ያስቻላቸውን የጽናትና የቀጥተኝነት መንፈስና አስተሳሰብ ማካፈል ነበር።

ከአንዲት የተሀድሶ ቤተክርስቲያን የሚመነጩት የመረጋጋት፣ የብስለት፣ የተጠያቂነት የመስጠትና የክብር ምልክቶች በጣም ግልጽ ናቸው። ተሀድሶ እጅግ ወደ ተጣራው በመንፈስ ያለ ይዞታ ከፍ ያደርገናል። በንጉሡና በሕዝቡ መካከል የተፈጠረው የዓላማ አንድነት የእግዚአብሔር መንፈስ ከፍ ያለ ዓላማውንና ፈቃዱን በሀገሪቱ ሁሉ ላይ ሊፈጽም እንደመንደርደሪያ መሬት አገልግሎታል። የእግዚአብሔር ቃል እንደሚገልጠው ይህ ይዞታ እጅግ ግርማዊና ንጉሣዊ ነው።

> " መልካም አረማመድ የሚራመዱ ሦስት ፍጥረቶች አሉ፣ አራተኛውም መልካም አካሄድን ይሄዳል፣ የእንበሳ ደቦል ከእንሰሳ ሁሉ የሚበረታ፣ የማይመለስ፣ እንስሳንም የማይፈራ፣ በእንስቶች መካከል በድፍረት የሚራመድ፣ አውራ ዶሮ፣ መንጋን የሚመራ አውራ ፍየል፣ በሕዝብ ፊት በግልጥ የሚናገር ንጉሥ" ምሣሌ 30:29-31

በሠራዊቱ የታጀበው ንጉሥ ምሳሌነት የሚያሳየን በአመራርና በተከታይ መካከል ያለውን የዓላማ አንድነትና

መግባባት ነው፡፡ ተሀድሶ በአንዲት ፈቃደኛና ተባባሪ ቤተክርስቲያን ላይ መጣጣምን በማምጣት በደረጃው ከፍተኛ የሆነን መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ያቀጣጥላል፡፡

## ★ *መንፈሳዊ እንቅስቃሴን ተደርሶበት ወዳልታወቀ ደረጃ ያሸጋግራል*

" እንደ ንጉሡም እንደ ኢዮስያስ ትዕዛዝ በእግዚአብሔር መሠዊያ ላይ የሚቃጠለውን መስዋዕት ያቀርቡ ዘንድ ፋሲካውንም ያደርጉ ዘንድ የእግዚአብሔር አገልግሎት ሁሉ በዚያ ቀን ተዘጋጀ፡፡ የተገኙትም የእሥራኤል ልጆች በዚያ ቀን ፋሲካውን ሰባት ቀንም የቂጣ በዓልን አደረጉ፡፡" 2ኛ ዜና 35:16-18

የፋሲካ በዓል (Passover Feast) እሥራኤል ከግብጽ ሊወጡ በተዘጋጁበት የዋዜማ ሌሊት በሙሴ የተመሠረተና በእሮጌው (ብሉይ) ኪዳን ውስጥ በሚከሰቱ የተሀድሶ ንቅናቄዎች ውስጥ አዲስ የመንግሥቱ የፊት ለፊት ጉዞ እንደዋነኛ ገጽታ የሚታይ ነበር፡፡ እስቲ እንግዲህ በዛሬው ዘመን ተሀድሶ ውስጥ ቋሚ እውነታዎችን የሚወክሉ ሕያው መርሆችን በዚያ በመጀመሪያው ፋሲካ ውስጥ እንፈልግ፡፡

## ★ *የፋሲካ መርህ አንድ፡- አዲስን ዘመን ማብሰር*

*" ይህ ወር የወሮች መጀመሪያ ይሁናችሁ፣ የዓመቱም መጀመሪያ ወር ይሁናችሁ"*

**ዘፀአት 12:2**

ፋሲካ ስለጊዜና ስለእድሜ ዘመናቸው የሕዝቡን አመለካከት የለወጠ ክስተት ነው፡፡ ከግብጽ በወጡበት ቀን ጠቅላላው የዘመን አቆጣጠራቸው ተለወጠ፡፡ የነፃነታቸው ወር ካሁን ወዲያ የወደፊት ሕይወታቸው ዘመን አቆጣጠር የመጀመሪያ ወር ሊሆን ተወሰነ፡፡ በትውልዳቸው ሁሉ ፋሲካ ካሁን ወዲያ ለዘለዓለም ከአዲስ የአኗኗር ዘይቤ፣





ከአዲስ ፍጻሜ (Destiny) እና አዲስ ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖር የግንኙነት መስመር አጀማመር ጋር የተሳሰረ ጉዳይ ሆኖ ሲታወቅ ነው፡፡ ይህ የፋሲካ መርህ በተሀድሶ እንቅስቃሴዎች ሁሉ የተጠበቀ ነው፡፡ ትክክለኛ ተሀድሶ በምድር ላይ ያላትን ዘመንና ጊዜ አስመልክቶ የቤተክርስቲያንን ዕይታ እንደገና ያስተካክላል፡፡ ተሀድሶ ቤተክርስቲያንና በምድር ላይ እስካሁን የኖረችበትን የአኗኗር ዘዴ ለዘለዓለም በመለወጥ ወደ አዲስ የዓላማ ደረጃዎች በኃይል እንድትገባ እንደመስፈንጠሪያ መደብ (Ground) እና እንደ ካታሊስት ሆኖ ያገለግላል፡፡

## ★ *የፋሲካ መርህ ሁለት፡- የሕዝባዊ ጉዞን (Migration) አስተሳሰብ መመሥረት*

በታላቁ የመጀመሪያው ፋሲካ ምሽት ጠቅላላው እሥራኤላዊ ሕብረተስብ ለአስቸኳይ የጉዞ ጥሪ ታጥቆ እንዲጠባበቅ ታዝዟል፡፡ ሊመጡ ካሉት ልብ የሚያንጠለጥሉ ተከታታይ ክስተቶች ጋር ጊዜን ለመሻማት በችኮላ እንዲበሉ ተነግሯቸዋል፡፡ የተሀድሶ መንፈስና አስተሳሰብ እንግዲህ ይህንን የመሰለ ነበር፡፡ በቅርብ ሰዓታት ውስጥ በምድረ በዳ መካከል ታላቅ ሕዝባዊ ጉዞ ይጀምራሉ፡፡ ጊዜው የእርነትም ከችግሮች ጋር ፊትለፊት የመጋጠምም ጊዜ ነው፡፡ በፈርኦን የባርነት ቀንበር ሥር መራራው የግዞት ዘመን ሊያልፍ ቀርቧል፡፡ ለአባቶች የተገባውን ጣፋጭ ፍፃሜ ለመውረስ ረጅሙ ሰልፍ (March) መጀመሩ ነው፡፡ ከአሮጌው ጎደሎ የሕይወት ይዞታ ትኩስ የሆኑ የሕይወት ፈተናዎችን ተጋፍጦ በማሸነፍ ወደሚገኝ ትንቢታዊ ፍሬያማነት (Accomplishment) መተላለፍ ትክክለኛ ከሆነ የተሀድሶ እንቅስቃሴ መገኘት የሚገባው ውጤት ነው፡፡

ተጭኖባቸው የነበረው የጥድፊያ ስሜት በራስ የመተማመንን መዘናጋት አፍርሶታል፡፡ ወደ አንድ ፍጻሜ ያነጣጠረና ለጉዞ የተዘጋጀ ሕዝብ ነው፡፡ ለሚመጡ መልካም ነገሮች ያለን ጉጉት አሁን የተቀመጥንበትን ሥፍራ ካላስጠላን ከአንድ መንፈሳዊ ይዞታ ወደ ሌላው ልንሸጋገር የተዘጋጀን አይደለንም፡፡ የፋሲካው ሥርዓት

የሩቅ አባቶቹ ተከትለዋቸው ስለነበሩ የጥራት (Excellence) ስልቶች የሚነግረውን መረጃ አግኝቶ ነበር:: ለዚያ ጊዜ ከነበረው የራሱ ዘመናዊነት ጋር የጥንቶቹን የተሀድሶ መንፈስ ሊያገናኝ ችሎ ነበር:: ከሳሙኤል ዘመን አንስቶ እስከ ኢዮስያስ እንደዚያ ያለ የፋሲካ አከባበር ተሰምቶ አያውቅም ነበር::

እንደ እውነቱ ከሆነ ሳሙኤል ፋሲካን ስለማክበሩ መጽሐፍ ቅዱስ ቀጥተኛ ማስረጃ አይሰጠንም:: ነገር ግን ሳሙኤል እሥራኤልን በመንፈሳዊ ሙስና ከተዘፈቀው የኤሊ ዝብርቅርቅና የተሳሳተ አመራር አውጥቶ ወደ ተሻለ ሥፍራ ባመጣበት መንፈሳዊ ትክክለኝነት ውስጥ እግዚአብሔር የፋሲካን በዓል ኃይልና ብርታት ተመልክቶ ነበር:: የሳሙኤል የተነቃቃ ትንቢታዊ አመራር እሥራ-ኤልን ከዘመነ መሳፍንት ወደ ዘመነ ነገሥታት ያሸጋገረ ድልድይ ከዘረጋበት ጊዜ ወዲያ እስከ ኢዮስያስ ያንን የሚመስል ታላቅ ኃይል የታየበት የሽግግር ወቅት መሪ አልተነሳም::

ኢዮስያስ ቀድመውት የነበሩትን ነገሥታት ሁሉ በለጣቸው:: እሥራኤልን መጠነ-ሠፊ ወደ ሆነ የተትረፈረፈ የመስዋዕት አቀራረብ ደረጃ ከማምጣቱ በተጨማሪ ለእግዚአብሔር ስለሚቀርቡ መስዋዕቶች ተገቢ የማስተያያ ሚዛኖችን (Standards) ለተከታታይ ትውልዶች ሁሉ ደነገገ:: ተሀድሶ የመንፈሳዊ ስጦታ አቀራረቦችን ጥራት ወደ አዲስ ደረጃ በማሻገር ከእግዚአብሔር ጋር ለሚኖር የመቀባበል ግንኙነት አዲስ ሥርዓት ያበጃል::

ብኢዮስያስ መርህ ላይ ተመሥርተን ይህንን የእኛን ትውልድ አዲስ ወደ ሆነ የእምነት፣ የእግዚአብሔር ዓላማ መገለጦች፣ የትንቢታዊ ትክክለኝነት፣ የሐዋርያዊ ብርታትና የግል መሰጠት ድንበሮች ልናደርሰው ይገባናል:: ቀድመውን የነበሩ ነገሥታትን አልፈን በመሄድ ዓለምና የጨለማው ግዛት ካሁን በፊት አይተውት ያላወቁትን ዐይነት በጥራቱ ተወዳዳሪ የሌለው የዓላማ ትውልድ ማፍራት አለብን:: የአባቶችን የጥንት እውነት ለዘመናችን በመቅሰም ለእግዚአብሔር ዙፋን ታላቅን ክብር ማስገኘት አለብን::





## ምዕራፍ 7

# የተሀድሶ ኃይል
# ችግሩን መፍታት፣ አሕዛብን መባረክ

በመጽሐፈ አሞጽ በትንቢታዊ መልኩ ይሄንን የእኛን ዘመን ተሀድሶ የሚያንጸባርቁ ሁኔታዎች ተዘርዝ-ረዋል:: የተትረፈረፈ የኢኮኖሚ ብልጽግና የሚታይበት ነገር ግን ማሕበራዊና ሞራላዊ መበስበስ የወረሰው ዘመን:: የምድር መንቀጥቀጥ ከመምጣቱ ሁለት ዓመታት አስቀድሞ እግዚአብሔር አሞጽን ለአሕዛብ ለይሁዳና ለእሥራኤል መልእክተኛ እንዲሆነው ይጠራዋል (አሞፅ 1:1):: ጥፋት በላያቸው ላይ አንዣብቧል፣ የሕዝቡ ልብ ግን በእግዚአብሔር ላይ አምጿል:: ለተሀድሶ የበሰለ ምቹ ጊዜ ነው:: ትንቢታዊ ድምጹን በማስተጋባት ላይ እያለ በሕዝቦች ውስጠኛ ባህሪና ነፍስ ላይ ፍተሻ (inventory) በማድረግ በምድር ያለውን ነባራዊ ጉድለትና ድክመት ገሀድ አውጥቶ በማሳየት ላይ ነበር::

## የችግሩ ተፈጥሮአዊ ምንነት

ፍተሻው የተካሄደው በታላቅ ኃይልና የብርታት ሁሉ የመጨረሻ ልክ ከሚታይበት ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው::

> "እንዲህም አለ:- እግዚአብሔር በጽዮን ድምጹን ከፍ አድርጐ ይጮሀል፣ በኢየሩሳሌም ሆኖ ቃሉን ይሰጣል፣ የእረኞችም ማሰማሪያዎች ያለቅሳሉ፣ የቀርሜሎስም ራስ ይደርቃል::"
>
> **እሞጽ 1:2**

አሕዛብ በጌታ ተመርምረው ሁሉም የመረረ ጉድለት ተገኝቶባቸዋል::

*★ ደማስቆ በጎረቤቶችም ላይ ስለፈጸመችው ጭቆናና ተገቢ ያልሆነ አገዛዝ ሊፈረድባት ነው*

" እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ ገለዓድን በብረት መንከራኩር አሂዷልና...በአዛሔል ቤት እሳትን እሰዳለሁ፣ የወልደ አዴርንም አዳራሾች ትበላለች" አሞጽ 1:3-4

*★ ጋዛ ሰዎችን በገንዘብ ገዝታ ለኤዶም በባርነት ሸጣለችና ትወድማለች*

". እግዚአብሔር እንዲህ ይላል:- ለኤዶምያስ አሳልፈው ይሰጧቸው ዘንድ ምርኮኞችን ሁሉ ማርከዋልና ስለ ሦስት ወይም ስለ አራት የጋዛ ኃጢዓት መቅሰፍቴን ከማድረግ አልመለስም" አሞጽ 1:6

*★ ጢሮስ የወንድማማችነትን ቃልኪዳን በማፍረስ የገዛ ሥጋ ዘመዶችዋን እንደሸቀጥ ነግዳለችና በእሳት ትበላለች*

" እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ ምርኮኞችን ሁሉ ለኤዶምያስ አሳልፈው ሆጥተዋልና የወንድሞችንም ቃል ኪዳን አላሠቡምና ስለ ሦስት ወይም ስለ አራት የጢሮስ ኃጢዓት መቅሰፍቴን ከማድረግ አልመለስም::"

አሞጽ 1:9

*★ ኤዶም በኃበኛ ጦርነት "ዘር ማጽዳት" (Ethnic Cleansing) በሚለት ፈሊጥ ወንድሙን ጨፍጭፎአልና የእግዚአብሔር ፍርድ ይጠብቀዋል*

" እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ ወንድሙን በሰይፍ አሳድዶታልና ርኅራኄንም ሁሉ ጥሏልና ቁጣውም ሁል ጊዜ ቀድዶአልና





መዓቱንም ለዘላለም ጠብቋልና ስለ ሦስት ወይም ስለ አራት የኤዶምያስ ኃጢአት መቅሰፍቴን ከማድረግ አልመለስም::"

አሞጽ 1:11

*★ አሞናውያን በፓለቲካዊ ድንበርን የማስፋፋት ፖሊሲ ተወጥረው እግረ መንገዳቸውን ምንም ያላጠፉ ሰላማዊ ሰዎችን ጨፍጭፈዋል*

" እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ ዳርቻቸውን ያሰፉ ዘንድ የገለዓድን እርጉዞች ቀድደዋልና ስለ ሦስት ወይም ስለ አራት የአሞን ልጆች ኃጢዓት መቅሰፍቴን ከማድረግ አልመለ-ሰም::" አሞጽ 1:13

*★ ሞአብ ለገዛ ንጉሥዋ ተገቢ የቀብር ክብር በመንሳት አጥንቱን በማቃጠልዋ ምድሪቱን በሙሉ አዋርዳለች*

" እግዚአብሔር እንዲህ ይላል:- የኤዶሚያስን ንጉሥ አጥንት አመድ እስኪሆን ድረስ አቃጥለውታልና ስለ ሦስት ወይም ስለ አራት የሞዓብ ኃጢአት መቅሰፍቴን ከማድረግ አልመለሰም:: " አሞጽ 2:1

ግምገማው ይቀጥልና ይሁዳንና እሥራኤልንም እንኳ እግዚአብሔርን ከማያውቁ ጣኦት አምላኪ አሕዛብ ጋር በጥፋተኝነት ይፈርጃል:: የወንጀላቸው ዝርዝር ሠፊ ነው::

- የእግዚአብሔርን ሕግ ንቀዋል
- ሐሰተኝነታቸው ለክፉ አጋልጧቸዋል
- ጻድቃንን ለብር (Silver) ሸጠዋል
- ለምድሪቱ አፈር አለክልከዋል
- የትሁታንን መንገድ አጣምመዋል
- በየመሰዊያው ፊት ዝሙት ፈጽመዋል

- በሀሰተኛ አምላካቸው ቤት በመቀጫ የተወሰደውን የወይን ጠጅ ጠጥተዋል (አሞጽ 2:4-8)

የሁኔታውን አሳዛኝነት የባሰ የሚያደርገው እግዚብሔር በራሱ ሕዝብና በአሕዛብ መካከል ምንም ዐይነት ልዩነት ሊያገኝ አለመቻሉ ነው:: በዙሪያው ካሉ አሕዛብ ጋራ የነበረው የዓላማና የባህል መዳቀል ለእግዚአብሔር ሕዝብ የነበረውን የጥራት መለኪያ (Standard) ፈጽመው እንዳያሟሉ እንቅፋት ነበር:: ከዚህም የተነሳ በእግዚአብሔር ፊት የነበራቸውን ሞገስ በማጣት እንደማናቸውም አሕዛብ ራሳቸውን ከእግዘብሔር ፍርድ ሥር አገኙት::

## የተደባለቀችው ቤተክርስቲያን ተዘናግቶ መቀመጥ

በይሁዳና በእሥራኤል ያየነው ሁኔታ ትክክለኛ ሥፍራዋ አጠያያቂ (Compromised) በሆነው የዛሬይቱ ቤተክርስቲያን ያለውን የተዘበራረቀና የፈራረሰ መንፈሳዊ ሁኔታ አመልካች ነው:: ከእግዘብሔር ዘንድ የሆነ ተሀድሶ በሚገለጥበት ዋዜማ ላይ የሚታዩ ሁኔታዎች ይህንን ይመስላሉ:: መሪር የሆነ የመንፈሳዊ ኃይል እጥረትና የአገልግሎት ክብር መራቆት አለ::

> **"እነሆ ነዶ የተሞላች ሠረገላ እንደምትደቀድቅ እንዲሁ አደቀድቃችኋለሁ:: ከርዋጪም ሽሽት ይጠፋል ብርቱውም በብርታቱ አይበረታም፣ ኃያሉም ነፍሱን አያድንም፣ ቀስተኛውም አይቆምም ፈጣኑም አይድንም፣ ፈረሰኛውም ነፍሱን አያድንም በኃያላኑም መካከል ልበ ሙሉው በዚያ ቀን እራቁቱን ይሸሻል ይላል እግዚአብሔር" አሞጽ 2:13-16**

ቤተክርስቲያን መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ማካሄድዋን ተወች ማለት አይደለም:: ውጫዊውን የአምልኮ አቀራረብ ሥርዓት በአጥጋቢ ሁኔታ የሚያንጸባርቅ ትልቅ እንቅስቃሴ





አለ:: ይሄ እንቅስቃሴ ግን የዕውነትን ውስጣዊ ኃይልና ፍትሐዊነት ማሳየት ስለማይችል በእግዚአብሔር የተናቀ ነው::

> **" ዓመት በዓላችሁን ጠልቼዋለሁ፣ ተፀይፌውምአለሁ የተቀደሰ ጉባዔአችሁም ደስ አያሰኘኝም:: የሚቃጠለውን መስዋዕታችሁንና የእህሉን ቁርባናችሁን ብታቀርቡልኝም እንኳን አልቀበለውም:: ለምስጋና መስዋዕት የምታቀርቡልኝን የሰቡት እንስሶች አልመኘም የዝማሬህንም ጩኸት ከእኔ ዘንድ አርቅ የመሰንቆህንም ዜማ አላዳምጥም ነገር ግን ፍርድ እንደውሃ ፅድቅም እንደማይደርቅ ፈሳሽ ይፍሰስ::" አሞጽ 5:21-24**

ከሚገባው በላይ በራስ መኩራራት (Complacency) በአሕዛብ መካከል ያለችውን ቤተክርስቲያን ውስጣዊ ጥንካሬ ሸርሽሮታል:: በሥጋ ብርታት እንጂ በመንፈስ ቅዱስ ባለመደገፍ የጽዮን ሕዝቦች ተዝናንተውና ተዘናግተው ተቀምጠዋል:: የእግዚአብሔር ፍርድ ስለመቅረቡ ማሰብን ለነገ ብለውታል፣ ራስን በሚያዝናና ለሥጋና ነፍስ ደስ በሚል ምስጋና ተሠማርተዋል፣ በቤተክርስቲያን በታላቅ ጭንቀት ወስጥ ላሉት "የዮሴፍ" ሕዝቦች ከልባቸው ባለማዘን አምልኮን ወደ መዝናናት ለውጠውታል:: በድግስ ገበታ ላይ ተዝናንተው ተቀምጠው የተሀድሶን አስቸኳይነት ዘንግተውታል::

> **" በፅዮን ላሉ አለመኞች በሰማርያም ተራራ ተዘልለው ለተቀመጡ የእሥራኤልም ቤት ወደ እነእርሱ ለመጡባቸው ለአሕዛብ አለቆች ወዮላችሁ ክፋውን ቀን ከእናንተ ለምታርቁ የግፍንም ወንበር ለምታቀርቡ ከዝሆን ጥርስ በተለራ አልጋ ላይ ለምትተኙ በምንጣፋችሁም ላይ ተደላድላችሁ ለምትቀመጡ፣ ከበጐችም መንጋ ጠቦትን ከጋጣም ውስጥ ጥጃን ለምትስቡ በመሰንቆም ቃምፅ ለምትንጫጩ እንደ ዳዊትም የዜማን እቃ ለምታዘጋጁ በፋጋ**

**ወደ አፍንጫችሁ እወጣለሁ:: እናንተ ግን ወደ እኔ አልተመለሳችሁም ይላል እግዚአብሔር"**

**አሞጽ 4:10**

ጎልማሶች በለይፍ እየወደቁ ናቸው:- ለውጤታማ አገልግሎት የማይሆን የታመቀ ጉልበት ከቤተክርስቲያን ተጠርጎ እየወደመ ነው:: የተቀቡ የእግዚአብሔር ሰዎች ረጅም ቀሚስ (Gown) እና ረጅም ቆብ (Mitre) ወደመልበስ እስኪያፈገፍጉ ድረስ በቤተክርስቲያን ውስጥ ያለው ብልሽት (Corruption) በሠፈር (Camp) እንዳለ ግማት ወደአፍንጫ ሁሉ ደርሷል:: "የመንግሥተስማያት ቁልፎች "እና የእረኞች" ዘንግ ብለው የሚጠሩአቸውን ነገሮችና ከናስ የተሠሩ ሰይፎች በእጃቸው ይዘው በመመሳሰስ ቀለበቶችን መሳለም የመሳሰሉ ልምምዶች ይከተላሉ:: መንፈሳዊ ሥልጣንን ከአልባሳት ጋር የማገናኘትና ለአገልግሎታቸው ዐይነት የሆነውን መጠሪያ ሹመት እንዳለበት የማዕረግ ስም የመቁጠር ባህሪም ይስተዋልባቸዋል:: ክርስትናን አጠያያቂ በሚያደርገው በዚህ ሁኔታ ውስጥ የምትገኝ ቤተክርስቲያን ይህንን በመሳለሰ ቸነፈሮች ተወርራለች:: ተሀድሶ እንዲመጣ ወደ ጌታ የተደረገ ጩኸት ግን የለም::

ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣው ጥሪ ግን "እኔን ፈልጉ በሕይወትም ትኖራላችሁ" የሚል ነው (አሞጽ 5:4-6):: ተሀድሶ ሕዝቦችን ከተበላሸ የእምልኮ ሥርዓት ነፃ አውጥቶ ትኩረታቸውን እንደገና ወደ እግዚአብሔር ይመልሳል:: እግዚአብሔር በሕዝቡ ሠፈር መለኪያዎቹን እየመሠረተ ባለበት አሠራሩ መካከል በእሥራኤል ላይ ይገለጣል:: "ቱንቢውን ይዞ በቱንቢ በተሠራ ቅጥር ላይ ቆሞ" ይታያል (አሞጽ 7:7):: ለእሥራኤል ቤት እንደ ማስመሪያና እንደ ቱንቢ ቀጥ ያሉ የጥራት መለኪያዎች ያስፈልጋሉ፣ እግዚአብሔርም ነገሮችን ወደ (ትክክለኛ) መለኮታዊ ሥርአት ሊመልሳቸው ይፈልጋል:: ለዘመኑ ፍጻሜ ያሰበውንም ቤቱን ከመፍረሱ በፊት ወደነበረበት መልኩ የመመለስ ማስተር ፕላን እየገለጠ ነው:: ከሰማይ እየመጣ ያለውም ትዕዛዝ "እሥራኤል ሆይ... አምላክህን ለመገናኘት ተዘጋጅ" የሚል ነው (አሞጽ 4:12)::





## የዳዊት ድንኳን ተመልሶ መተከል

**" በዚያ ቀን የተወደቀችውን የዳዊትን ድንኳን እነሣለሁ የተናደውንም ቅጥርዋን እጠግናለሁ፣ የፈረሰውንም አድሳለሁ፣ እንደ ቀድሞውም ዘመን እሠራታለሁ፣ ይኸውም የኤዶምያስን ቅሬታ ስሜም የተጠራባቸውን አሕዛብ ሁሉ ይወርሱ ዘንድ ነው:: ይላል ይህን የሚያደርግ እግዚአብሔር"**

**አሞጽ 9:11-12**

የዳዊትን ድንኳን መልሶ መትከል ማለት ቤተክርስ-ቲያንን በኃይል ለመሙላት እግዚአብሔር ያለበው የዘመን ፍጻሜ ዓላማው ነው:: በዚህ ድርጊቱ ያልተስተካከሉ የተዛቡ ነገሮችን ያስተካክላል፣ ቤተክርስቲያንን በትኩስ ኃይል ሞልቶ ድንበሮችን እስከ አሕዛብ ዳርቻዎች ልታለፋ ያቀጣጥላታል::

የዳዊትን ድንኳን እንደገና መልሶ በመትከል ሥራ ውስጥ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ብዙ ነገሮች አሉ:: "እነሳለሁ" የሚለው ቃል በዕብራይስጥ "ኩውን" ይባላል:: ኃይልን ተሞልቶ መነሳት፣ ንቁና ኃይለኛ ሆኖ በአውደ-ውጊያው ላይ መገለጥ፣ በሥፍራ መጽናት፣ ዋጋ ያለውና አስተማማኝ ሆኖ ያለመናወጥ መቆም የሚሉ ሐሳቦችን ያካትታል፣ ደብዝዞና ተዳክሞ የተገኘን የቀደመ ውጤታማነት ወደ ሥፍራው ወደ ብርታቱ መመለስን ያመለክታል:: ስለዚህ የድንኳኑ ጽንሰ ሐሳብ አንድ ቀድሞ የነበረ የቤተክርስቲያን ብርቱ ገጽታዋ አሁን ተመልሶ እየመጣባት ስለመሆኑ ጠቋሚ ነው:: ተመሳስሎና ተሰላልሶ በመኖር፣ በቸልተኝነትና በኃይማኖተኛ የድንቁርና ወራትዋ ምክንያት ሕዝቦችዋ ከተለከፉበት የሽባነት ወረርሽኝ ነፃ ወጥታ እስካሁን መሥራት ያቃታትን ትልቅ የመንግሥቱ ሥራ በብቃት ለማከናወን ኃይልን ስለመቀበልዋ የሚናገር ሐሳብ ይዟል::

ድንኳኑን መልሶ ስለመገንባት እግዚአብሔር በአሞጽ በኩል በአጽኖት መናገሩ በጣም ጠቃሚ የነበረን አንድ

ጠንካራ ነገር ከጥቅም ውጪ ሊያደርጉ የቻሉ ኃይሎች መኖራቸውን ያመለክታል። መልሶ የመትከሉ ሥራ በመንፈሳዊ ተቃውሞ መካከል የሚካሄድ ቢሆንም ክፍተቱ ግን ፈጥኖ ይደፈናል። አንድነታቸው ፈርሶ የተለያዩ የቤተክርስቲያን ነገሮች ሁሉ በዚህ ጊዜ ተመልሰው ይጠገናሉ። የፈራረሱ አስተሳሰቦች የሚፈወሱበትና የተዛቡ አመለካከቶች የሚቃኑበት ጊዜ ይሆናል። በመጨረሻው የተሀድሶ ዘመን ድንኳኑ በቤተክርስቲያን ተመልሶ ተገነባ ወይም ቆመ ማለት በረጅም የሰይጣን ወረራና የማበላሸት ዘመቻ ዓመታት ውስጥ ተበታትነውና ከጥቅም ውጪ ተደርገው የቆዩ የእግዚአብሔር ዓላማና መርሀ ግብሮችን ወደ ቀደመ መልክና ይዞታቸው መልሶ ለማስተካከል መንፈስ ቅዱስ የጀመረው ትልቅ እንቅስቃሴ ነው።

የተሰጠው የሥራ ኃላፊነትና ሥልጣን "እንደቀ-ደመው ዘመን" መልሶ ማቋቋም ነው። ድንኳኑን መልሶ የመገንባት ሥራ ጥልቅና ሠፊ የሆነውን የጥንቱን መረዳት በእኛ ዘመን ወዳለው ዘመናዊና ግዴለሽ አስተሳሰብና አመለካከት ሰብሮ ማስገባት ያስችላል። የጥንቱን መንፈሳዊ ይዞታ መልሰን መቆጣጠር ብቻ ሳይሆን ከዚያም ወደበለጠ የጥራት ደረጃ አልፈን እየሄድን ነን። የመልሶ ግንባታው አጣዳፊ ዓላማና ተፈላጊ የፍጻሜ ውጤት አሕዛብን መጠቅለል ነው።

በዳዊት የተገነባው የመጀመሪያው ድንኳን ይህን የመሰለ ትኩረት አልነበረውም። የእርሱ ዓላማ ሕዝቦች እግዚአብሔርን ለማምለክ የሚገናኙበትን ሥፍራ ማዘጋጀት ብቻ ነበር። በሙሴ ሥርዓት ውስጥ ሆኖ የሙሴን ጠባብ የሕግ መገለጥ የሚበልጥ ገጽታን ሲያንጸባርቅ ዳዊት በግንባታው ሥርነቀል ወደሆነ የመገለጥ ደረጃ ገብቶ ነበር። ሕጉን አልተላለፈም፤ ከሕጉ የላቀና የተሻለ ነገርን አደረገ እንጂ። አሞጽ በትንቢቱ እፊታችን ላይ እየፈታታ ያለው ነገር ደግሞ ዳዊት እንኳ ሊደርስበት ያልቻለ የመጨረሻው የእግዚአብሔር ነገሮች መረዳት ደረጃ ነው።

ይህንን ቴክኖሎጂ ዳዊት ራሱ ሊገነዘብ ይችል ከነበረው ወደ በለጠ ደረጃ እያመጣነው እንገኛለን። በዳዊት





ዘመን እንኳ ሊታወቅ ያልቻለ ይሄ ያሁኑ ተሀድሶ እስከተገለጠበት ዘመን ድረስ ያለሥራ ተኝቶ የኖረ ገና የመጀመሪያው ድንኳን በእግዚአብሔር መንፈስ አነሳሽነትና አመራር በታነጸበት ቀን የድንኳኑ አካል ሆኖ በውስጡ የተደበቀ እውነት ነው። አዲስ የዳዊት ኃይል በሚገለጥበት በእኛ ዘመን፤ እነዚህ የቀደሙ መንፈሳዊ አሠራሮች ጠረማምሰን በማለፍ ከነርሱ እጅግ ወደ በለጡ የመንፈሳዊ ቴክኖሎጂ መገለጦችና ትግበራዎች እየገባን ነን። መንግሥቱን በትክክል የመግለጥና የማቅረብ ሥራ ከጥንታዊነቱ የተነሳ ጠቃሚነት ያለውን የከረመ ነገርና ከአሠራር መገለጡ ትኩስነት የተነሳ ጠቃሚ የሆነውን አዲስ ነገር አዋህዶ መሥራትን ይጠይቃል።

> " እርሱም ስለዚህ የመንግሥተ ለማያት
> ደቀመዝሙር የሆነ ፃፊ ሁሉ ከመዝገቡ
> አዲሱንና አሮጌውን የሚያወጣ ባለቤትን
> ይመስላል አላቸው።" ማቴዎስ **13:52**

ይህንን ተሀድሶ እንቅፋቶችን የሚለባብር የመንፈስ ቅዱስ የወደፊት ግስጋሴ የሚያደርገው የድንኳኑን ምስጢር በመገላለጥ ላይ ላለን በዘመናዊው ትንቢታዊና ሐዋርያዊ ጥርመስ ውስጥ ያሉ የጥንት እሴቶችና መለኪያዎች ይፋ መውጣት ነው።

ስለዚህ የዳዊት ድንኳንና በውስጡ ያለው የቃል ኪዳን ታቦት ወደ ተሀድሶ ለሚያደረግ ኃይለኛ ግስጋሴ ጠንካራ ምልክት ነው። በዳዊት ዘመን እንደነበረው ዛሬም አንድን ሙሉ ሕብረተሰብ ለመለወጥና የሰውን የአስተሳሰብ ችሎታ ለዘመኑ ወደሚገባ በጣም የተሻሻለ ደረጃ ከፍ የማድረግን ሠፊ የመንፈስ ቅዱስ ቴክኖሎጂ ይወክላል። በዳዊት ጊዜ ተራ ሰዎች እንኳ በአሮን ሥርአት የነበሩ ካህናት ተለማምደው ወዳላወቁት የመንፈሳዊ መርሀ አጠቃቀም ውስጥ ገብተው ነበር። በዚህም በእኛ ዘመን በቤተክርስቲያን ያሉ ብዙ ወገኖችን ወደ ድንኳኑ ልምምድ በማምጣት ሥራ ብንበረታ ሰዎች ከዚህ ቀደም ታይተው ወዳልታወቁ የመንፈሳዊ ችሎታና ለእግዚአብሔር ፈቃድ ምቹ የመሆን ደረጃዎች ከፍ ይላሉ።

ዳዊት በዘመኑ እሥራኤልን ወደ ተሀድሶ ከፍታዎች ለማምጣት የተጠቀመባቸውን አንዳንድ መርሆች እስቲ ከዚህ በታች እንመልከት። እነዚህ መርሆች የዳዊትን የተሀድሶ ንቅናቄ ጉልበት በዘመናችን በሥራ ለመተርጎም ጠንካራ መሠረት ይሆኑልናል።

## የድንኳኑ አራት መርሆች

### ★ የድንኳኑ መርህ ቁጥር አንድ፦

**በእሥራኤል ሁሉ አዲስ የንጉሥ መገኘት ከተመሠረተ በኋላ ታቦቱ እንዲመጣ ተደረገ**

**" እሥራኤልም ሁሉ በኬብሮን ወደ ዳዊት ተሰብስበው፣ እነሆ እኛ የአጥንትህ ፍላጭ የሥጋህ ቁራጭ ነን። አስቀድሞ ሳኦል ንጉሥ ሆኖ ሳለ እሥራኤልን የምታወጣና የምታገባ አንተ ነበርህ፣ አምላክህ እግዚአብሔርም ሕዝቤን እሥራኤልን አንተ ትጠብቃለህ፣ በሕዝቤም በእሥራኤል ላይ አለቃ ትሆናለህ፣ ብሎህ ነበር አሉት፣ የእሥራኤልም ሽማግሌዎች ሁሉ ወደ ንጉሡ ወደ ኬብሮን መጡ ዳዊትም በኬብሮን በእግዚአብሔር ፊት ቃል ኪዳን ከእነርሱ ጋር አደረገ በሳሙኤልም እጅ እንደተናገረው እንደ እግዚአብሔር ቃል በእሥራኤል ላይ ንጉሥ ይሆን ዘንድ ዳዊትን ቀቡት" 1ኛ ዜና 11:1-3**

**" እነዚህ ሁሉ ዳዊትን በእሥራኤል ሁሉ ላይ ያነግሡት ዘንድ አርበኞችና ሰልፈኞች እየሆኑ በፍጹም ልባቸው ወደ ኬብሮን መጡ ደግሞም ከእሥራኤል የቀሩት ሁሉ ዳዊትን ያነግሡት ዘንድ አንድ ልብ ነበሩ" 1ኛ ዜና 12:38**

**ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን ሰዎች ማንቀሳቀስ**





በእሥራኤል መካከል ከዚያም በፊት ይሁን ከዚያ ወዲህ ይህንን የመሰለ ከፍተኛ ጥራት ያለው የሰዎች ንቅናቄ ታይቶ አይታወቅም። እነዚህም ከዳዊት ጋር በአዶላም የዋሻ ኑሮ በፈተና ውስጥ አብረው የተሠሩና ከጺቅላግ ልምምድ የወጡ ሰዎችና ትልቅ የማመዛዘንና የተዋጊነት ችሎታ አላቸው። በዳዊት ሕይወት ውስጥ ያለው ከእግዚአብሔር የሆነ አሸናፊነትና ሞገስ በመንግሥቱ ላይ ከመታየቱ ብዙ ዓመታት በፊት እነዚህ ሰዎች በዳዊት ሕይወት ላይ ያለውን የእግዚአብሔር ጣት ለማስተዋል ችለዋል። ስለዚህ ምልክቶቹ በገሀድ ከመታየታቸው ብዙ ዘመናት አስቀድመው እነዚህ ሰዎች ዳዊትን ሊከተሉት መረጡ። እየተለወጠ በመምጣት ላይ ላለው የነገሮች ሥርአት አዲስ አመለካከት ፈር ቀዳጆች ነበሩ። ኃይለኛ የሆነ የወደፊት የእግዚአብሔር መለኮታዊ ቅባት ማረፊያ የት መሆኑን በመንፈሳቸው የተረዱ ናቸው። እያለፈ ካለው የሳኦል መንግሥት አሮጌ ሥርአት ውስጥ የተገኙ ናቸው። ከብንያም ነገድ የሆኑ የሳኦል ወንድሞች።

> **" በጺቅላግም ከቂስ ልጅ ከሳኦል በተሸሸገ ጊዜ ወደ ዳዊት የመጡ እነዚህ ናቸው፣ በሰልፍም ባገዙት ኃያላን መካከል ነበሩ። ቀስተኞችም ነበሩ፣ በቀኝና በግራ እጃቸው ድንጋይ ሊወነጭፉ ፍላጻም ሊወረውሩ ይችሉ ነበር፣ከብንያም ወገን የሳኦል ወንድሞች ነበሩ"**
> **1ኛ ዜና 12:1-2**

በያንዳንዱ ተሀድሶ ውስጥ ጅማሬያቸው በሚያልፈው ሥርአት ውስጥ የነበረ አይታቸው ግን የወደፊቱ ላይ የተተከለ እነዚህን የመሰሉ የጀብዱ ሰዎች ይፈልቃሉ። በእግዚአብሔር ዓላማ ላይ አዲስ ነገር ገና ሳይወለድና ሙሉ ለሙሉ በኃይል ሳይገለጥ አሮጌውን ለመተው የቆረጡ ጠንካራ የሽግግር ፈር ቀዳጆች ናቸው።

**የመለኮታዊ ሥርዓት እውነታና የመንፈሳዊ ልክ ግንባቤ**

ወደ ዳዊት የተሰባሰቡት ጦረኞች ኃይለኛ ቅባትና መንፈሳዊ ችሎታ ነበራቸው። በውሳኔአቸው ትክክለኞች

ከመሆናቸው ሌላ በንጉሡ ላይ ተነግሮ የነበረውን ትንቢታዊ ቃል አሟልተዋል (1ኛ ዜና 11:10)፡፡ ከመካከላቸውም ዳዊት ራሱ ከሠራው ይልቅ እጅግ በጣም የገዘፉ ጀብዱዎችን የፈጸሙ ግለሰቦች ይገኙባቸዋል፡፡ ከመካከላቸው ትንሹ ከመቶ ትልቁ ከሺህ የሚመዛዘን ነበር (1ኛ ዜና 12:4)፡፡ ሁኔታዎች አመቺ ባልሆኑበት ሰዓት ጦርነት የማድረግ ብቃት ነበራቸው፡፡ ዮርዳኖስ ዳር እስከዳር ሞልቶ በነበረ ጊዜ ተሻግረው ጠላትን በማስደንገጥ ድል ነስተዋል (1ኛ ዜና 12:15)፡፡ ይህንን ሁሉ ችሎታ ተሸክመው ሳለ ወደ ለመጽና የእርስበርስ ብጥብጥ ሳያፈገፍጉ እንደየችሎታቸውና እንደየጥሪአቸው የሥልጣን ተዋረዳቸውን አክብረው ይመላለሱ ነበር፡፡

የተሀድሶ ተጨባጭ ሁኔታ (environment) በግለሰባዊ ቅባቶች ውስጥ ያለው አስደናቂ ችሎታ በእግዚአብሔር መለኮታዊ ሥርዓት የሚመራ መሆኑ ነው፡፡ እግዚአብሔር በምድር ያለውን የመንግሥቱን ግስጋሴ እንዲቆጣጠርና የነገሮችን ፍጻሜ በማፋጠን ሥራ ላይ ቤተክርስቲያንን በምድር-አቀፍ እንቅስቃሴዋ በትክክል እንዲመራት እነዚህ ሁኔታዎች ሊኖሩ ይገባል፡፡ በዚህ በ21ኛው ምዕተ ዓመት ራሳቸውን ለማሻሻልና ለማበልጸግ የራሳቸውን ፍልስፍና እየተከተሉ ከእግዚአብሔር መለኮታዊ ሥርዓት ውጪ ራስን ከፍ በማድረግ ከንቱ መፍጨርጨር የተሠማሩ ባለቤት የለሽ አገልግሎቶች ሆነን ከሥልጣን ተዋረድ ውጪ ልንገኝ አይገባንም፡፡ በዘመነ ተሀድሶ በሚኖረው የመንፈስ ንቅናቄ በኩል እግዚአብሔር የባሪያዎቹን ዓላማና የትኩረት አቅጣጫ በሚቀድስበት ሰዓት በምድር አቀፏ ቤተክርስቲያን ዘንድ ያለው በየትኛውም ክልል የተሠማራ ልብ ታላቅ መንፈሳዊ ቀዶ ጥገና ሊከናወንበት ይገባል፡፡

ቁጥጥር የሚመጣው ከአንድ "ጳጳሳዊ" ሥልጣን፣ ከሚቴ ወይም የምክክር ጉባኤ (Council) አይደለም፡፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ነን እንጂ ኃይማኖታዊ ድርጅት አይደለንም፡፡ ቁጥጥር የሚመጣው ሰዎች የሥልጣን ተዋረድ ሥርዓት መኖሩን ተረድተውና በራሳቸው ችሎታ ጥንካሬና መለኪያ ላይ የተቀመጠውን ገደብ አስተውለው መለኮታዊውን ሥርዓት ሲቀበሉ በምድር





ባለችው ቤተክርስቲያን ላይ በስፋት በሚገለጥ የተቀናጀ የመንፈስ ቅዱስ አሠራር በኩል ነው፡፡

## በቤተክርስቲያን ውስጥ ያለውን እውነተኛ መንፈሳዊ አመራር መገንዘብ

የዳዊት በኬብሮን መቀባት ተለያይተው የነበሩትን የይሁዳና የእሥራኤል ቤቶች ተመልሶ አንድ የመሆን መልካም ዜና ተከትሎ የመጣ ክስተት ነው፡፡ የቃል ኪዳኑን ታቦት መልሶ በማምጣትና የዳዊትን ድንኳን በማጽናት ለተከናወነው ንቅናቄ የብርታቱ ሚስጥር በዳዊት አመራር ሥር የተገኘው የወገን አንድነት ነበር፡፡ ሳሙኤል በቀንድ ሞልቶ ያመጣውን ዘይት በራሱ ላይ አፍስሶበት ዳዊት ትንቢታዊ ቅባትን የተቀበለ ቢሆንም እንኳ (1ኛ ሳሙኤል 16:12-13) እግዚአብሔር በእርሱ ላይ ወዳለው የዓላማ ከፍታ ለመድረስ እካሄዱን የሚያፋጥንለት የተባበረና የተስማማ የወገን ድጋፍ ድምጽ ያስፈልገው ነበር፡፡

ኬብሮን ላይ የተካሄደው ይሄ የቅባት ሥርዓት ሁለት አስፈላጊ ገጽታዎች አሉት፡፡ በመጀመሪያ ሽማግሌዎች ዳዊትን የእግዚአብሔር ትንቢታዊ እቅድ ፍጻሜ እንደሆነ አወቀውት ነበር፡፡ ሳኦል ተፈጥሮአዊና አፈር-ቀመስ (ምድራዊ) በሆነ አስተሳሰብ የተሞሉ ሰዎች ምርጫ ነበር፡፡ ንጉሥ እንዲሰጣቸው ያቀረቡት ጥያቄ ከእግዚአብሔር ትንቢታዊ ዓላማ ጋር በአንድ መስመር የሚሄድ አልነበረም፡፡ የእግዚአብሔር ደስ አለመሰኘት መካከል የተከናወነና የእግዚአብሔርን እቅድና ዓላማ ወደ ጎን ገሸሽ የማድረጋቸው ምልክት ነበር፡፡

> " የእሥራኤልም ሽማግሌዎች ሁሉ ተሰብስበው ወደ ሳሙኤል ወደ አርማቴም መጡና፣ እነሆ አንተ ሸምግለሃል ልጆችህም በመንገድህ አይሄዱም አሁንም እንደ አሕዛብ ሁሉ የሚፈርድልን ንጉሥ አድርግልን አሉት፡፡ የሚፈርድልንም ንጉሥ ስጠን ባሉት ጊዜ ነገሩ ሳሙኤልን አስከፋው፣ ሳሙኤልም ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፡፡ እግዚአብሔርም ሳሙኤልን አለው፦ በእነርሱ ላይ እንዳልነግሥ እኔን

**እንጂ አንተን አልናቁምና በሚሉህ ነገር ሁሉ የሕዝቡን ቃል ስማ" 1ኛ ሳሙኤል 8:4-7**

ዳዊትን ንጉሥ አድርገው በተቀበሉበት ጊዜ የእሥራኤል ሽማግሌዎች እግዚአብሔር ለሳሙኤል ሰጥቶት የነበረውንና ወጣቱ ዳዊት መጀመሪያ የተቀባ ጊዜ በእርሱ ላይ የተነገረውን ትንቢታዊ ቃል ነበር ቃል በቃል የደገሙት (1ኛ ሳሙኤል 16:1-3)። ይህም በበኩሉ ሕዝቡ ባለፉት ዘመናት በታላላቅ ነቢያት በላያቸው ላይ ተነግረው የነበሩ ትንቢታዊ መልእክቶች ባለአደራ መሆናቸውን አመልካች ነው። በዚህ አባባላቸው "እንደሌሎች አሕዛብ የራሳችን ንጉሥ ይግዛን" ካሉበት ከግል ምኞታቸው በመመለስ እንደገና በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ለመገዛት መፍቀዳቸውን እንመለከታለን።

በሁለተኛ ደረጃም በዚያው በአንዱ የእግዚአብሔር ጉባኤ (የጦር ሠፈር ወይም ቤተክርስቲያን) ውስጥ የትክክለኛው መንፈሳዊ አመራርና ሥልጣን መቀመጫ ሥፍራው የት እንደነበረ ሕዝቡ ማወቅ ችለዋል።

> " አስቀድሞ ሳኦል ንጉሥ ሆኖ ሳለ እሥራኤልን የምታወጣና የምታገባ አንተ ነበርህ አምላክህ እግዚአብሔርም፣ ሕዝቤን እሥራኤልን ትጠብቃለህ በሕዝቤም በእሥራኤል ላይ አለቃ ትሆናለህ ብሎህ ነበር።"
>
> .1ኛ ዜና 11:2

ዘግይቶም ቢሆን ሕዝቡ በኃይማኖታዊ ይዘታዎች አሠራርና ፍሬ ባለው መንፈሳዊ ሥልጣን መካከል ያለውን የጎላ ልዩነት ሊያስተውሉት ችለዋል። ሳኦል በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ጉልህ የሆነን የሚታይ ንጉሣዊ ብርታትንና አስተዳደርን ቢያንጸባርቅም እንኳ ጥልቅና ትክክል ወደሆነው የእግዚአብሔር ዓላማ መርቶ ያደረሳቸው ግን እርሱ እንዳልነበረ አውቀውታል።

ይህ ማስተዋል ዋጋ ላለው ተሀድሶ የመጀመሪያው ቁም ነገር ነው። ተሀድሶ ኃይማኖታዊ የእወቁልኝ ጥሪ





ወይም ለአንድ አፍታ ታይቶ ወደጎን የሚባል የሕዝቡን ጥልቅ የውስጥ ፍላጐት ከግምት ያላስገባ መንፈሳዊ ሆያሆዬ አይደለም። አዲስ የመንፈሳዊ መገለጦችና ምሪቶችን ደረጃ ወደ ገሀድ የሚያመጣ ተሀድሶ የሚመራው እሥራኤልን በትክክል በሚያወጡና በሚያገቡ ሰዎች እጅ ነው። ከእግዚአብሔር ቀጥተኛ ሥልጣን ሥር ሆነው የነገዶቹን ጉዞ የሚቀይሱ መሀንዲሶች እነዚህ ናቸው።

በእነዚህ ከፊታችን ባሉ የቤተክርስቲያን አዲስ ወራት የእግዚአብሔር ሰዎች በዓለም ዙሪያ ተሠራጭተው የሚገኙትንና ለዚህ ተሀድሶ የሚሆነውን ትክክለኛ ቃል የያዙ ሐዋርያዊ መሪዎችን ድምጽ ምድር-አቀፏ ቤተክርስቲያን (global church) ከምትገኝበት የትኛውም አካባቢና የአገልግሎት ክፍል በትክክል ሰምተውና ገምግመው ሊለዩ ወደሚችሉበት የቃሉ መረዳት ደረጃ ማደግ ይኖርባቸዋል። በባህል መመካታችንን በዘር ልዩነት ላይ የተመሠረተ ወገናዊነታችንን ልማዳዊ የአሠራር መስመሮቻችንን (Traditional Patterns) ወይም የቤተክርስተያንን ትክክለኛ ቅርጽ ሊያጎሉ ያልቻሉ ድርጅታዊ እንቅፋቶችን ሁሉ የእሥራኤል ሽማግሌዎች የራሳቸውን ድክመቶች ባስወገዱበት ምሳሌ ማስወገድ አለብን። የምድሪቱን እውነተኛ ዳዊቶች ቤተክርስቲያን ልትቀበላቸውና ለድንኳኑ ወደ ተዘጋጀው ትክክለኛ ሥፍራ የሚደረገው ጉዞ በአስቸኳይ መጀመር አለበት።

## ★ *የድንኳኑ መርህ ቁጥር ሁለት ድንኳኑ አዲስ ምሽግ መገንባትን ይጠይቃል*

> " ዳዊትም እሥራኤልም ሁሉ ኢያቡስ ወደምትባል ወደ ኢየሩሳሌም ሄዱ፣ በአገሩም የተቀመጡ ኢያቡሳውያን በዚያ ነበሩ። በኢያቡስም የተቀመጡ ዳዊትን፣ ወደዚህ አትገባም አሉት፣ ዳዊት ግን አምባይቱን ጽዮንን ያዘ፣ እርስዋም የዳዊት ከተማ ናት።"
>
> 1ኛ ዜና 11:4-5

## ሳታመቀው ኃይል ፍንዳታ አዲስን "ኤፒሴንተር" ፈልጎ ማግኘት

ድንኳኑን የመትከል ሂደት አዲስን ኤፒሴንተር ማግኘት አስፈልጓል:: ኤፒሴንተር (Epicentre) ማለት ለዘመኑ ተስማሚ የሆነ የእግዚአብሔር ነገሮችን ወደገሀድ ለማምጣት እንዲረዱን የምንጠቀምባቸው የአስተሳሰብ፣ የአቋሞችና የመረዳቶች ጽኑ አምባ ነው:: ታላላቅ ድርጊቶች የሚፈልቁበት ሥፍራ ነው:: ለዳዊት ጉዞው ከጺቅላግ ተነስቶ ወደጽዮን የሚያመራ ነው:: ጺቅላግ የዳዊትን የግል ጽኑ አምባ ያመለክታል::

> "በጺቅላግም ከቂስ ልጅ ከሳኦል በተሸሸገ ጊዜ ወደ ዳዊት የመጡ እነዚህ ናቸው በሰልፍም ባገዙት ኃያላን መካከል ነበር::" 1ኛ ዜና 12:1

> "ዳዊትም በምድረበዳ ውስጥ ባለችው በአምባ-ይቱ ሳለ ከጋድ ወገን የሆኑ እነዚህ ጋሻና ጦር የሚይዙ ጽኑዓን ኃያላን ሰልፈኞች ወደ እነርሱ ተጠጉ፣ ፊታቸውም እንደ አንበሳ ፊት ነበር:: በተራራም ላይ እንደሚዘልል ሚዳቋ ፈጣኖች ነበሩ::" 1ኛ ዜና 12:8

ተሀድሶ በምድረ እሥራኤል ከመምጣቱ በፊት ዳዊት ከሳኦል ሸሽቶ ባለበት ዘመን ጺቅላግ የብርታቱና ሠራዊት የማንቀሳቀሱ የመጀመሪያ ጽኑ አምባው ነበር:: ዳዊት በእሥራኤል ሁሉ ላይ ወደዙፋን ከፍ ከፍ በተደረገበት ጊዜ ግን ወደ አዲስ ጽኑ አምባ መሸጋገር ነበረበት:: ጽዮን የእግዚአብሔር ጽኑ አምባ ነበረች፣ የእግዚአብሔር ብርታት መገኛና የኃይሉ መገለጫ ሥፍራ ናት::

> "እግዚአብሔር ጽዮንን መርጦአልና ማደሪያ-ውም ትሆን ዘንድ ወድዶአታልና::"
> መዝሙር 132:13





የተሀድሶ ሂደት በቤተክርስቲያን ከራሳችን ጽኑ አምባ ወጥተን ወደ እግዚአብሔር ጽኑ አምባ መሸጋገርን ይወክ-ላል:: የራሳችን የግል ብርታት ዋስትና ሆኖ ከተቆጠረበትና የራሳችን የአገልግሎት ብቃት በእኛው ክልል ገናናነቱን ካስመሰከረበት ሁኔታ ወጥተን ብርታቱ ሙሉ ለሙሉ የእግዚአብሔር ወደ ሚሆንበት አዲስ አምባ መግባት አለብን:: የጽዮን ይዞታ እግዚአብሔር የሚኖርበት ሥፍራ ነው:: ብርቱ የንግሥና ኃይል የሚገለጥበትና ለዘለዓለም ከእግዚአብሔር ክብር ጋር የተሣሰረ ሥፍራ ነው::

## ኢያቡሳውያንን ማባረር

የእግዚአብሔር ጽኑ አምባ በቁጥጥር ሥር የገባችው ከሽባዎችና እውራን ጋር በተደረገ ብርቱ ትንንቅ መካከል ነው::

> "ንጉሡና ሰዎቹም በአገሩ ውስጥ ከተቀ-መጡት ከኢያቡሳውያን ጋር ለመዋጋት ወደ ኢየሩሳሌም ሄዱ፣ እነርሱም:- ዳዊት ወደዚህ ሊገባ አይችልም ብለው አስበው ነበርና ዳዊትን እውሮችንና አንካሶችን ካላወጣህ በቀር ወደዚህ አትገባም አሉት:: ነገር ግን ዳዊት አምባይቱን ጽዮንን ያዘ፣ እርስዋም የዳዊት ከተማ ናት:: በዚያም ቀን ዳዊት ኢያቡሳውያንን የሚመታ በውኃ መሄጃው ይውጣ የዳዊትም ነፍስ የምትጠላቸውን እውሮችንና አንካሶችን ያውጣ አለ::"
>
> 2ኛ ሳሙኤል 5:6-8

የተሐድሶ ሰው ነፍስ በቤተክርስቲያን ውስጥ ያለውን የኢያቡሳውያን መርህ ሊጸየፈው ይገባል:: ኢያቡሳውያን የሚወክሉት የእግዚአብሔርን ጽኑ አምባ የሚያረክሰን ማንኛውንም ነገር ነው:: የእግዚአብሔርን ክብር የወደፊት መገለጫ ሥፍራ የምታመለክተው የኢየሩሳሌም ከተማ በአንድ ዘመን ኢያቡስ ተብላ የምትጠራና ገና ዘውድ ጭኖ መንገሥ የጀመረውን ዳዊት ወደ ሥልጣኑ እናስገባም ብለው በተቃወሙት

ኢያቡሳውያን ተይዛ የነበረች ከተማ ናት፡፡ ኢያቡስ በመጨረሻ ድንኳኑ የተተከለባት ሥፍራ ሆነች፡፡ አሞጽ በትንቢቱ እንዳስታወቀው የዳዊት ድንኳን በዘመናችን ተመልሳ የምትገነባና የምትመሠረት ከሆነ እኛም ከመካከላችን ኢያቡሳዊ አሠራርን መመንጠር አለብን፡፡

በየትኛውም ዘመን ቢሆን የዳዊት መንፈስ ወደ ተሀድሶ ሥፍራ የሚያደርገውን ግስጋሴ ሲቋቋሙት የሚወጡት በከተማይቱ የሠፈሩ አንካሶችና እውራን ይሄም የኢያቡሳዊ አመለካከትና አስተሳሰብ መካከለኛ እውነት ነው፡፡ "አንካሶች" የሚወክለው በእግዚአብሔር ዓላማዎች ውስጥ ቀጥ ብለን እንዳንራመድ የሚከለክሉ ነገሮችን ነው፡፡ "እውራን" ደግሞ ለዘመናችን ያለውን የእግዚአብሔር ሐሳብ፣ ፈቃድና ፍላጎት የማስተዋል የመገንዘብና በትክክል የመረዳት ችሎታችንን የሚገድሉ ሁኔታዎችን ይወክላል፡፡ የእውሮችና የአንካሶች ጥምረት የእግዚአብሔርን ዓላማ በትክክል ወደመረዳት የጽዮን ከፍታ መግባትንና ለዚች ኘ ላኔት ያለው ፈቃዱ በኃይል መገለጡን የምትከለክል በኃይማኖትና "በኘሮግራሞች" የብረት ጫማ ሥር የተረገጠች ደካማ ቤተክርስቲያንን የሚያመለክት ነው፡፡ ተሀድሶ ኢያቡሳውያንን ከእግዚአብሔር ተራራ ላይ አሳድዶ ያጠፋል፡፡

እነዚህ ጨካኝ ጠላቶች የሚጠረጉት በተሀድሶ ወራት የእግዚአብሔር መንፈስ በሰዎች ልብ ውስጥ በሚያደርገው ሥልጣን የተሞላ እንቅስቃሴ በኩል ነው፡፡ ዳዊት አምባይቱን ጽዮንን ለመቆጣጠር ያካሄደው ውጊያ ፊትለፊት የተደረገ ወታደራዊ ግጥሚያ ሳይሆን እስከምሽጋቸው ድረስ ደረጃ በደረጃ የተካሄደ የደፈጣ ውጊያ ነበር፡፡

> **"በዚያም ቀን ዳዊት፣ ኢያቡሳዊያንን የሚመታ በውኃ መሄጃው ይውጣ የዳዊትም ነፍስ የምትጠላቸውን ዕውሮችንና አንካሶችን ያውጣ አለ፡፡" 2ኛ ሳሙኤል 5:7-8**





የዳዊት ጀግኖች በውሃ መተላለፊያው ወደ ላይ ወጡ፡፡ "የውሃ መተላለፊያ" የሚለው የመንፈስ ቅዱስን እንቅስቃሴ ነው፡፡ ውጤቱም አንካሶችና እውሮች እንዳይገቡ ለዘላለም የተከለከሉበትን ቤት መሥራት ነበር፡፡ ይሄም ለአዲስ ምሳሌያዊ ንግግር መወለድ ምክንያት ነበር፡፡ ከዚያ ቀን ጀምሮ "አንካሳና እውር ወደቤት አይገባም" እየተባለ መነገር ጀመረ፡፡

እግዚአብሔር በአሞጽ በኩል በሰጠው ተስፋ መሠረት በዘመኑ ፍጻሜ ላይ ያለች ቤተክርስቲያን በምድር ላይ ወደኃይል ሥፍራዋ ስትመጣ የሚገነባው የተሀድሶ ቤት ይሄንን ይመስላል፡፡ አንካሶችና እውሮች ወደ እግዚአብሔር ቤት ፈጽመው መግባት የሌለባቸው መሆኑ በሕዝቡ ዘንድ ሙሉ ተቀባይነት እስኪኖረው ድረስ የእግዚአብሔርን በዓላማ የተመሠረተ የኃይል ግስጋሴ የሚቋቋሙ ነገሮች ተጠርገው የተወገዱበት ሥፍራ ነው፡፡ ጽዮን የምትወክለው ለዘመናችን ያለውን የእግዚአብሔር ፈቃድ ወደፊት ለማራመድ የሚጠቅሙ የአመለካከት አቋሞችን በማሕበረ ምዕመናኑ መካከል ማዳበርን ነው፡፡

## በጽኑው አምባ መኖር

> **"ዳዊትም ዙሪያዋን ከሚሎ ጀምሮ ወደ ውስጥ ቀጠራት፡፡ ዳዊትም እየበረታ ሄደ፣ የሠራዊት አምላክ እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር ነበረ፡፡"**
> **2ኛ ሳሙኤል 5:9-10**

ቤተክርስቲያን በእግዚአብሔር ጽኑ አምባ መኖርን መለማመድና ይህንኑ "የጽኑ አምባ የኑሮ ዘይቤ" ለምድር አሕዛብ ልታሳይ ይገባታል፡፡ ኢያቡሳውያንን ከደመሰሰ በኋላ ዳዊት ከተማይቱን "የዳዊት ከተማ" ብሎ ጠራት፡፡ በአምባይቱ በጽዮን ያለው የአኗኗር ዘይቤ ከዳዊት ስም ጋር ለዘላለም ተቆራኝቷል፡፡ የዳዊት ዐይነቱ የሕይወት ዘይቤና የእግዚአብሔር ክንድ መገለጥ ተለያይተው የማይታዩ ናቸው፡፡ ስለዚህም የዳዊት ከተማ የእግዚአብሔር ተራራ ተብሎ ሊታወቅ ቻለ፡፡

ዳዊት ያንን ጽኑ አምባ በመቆጣጠር ብቻ አልተዘናጋም። ቁጥጥሩ ከብዙ መጪ ትውልዶቹ እጅ እንደማይወጣ አድርጎ በምሽጎች አጠናከረው። ጽዮን ከውስጥም ከውጪም የተጠናከረች እንድትሆን ዙሪያዋን ከገነባ በኋላ መልሶ ውስጧን ገነባት። ይሄም በዘመነ ተሀድሶ ላሰችው ቤተክርስቲያን የአስተሳሰብ ይዘት ብርቱ ምሳሌነት ያሰውትምህርት ነው። በአሕዛብ ላይ ጠንካራ ተጽእኖ ማምጣት በሚያስችል ትክክለኛና ምልክት ሰጪ የ21ኛው ክፍለ ዘመን የነሮ ዘይቤ በመመላለስ የእግዚአብሔርን ኃይልና ብርታት ካሁን ቀደም ባልታየ መልኩ ለመግለጥ ራሳችንን ከበስተውጪ መገንባት ይኖርብናል። ሆኖም ይሄ ብቻውን አይበቃም። በመጪዎቹ ተከታታይ ዘመናት የመንግሥቱ ኃይል በእኛ በኩል ግልጽና ንጹሕ ሆኖ እንዲታይ በጠንካራ አስተሳሰብና መንፈሳዊ ሥነ-ምግባር የተጠናከሩ ውስጣዊ መሰኮታዊ ጠንካራ ምሽጎችን መገንባትም ግዴታችን ይሆናል።

የወደፊት እድልፈንታችን የሚወሰነው እነዚህን እሴቶች ሰራሳችን በማሰባሰባችን ላይ ነው። ዳዊት ሁልጊዜም ጠንካራ ተዋጊ፣ ነብይና የሕዝብ መሪ ነበር። በተከታዮቹ ዘንድ ታማኝ ተገዥነትን (loyalty) እና መደፋፈርን (Confidence) የሚያነሳሳ ባህሪ ከማንጸባረቁ በተጨማሪ ልባቸውንም የማቀጣጠል ችሎታ ነበረው። ነገር ግን ይሄ ሁሉ ታላቅ ችሎታ የተጨመረለት ወደጽዮን የምሽግ ደረጃ ወጥቶ ኢያቡሳውያንን በማባረር ጽኑ አምባ ከመሠረተ በኋላ ነበር።

> " ዳዊትም እየበረታ ሄደ የሠራዊት አምላክ እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር ነበረ።"
>
> **2ኛ ሳሙኤል 5:10**

የወደፊት የቤተክርስቲያን ታላቅነት በምድር ላይ ከሚገለጠው የእግዚአብሔር ክብር (ታላቅነት) ተነጥሎ አይታይም። በተሀድሶ ሂደት ውስጥ የእኛ ስምና ዝና በአሕዛብ መካከል ከሚገለጠው የእግዚአብሔር ስምና ዝና ጋር በአንድነት የሚታወቅ ይሆናል። ኢየሱስ ክርስቶስ አስተማማኝ በሆነ መልኩ በዳዊት ዙፋን ላይ ይቀመጣል።





እኛም ከጌታችን አገዛዝና ኃይል ተነጥለን መታየት አንችልም።

## ★ የድንኳኑ መርህ ቁጥር ሦስት፡- ድንኳኑ አሕዛብን የመባረክ ፍላጎት ያካትታል

> " ዳዊትም ከሻለቆችና ከመቶ አለቆች ከአለቆቹም ሁሉ ጋር ተማከረ። ዳዊትም የእስራኤልን ጉባኤ ሁሉ፡- መልካም መስሎ የታያችሁ እንደሆነ ከአምላካችን ከእግዚአብሔርም ወጥቶ እንደሆነ በእሥራኤል አገር ሁሉ ለቀሩት ወንድሞቻችን በከተሞቻቸውና በመሰማርያዎቻቸውም ለሚቀመጡ ካህናትና ሌዋውያን ወደ እኛ ይሰበሰቡ ዘንድ እንላክ በሳኦልም ዘመን አልፈለግነውምና የአምላካችንን ታቦት ወደ እኛ እንመልስ አላቸው። ነገሩም በሕዝቡ ሁሉ ዓይን ቅን ነበርና ጉባኤው ሁሉ እንዲሁ እናደርጋለን አለ። "
>
> **1ኛ ዜና 13:1-4**

## ራስ ወዳድነትን ያስወግዳል

ታቦቱን ለማስመለስ ዳዊት ያደረገው የመጀመሪያ ሙከራ ለሕዝቡ ደህንነት ከነበረው መልካም ምኞት የመነጨ ነበር። ተሃድሶን ለማቀጣጠል የገፋፋው ነገር በሕዝቡ የማድረግ ዴሞክራሲያዊ መርህ ነበር። ይሄም ማለት ተሀድሶው የተመሠረተበት ዝቅተኛ መለኪያ (Common Denomenetor) ራስ ወዳድነት ያለበት የሕዝብ አጠቃላይ ስምምነት ነበር።

ይህ ዓይነቱ ወደ ተሀድሶ የተደረገ የመጀመሪያ ሙከራ በእግዚአብሔር እጅ ሲፈርስ እናያለን። ወደ ኢየሩሳሌም በሚደረገው ጉዞ መካከል አዛ "ሊወድቅ የነበረውን ታቦት" በመደገፍ ሙከራ ላይ በእግዚአብሔር ተቀሰፈ. (2ኛ ሳሙኤል 6:5-7)። በተነቃቃው የዳዊት

ድንኳን ምሳሌ የሆነው የቃል ኪዳኑ ታቦት የጌት ሰው በነበረው በአቢዳራ ቤት ለሦስት ወር ተቀመጠ።

## ኤዶማውያንን መባረክ

አሁን ላለንበት ሁኔታ የድንኳኑን ምስጢር ፍቺ ስንመረምር አቢዳራ (Obed-Edom) የሚለው ስያሜ ጠቀሜታው የላቀ ነው። የስሙ ትርጓሜ "የኤዶም ልጅ" ማለት ነው። ይሄ ስም ለመጀመሪያ ጊዜ ተገልጦ የምናገኘው ኤሳው ከአባቶች የወረደለትን የትውልድ መብቱንና እግዚአብሔር ለአብርሃም ዘር የገባውን ቃል ኪዳን ባቃለለበት ምዕራፍ ውስጥ ነው (ዘፍጥረት 25:30)። በጠቅላላው መጽሐፍ ቅዱስና በእሥራኤል ታሪክ ሁሉ ኤዶማውያን የሚታወቁት በእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላትነታቸውና ይህንንም ጥላቻ በልጅ ልጆቻቸው ዘንድ አጽንተው በመጠበቃቸው ነው። ከግብጽና ከፈርኦን ባርነት በተደረገው በታላቁ ጉዞ እሥራኤልን በግዛ ቸው ሊያሳልፉ ፈቃደኞች አልነበሩም (ዘኁልቁ 20:18-21) በሀዳድ መሪነት ኤዶምያስ ለንጉሥ ሰለሞን ዋነኛ ጠላት ነበረች። ከግብጽ ጋር ሕብረት ፈጠሩ። እንዲያውም ሀዳድ የግብጽን ንግሥት የቴቁምናስን እህት አግብቶ ይኖር ነበር (1ነገሥት 11:14-25)። በባቢሎናዊው ናቡከደነጾር ኢየሩሳሌምን የማፍረስ አስከፊ ዘመቻ ጊዜ ኤዶምያስ የዘመቻው ቀንደኛ ደጋፊና የማፍረሉና የዘረፋው ዋነኛ ተባባሪ ነበር (መዝሙር 137:7)።

ታሪክ እንደመዘገበው ደግሞ በብሉይና አዲስ ኪዳን መካከል በነበረው የማካባውያን (Macabees) የአገዛዝ ዘመን ኤዶማውያን ኢዱሚያ በተሰኘች አንዲት የእሥራኤል ሀገር ተጠቃልለው ነበር። ነገር ግን ጥላቻቸውና መሪር የተቃራኒነት አቋማቸው ፍንክች አላለም። በ70 ዓ.ም. ሮማዊው ጀነራል ቲቶ ኢየሩሳሌምን ማጥቃት በጀመረ ጊዜ 20,000 ኤዶማውያን ወደ ከተማይቱ እንዲገቡ ስለተፈቀደላቸው በዚያ አስጨናቂ የጥፋት ዘመን በጨካኝ አገዳደል፣ በዘረፋና በማፍረስ ተግባር ውስጥ ዋነኛ ተዋናይ ነበሩ። ንጉሡ አሜስያስ በሴይር በሚገኙ ኤዶማውያን ላይ





ዘመቻ በከፈተ ጊዜ ኤዶማውያን ጣኦት አምላኪ ሕዝቦች እንደነበሩ ይታወቃል (2ኛ ዜና 25:14)።

እንግዲህ አቢዳራ (የኤዶም ልጅ) የሚወክለው እንዲህ ዓይነቱን የኋላ ታሪክ ነው። እንዲሁም የጌት ሰውና ከዋነኛይቱ የፍልስጤም ከተማ ጋር የተሳሰረ ስም ያለው ነው። ጌት ደግሞ ዳዊት ወደ መንፈሳዊ ዕውቅና መምጣት በጀመረበት ዘመን የእሥራኤል ዋነኛ ተገዳዳሪ የነበረው የጎልያድ መኖሪያ ናት። አቢዳራ በእግዚአብሔር ነገሮችና በእግዚአብሔር ሕዝቦች ላይ ዘለዓለማዊ ጥላቻን ይዞ የተቀመጠን መርህ የሚወክል ሰው ነው። ነገር ግን የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት በቤቱ ለ3 ወር ተቀመጠ። የዚህ ድርጊት መንፈሳዊና ገሀድ ውጤት የሚሰጠን ትምህርት ጉልህና ከማንም ዕይታ የማያመልጥ ነው። ይህም በተግባራቸውና በይዞታቸው የእግዚአብሔር ሕግና በመካከላቸው ሊገኝ የሚፈልግ ሕልውናው ጠላቶች የሆኑ አሕዛብን እግዚአብሔር በመካከላቸው ተገኝቶ ሊባርካቸው ምን ያህል እንደሚወድድ የእግዚአበሔርን ልብ አመልካች መስታወት ነው።

የታቦቱ በአቢዳራ ቤተሰብ መካከል መገኘት ተጨባጭ የሆነን የእግዚአብሔር በረከት በዚያ ቤተሰብ ሁሉ ላይ ማስገኘቱን በተመለከተ ጊዜ ዳዊት የልብ፣ የአመለካከትና የትኩረት አቅጣጫውን እንዲለውጥ ተገደደ።

> "የእግዚአብሔርም ታቦት በጌት ሰው በአቢዳራ ቤት ሦስት ወር ያህል ተቀመጠ እግዚአብ-ሔርም አቢዳራንና ቤቱን ሁሉ ባረከ። ንጉሡ ዳዊትም እግዚአብሔር የአቢዳራ ቤትና የነበረውን ሁሉ ስለ እግዚአብሔር ታቦት እንደ ባረከ ሰማ። ዳዊትም ሄዶ የእግዚአብሔርን ታቦት ከአቢዳራ ቤት ወደ ዳዊት ከተማ በደስታ አመጣው።" **2ኛ ሳሙኤል 6:11-12**

የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት ወይም የእግዚአብሔር በሙሉ ሕልውናው በመካከላቸው መገኘት አሕዛብን እንደሚባርክና ኤዶማዊውን ነፃ እንደሚያወጣ

(እንደሚዋጅ) ልንገነዘብ ይገባናል። ይሄም በአሞጽ እንደተሰጠው ትንቢታዊ ተስፋ የዳዊት ድንኳን በመንፈሳዊ ደረጃ ተመልሶ በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ሲተከልና ሲገነባ የሚከሰት ይሆናል። ወደ እምነት አንድነት ሲመጡ አስቀድመው በእግዚአብሔር የተወሰኑት አሕዛብና የኤዶም ቅሬታዎች ሁሉ በበስሰችው የዳዊት ቤተክርስቲያን በኩል ተሰቅመው ወደ እግዚአብሔር ጎተራ ይጨመራሉ።

በዘመነ ተሀድሶ ግለሰባዊ ወደ ሰማይ ቤት የማምሰጫ መንገዳችንን ሰማቃናት ሳይሆን ነገር ግን አሕዛብ ወደ ደህንነት የሚጎርፉበትን ኃይለኛ ጎዳና ሰማሰናዳት የአሠራር ቅልጥፍናችንን እናሻሽላለን። እስከዛሬ ድረስ የቤተክርስቲያን አስተሳሰብ ተወጥሮ የቆየው በግለሰባዊ የማምለጥ ዘዴ ላይ ነው። ሰዎች በማምለጥ አስተሳሰብ (escape mentality) እስኪሞሉ ድረስ ስለ “መነጠቅ” አስተምረናቸዋል። ይሄም የእግዚአብሔር መንግስት ወደፊት ሊገሰግስ የሚያስችል ገገር አመለካከትና አስተሳሰብ እና በአጥፊ የሰይጣን ቀንበር ሥር ላሉት ብዙሀን የሚራራ ልብ እንዳይኖረን ታላቅ እንቅፋት ነው (ማቴዎስ 9:35-38)። አሁን ግን በተሀድሶ ዘመን ለጌታ ዳግም ምጽአት ወደ ላይ መመልከታችንን ሳናቋርጥ በተጠናከረ አዲስ ጉልበት እጃችንን አርዳታ ወደሚያስፈልጋቸው የምድር እስረኞች እንዘረጋለን። ይህንንም የምናደርገው አሕዛብ ራሳቸው ወደ እግዚአብሔር ቀርበው እንዲባረኩ ተጽእኖ የሚያደርግባቸውን ጠንካራ የተሀድሶ ይዞታ በምድር-አቀፉ ቤተክርስቲያን ውስጥ በመገንባት ነው።

## ✶ የድንኳኑ መርህ ቁጥር አራት፦ አስቀድሞ የተጻፈን አስተሳሰብ መያዝ ይጠይቃል

> “ የእግዚአብሔርንም ታቦት ይዘው ገቡ ዳዊትም በተከለለ ድንኳን ውስጥ አኖሩት፤ የሚቃጠለውን መሥዋዕትና የደህንነቱን መስ-ዋዕትም በእግዚአብሔር ፊት አቀረቡ።”
> 1ኛ ዜና 16:1





> “ በዚያም ቀን ዳዊት በአሳፍና በወንድሞቹ እጅ እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ አስቀድሞ ትዕዛዝን ሰጠ። እግዚአብሔርን አመስግኑ፤ ሰሙን ጥሩ፤ ለአሕዛብ ሥራውን አውሩ፤ ተቀኙለት፤ ዘምሩለት፤ ተአምራቱን ሁሉ ተናገሩ።” 1ኛ ዜና 16:7-9

ድንኳኑ ስንል ዳዊት በሕዝቡ ላይ ለሰዘረጋው ድንኳን ማለታችን ነው። በድንኳኑ ውስጥ ታላቅ የሰውጥ ሂደት እየተካሄደ ነበር። የሙሴ ሕግ በሕዝቡ ላይ አሁንም ገገር ነበር። በሕጉ ላይ ለውጥ የሚጠይቅ ዘመን ከእግዚአብሔር ስለመምጣቱ በነቢያት በኩል የተነገረ ምንም ዓይነት አጠቃላይ ጥቆማ አልነበረም። ነገር ግን ዳዊት በተገለጠለት ራዕይ ጠቅላላውን ሕብረተሰብ ከበፊቱ ወደበለጠ የመንፈስ ቅዱስ አሠራርና ልምምድ ደረጃ ከፍ ሲያደርግ እናያለን። የዳዊት ድንኳን እስከዚያ ጊዜ ድረስ በሥልጣን ላይ ከቆየው የሙሴ ድንኳን ጠባብነት የሕዝቡን አስተሳሰብ ነፃ ያወጣ አሠራር ነው።

ዳዊት በድንኳኑ ውስጥ የመሠረተው የአምልኮ ሥርዓት የዚህ አዲስ አሠራር እንቀሳቃሽ ኃይል ነበር። ይህ ዓይነቱ አምልኮ ሕዝቡን ከሕግ ውስንነት ነፃ የሚያወጣና አዲስ መንፈሳዊ ነፃነት እንዲለማመዱ የሚያደርግ ባህልና ሁኔታ የሚፈጥር ነበር። ይህም ማለት የዳዊት ድንኳን ሙሉ በሙሉ ሥራ ላይ በመዋሉ ውስጥ አስተድሞ የተወሰነ አስተሳሰብ አለ ማለት ነው። የእግዚአብሔርን ሥራ፣ ክብሩን፣ ተአምራቱን ከፍ አድርጎ ለምድር አሕዛብ በመናገር የሚገልጥ አንድ የድንኳኑ ኃይለኛ ትንቢታዊ ገጽታ አለ (1ኛ ዜና 16:10፣23-24)። ዳዊት በአሳፍ እጅ የሰጠው መዝሙር ለድንኳኑ ሥርዓት የወደፊት እንቅስቃሴ ትክክለኛ አቅጣጫን ያስያዘ መርህ ነበር። ይሄም ብቻ ሳይሆን ሕዝቡ በዳዊት ምሥጋናና አምልኮ በኩል ወደ እግዚአብሔር በሚቀርቡበት ጊዜ የዳዊትን አስተሳሰብ የመገለጥ ደረጃና መንፈስ ለሕዝቡ ያካፈለ አሠራር ነበር። የአምልኮ ሥርዓቱ የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን ተስፋዎችና እግዚአብሔር በምድር ላይ ሲፈርድ

የመምጣቱን እውነታ በማስታወስ ላይ ያተኩራል (1ኛ ዜና 16:33)።

እነዚህ ሁኔታዎች ሁሉ እግዚአብሔር በስሙ የተጠሩ አሕዛብን ለመሰብሰብ እጁን በሚዘረጋበት በዚህ በእኛ የተሀድሶ ዘመን በዳዊት ድንኳን ምስረታ ላይ አስፈላጊ የሆኑ ቁላቁሶችን ያመለክታሉ። ለዘመኑ ተሀድሶ የተወሰነ አስቀድሞ የተጻፈ የአስተሳሰብ ደረጃ አለ። ልክ ያኔ ዳዊት በጥንቃቄ አስቦባቸው የቀረጻቸውን ኃይለኛ የትንቢታዊ ተስፋዎች እወጃና ከእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ዓላማ ጋር በስምምነት የመቆም መንፈስ ስሕዝቡ እንዳካፈለ ስእኛ ዘመን የተወሰነውም ተሀድሶ በምድር ላይ ውጤቱ እንዲኖረው እኛም አስቀድሞ ወደ ተዘጋጀልን የጊዜው አመለካከትና አስተሳሰብ ውስጥ መግባት ይጠበቅብናል።

በአሮጌው ደካማና የጨረጨስ የቤተክርስቲያን የአስተሳሰብ፣ የአመለካከት ዝንባሌና መንፈስ ተጠቅሞ በአሕዛብ ላይ ለውጥ ማምጣት አይቻልም። ዳዊት ድንኳኑን ስመትከል ባሰበ ጊዜ ፈጽሞ ጸረ-ሙሴ የሆነ አመለካከትና አሠራር ማዋቀር አስፈልጎት ነበር። ካዋቀረውም በኋላ አመለካከቱና አሠራሩ ለተከታታይ ትውልዶች እንዳያቋርጥ የሚያደርጉ ሲስተሞችን (የአሠራር ቅደም ተከተሎች) ደነገገላቸው። የተሀድሶ አስተሳሰብ በሥራ ላይ ከቆየው ከዘመኑ የአሠራር ዘይቤ ጋር የተቃረነ ነው። ልክ ያኔ በዳዊት ዘመን ሕዝቡ በታቦቱ ፊት (እንደ ሙሴ አሠራር ቢሆን) ለሊቀካህናቱ ብቻ ወደተፈቀደ ሥፍራ መድረስ እንደቻሉ ለዘመናችን የተወሰነውም የተሀድሶ አስተሳሰብ ቅዱሳንን ነባር አሠራሮች ከሚፈቅዱላቸው በተሻለ መንገድ ወደ እግዚአብሔር ነገሮች ሊያደርስ ወደሚችል የመንፈስ ቅዱስ አሠራር ያስገባል።

አሞጽ ትንቢት እንደተናገረ በዚህ በእኛ ዘመን ድንኳኑ ተመልሶ በእግዚአብሔር ይገነባል። ምድር-አቀፏ ቤተክርስቲያን ሥር ነቀል ወደ ሆነ የአስተሳሰብ ደረጃ በመግባት ትውልዳችን ከጠበቀው ጊዜ እጅግ አስቀድማ የእግዚአብሔን ዓላማዎች በምድር ላይ ትገልጣለች። የ21ኛ ውን ክፍለ ዘመን አማኞች ወደ እግዚአብሔር የዓላማዎች





ልቀት የሚያስገባ አዲስ አመራር ስስሚነሳ በቤተክርስቲያን ውስጥ አዳዲስ የቃልኪዳን ደረጃዎች ይመሠረታሉ። ተሀድሶ የቤተክርስቲያንን መንፈሳዊ ጉዞ ጉልህና ጠንካራ በሆነ መንገድ ያነሳሳል። ትክክለኛው የእግዚአብሔር ፈቃድና ሐሳብ በምድር ውስጥ እንዳይገለጥ የሚቃወሙና የሚያደናቅፉ እንካሶችና እውሮችን ነቅለን እየጣልን ወደ ጽዮን ይዞታችን እንገሰግሳለን። የዳዊት ከፍታ ሥፍራዎችና አመለካከቶች ተቀባይነትን ያገኙ የመላይቱ ቤተክርስቲያን ገንዘቦች በሚሆኑበት ጊዜ የማዳን እጆቻችንን በአዲስና ከመቼውም በበለጠ ኃይለኛ መንገድ ወደ አሕዛብ መዘርጋት እንጀምራለን። የእግዚአብሔር ክብር ልዩ በሆነ መንገድ እየገሰጥን እስከ ዛሬ ድረስ ይከተሉት በነበረው አመለካከታቸው ላይ ትልቅ ተጽእኖ በማምጣት ብዙ አሕዛብንና በስሙ የተጠሩ ወገኖች ወደ እግዚአብሔር በረከት ማድረስ እንችላለን።

## ምዕራፍ 8

# ለተሀድሶ የተመረጠ ትውልድ በትውልዶች መካከል ማስተላለፍ

የእግዚአብሔር ዓላማ ለአንድ ትውልድ ብቻ የተወሰነ አይደለም። እርሱ የአብርሃም፣ የይስሐቅና የያዕቆብ አምላክ ነው። ዓላማዎቹ ወደ ሚቀጥሉት ተከታታይ ትውልዶች የመፍሰስ ባህሪ ያላቸው ስለሆኑ በውስጣቸው ያለውን ከትውልድ ወደ ትውልድ ተላላፊ ዘር ተሸክመው ወደየትውልዱ መንዝና ዘሩን ማካፈል ካልቻሉ (ዓላማዎቹ) ለፍሬ ደረሱ ማለት አይቻልም። ትውልድ የሚለው ቃል በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ በሰዎቹ ዓይነት፣ ሁኔታና መደብ ከሌሎች የተለየን አንድ የጊዜ ክልል ይወክላል። በቤተክርስቲያንም ሆነ በምድር ውስጥ ስላለ መንፈሳዊ ተሀድሶ በምንነጋገርበት ጊዜ በዘመን ቅደም ተከተል ላይ ሳይሆን ከዚያ ጠለቅ ባለ ደረጃ ስለትውልዶች መነጋገራችን ነው። ተሀድሶ የአንድን ሙሉ ሕዝብ የአሠራር ብርታት የመገለጥ ባህሪና አጠቃላይ ማንነት ስለሚያሸጋግር በምድር አቀፏ ቤተክርስቲያን ውስጥ አንድን አዲስ መንፈሳዊ ትውልድ ያስገኛል። በዓይነትና በሁኔታ የተለየን አንድ አዲስ የሰዎች ስብስብ በምድር ላይ ስለሚፈጥር የመንግሥቱን የፊትለፊት ጉዞ ወደአዲስ ደረጃ የሚያደርስ ችቦ ተሸካሚ ትውልድ ያዘጋጃል።

የእግዚአብሔር ታላቅነት ከሚገለጽበት አንዱ መንገድ ምስጋናውና የታላቅነቱ እውቀት ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ መሆኑ ነው።

> "እግዚአብሔር ታላቅ ነው እጅግም የተመሰገነ ነው። ለታላቅነቱም ፍጻሜ የለውም። ትውልደ ትውልድ ሥራህን ያመሰግናሉ። ኃይልህንም ያወራሉ።" መዝሙር (145):3-4

እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል አንዳንድ ነገሮችን ካደረገ በኋላ እነዚህ ነገሮች ከተከታታይ ትውልድ እንዳይሰወሩ የድርጊቱን ትንቢታዊ ዓላማ ለትውልዱ አባቶች ይገልጻል። ከጥንት የተሠወሩ ምስጢራት መገለጥ አለባቸው። መንፈሳዊ ትውልድ በምድር ላይ የመመሥረትና የእግዚአብሔርን ግርማዊነት ለተከታታይ ትውልዶች ሳይዛነፍ በቀጥታ የማስተላለፍ ሂደት ይህንን ይመስላል።

> **" አፌን በምሳሌ እከፍታለሁ ከቀድሞ ጀምሮ ያለውን ተምሳሊት እናገራለሁ። የሰማነውንና ያወቅነውን፣ አባቶቻችን የነገሩንን፣ ለሚመጣ ትውልድ ከልጆቻቸው አልሰወሩም። የእግዚአብሔርን ምስጋናና ኃይሉን፣ ያደረገውንም ተአምራት ተናገሩ። ለልጆቻቸው ያስታውቅ ዘንድ፣ ለአባቶቻችን ያዘዘውን ምስክር በያዕቆብ አቆመ። በእሥራኤል ሕግን ሠራ፣ የሚመጣ ትውልድ የሚወለዱም ልጆች ያውቁ ዘንድ፣ ተነሥተው ለልጆቻቸው ይናገራሉ። ተስፋቸውን በእግዚአብሔር እንዲያደርጉ የእግዚአብሔርንም ትዕዛዙንም እንዲጠብቁ።"**
>
> ***መዝሙር (78):2-7***

የመጨረሻ ውጤቱ፡ የእግዚአብሔር ታላቅነትና ለሕዝቡ የሠራቸው መልካም ሥራዎች ምስክርነት ያለማቋረጥ ለተከታታይ ትውልዶች በመድረስ እያንዳንዱን ትውልድ ወዲያው መልእክቱ እንደደረሰው "ተነስቶ" ያንን የሰማውን የትንቢት ቃል ከፍ ባለድምጽ ለቀጣዩ ትውልድ ("ለልጆቻው" ቁ.6) እንዲናገር ማድረጉ ነው። እያንዳንዱ መንፈሳዊ ትውልድ ቀድሞት ከነበረው ትውልድ ይልቅ ጠንካራና ቃሉን (ለልጆቹ) በመናገር በኩል የበረታ ሊሆን ይገባል። ምስክርነቱ ከፊት ይልቅ የጠነከረ መሆን አለበት። ትውልድ ተስፋውን በእግዚአብሔር ላይ ባጠነከረ መጠን ተደብቀው የቆዩ አዳዲስ እውነቶች ወደ ብርሃን ሊወጡ ያስፈልጋል።



*የአሁኑ ዘመን የቤተክርስቲያን ተሃድሶ*

የሚተላለፈው ነገር የእግዚአብሔር ብርታትና ኃይል ነው። የሽግግሩን ትውልድ በዋነኛነት የሚገልጡት እነዚህ መለኮታዊ ባህሪያት ናቸው። እነዚህ ቃላት በጥቅሉ የሚናገሩት አንድ መንፈሳዊ ትውልድ ወደ ሽበት ሲመጣና የተጠራቀመ የሕይወት ኃይሉን ሲጨርስ እግዚአብሔርም ደግሞ በመንፈስ ወደ ሚቀጥለው ደረጃ ሊያልፍ ባለበት ሁኔታ ከዚህ ከአረጀው ትውልድ ወደ ሚቀጥለው ስለሚተላለፉት ውርሶች ነው።

> **" እስካረጅም እስክሸመግልም ድረስ ለሚመጣ ትውልድም ሁሉ ክንድህን ኃይልህንም ጽድቅህንም እስክነግር ድረስ አቤቱ አትተወኝ።"**
>
> ***መዝሙር (71):18***

"ክንድ" (በእብራይስጥ ዜሮዋ) ተፈጥሮአዊና ጥሬ የሆነ ችሎታን አመልካች ሲሆን በመጽሐፍ ቅዱስ ስለጦር ሠራዊት ኃይል የሚናገር ነው። በሚቀጥለው ትውልድ ላይ የማያቋርጥ ተጽእኖ እንዲኖር ፍጹም የሆነ የእግዚአብሔር ኃይልና የተዋጊነት ብቃት እንዲተላለፍ በማድረግ ላይ ያተኩራል። ስለዚህ ወደ ተሀድሶ የሚያሸጋግረው ትውልድ ጉልህ የሆነን የእግዚአብሔር ኃይል ክንድ እያንጸባረቀ በኃይል ይወጣል።

"ኃይል" (በእብራይስጥ ጌቡውራ) ኃይለኛ በሆነ የጥበብ መገለጥና በመንፈስ ቅዱስ የሆነ ትክክለኛነት የታጀቡ ድርጊቶችና ክንውኖችን ያመለክታል፣ በማስተዋል የተመራ ችሎታ፣ በምክር የለከነ ኃይል ነው። ለአንድ የተሀድሶ ትውልድ የተለቀቁ መለያ ምልክቶች ይህንን ይመስላሉ።

መዝሙር (48) በምድር ላይ ቤተክርስቲያን መግባት ስላለባት የጽዮን ይዞታ ካብራራ በኋላ በጽዮን ውስጥ ያሉትን ታላላቅ ዕውነቶች ለሚቀጥለው ትውልድ ማስተላለፍ እጅግ አስፈላጊ መሆኑን በአጽኖት ያሳስባል። እየታወጀ ያለው ደብዛዛና የፈዘዘ መገለጥ ሳይሆን እግዚአብሔር በምድር ላይ ሊመሠርት ያላቸው ነገሮች ጉልህና ጠንካራ የቅርጽና የውስጣዊ ባህሪ ማብራሪያ ነው።

**" ጽዮንን ክበቡአት፣ በዙሪያዋም ተመላለሱ፣ ግንቦችዋን ቁጠሩ፣ በብርታትዋ ልባችሁን አኑሩ፣ አዳራሾዋን አስቡ፣ ለሚመጣው ትውልድ ትነግሩ ዘንድ::"**

**መዝሙር (48) : 12-13**

የሽግግሩ ትውልድ ይዞታ ሊሆን መታወጅ ያስበት ነገር አስቀድሞ በእኛ መመላለስ፣ ዙሪያውን መሄድ፣ መቁጠር፣ ልብ ብሎ መመልከትና ማስተዋል የተገኘ ምስጢር ነው:: ለተከታዩ ትውልድ መተላለፍ የሚኖርበት የዚህ ጠንቃቃ ምርምርና ጥናት ውጤት ነው::

ከዚህ በላይ ያጠናናቸው ነገሮች የተሀድሶ ትውልድን ትክክለኛ ማንነትና ተጨባጭ ባህሪ በድጋሚ የሚያብራ-ሩልን ናቸው:: በጥንቃቁ የተላሰፈን ሙሉ በሙሉ የታወጀን የእግዚአብሔር ክንድና ኃይል መገለጥ የተቀበለ ትውልድ ነው:: መንፈሳዊ አባቶቹ እስከ ዛሬ ያከናወኑትን ሁሉ የሚበልጥ ሥራ በመሥራት የእግዚአብሔርን ክብር ካሁን ቀደም ታይቶ በማይታወቅ ድምቀት ለዓለም እንዲታይ ማድረግ የሚችል የዓላማ፣ የግልጽነት፣ የልምድና የትንቢታዊ ችሎታ ትውልድ ነው:: እስቲ አሁን ወደ ተሀድሶ ይዞታዎች በሚደረግ ሽግግር መካከል ያለን አንድ ትውልድ የሚገልጹ አንዳንድ መርሆችና ባህሪያት ለመመልከት እንሞክር::

## የተሀድሶን ትውልድ ለይቶ ማወቅ

የእግዚአብሔር ቃል ሙሉ ማሕበረሰቦች ከአንድ የኑሮ ደረጃ ወደ ሚቀጥለው እንዴት እንደተሻገሩ በሚያ-ብራሩ ትረካዎች የተሞላ ነው:: ከግብጽ ባርነት ወጥተው ከምድረበዳው እልቂት የተረፉትን በዮርዳኖስ መካከል መርቶ ኢያሱ ወደ አዲስ የሕይወት ሁኔታ አምጥቷል:: ዘላኖች የከተማ ነዋሪዎች በመሆን ቀድሞ የነበሩትን በእግዚአብሔር የተጠሉ ጣኦት አምላኪ ሕዝቦች ከገዛ ምድራቸው አባርረዋል:: በሙስና የተጨማለቀው የኤሊ ሥርዓት ፈርሶ እግዚአብሔርን እንደገና በእሥራኤል ላይ ብቸኛ ባለሥልጣን የሚያደርገው የሳሙኤል ትንቢታዊ





ክህነት በሥፍራው ተተክቷል:: ከሳኦል አገዛዝ ወደ ዳዊት ዘመን የተደረገው ረጅምና መሪር ሽግግር ሀገሪቱን ወደ አዲስ ትንቢታዊ ገጽታ በማምጣት ቤተመቅደሱ ለሚገነባበት የሰሎሞን ወርቃማ ዘመን መንደርደሪያን ፈጥሯል:: እንደ ኢዮስያስ ያሉ ነገሥታት ደግሞ የአባቶቻቸውን ስህተቶች ከምድሪቱ ላይ በጥንቃቄ ፈልገው በማቃጠልና በሕዝቡ ልብ ላይ አዲስ የእምነትና የአገልግሎት መንደርደሪያዎችን በመገንባት ተሀድሶን ለምድሪቱ አምጥተዋል::

በሙሴ ዘመን የነበረው ትውልድ በፈርኦን ሥር ከነበረ ባርነት ነፃ ወጥቶ በረጅም የምድረበዳ ጉዞ ከእግዚአብሔር ጋር ወደሚሆን አዲስ ሕይወት የመጣ የተሀድሶ ትውልድ ነበር:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከየትኛውም ምዕራፍ ይልቅ ዘፀአት 12 የሽግግርን ወሳኝ ደቂቃ ለእይታ አጉልቶ በማቅረብ የብዙ የባርነት ዘመን ጸሎታቸው ወደ አንድ የእርነትና የለውጥ ደቂቃ መጠቃለሉን ወዳየንበት ወደዚያ አስደናቂ ሌሊት ቴክኖሎጂ ይወስደናል::

አሁን ደግሞ በተሀድሶ ዘመን የሚኖረውን ትውልድ ገላጭ የሆኑ ጥቂት ሁኔታዎች እንመርምር::

## *★ አንደኛ ሁኔታ:- በመከራው ውስጥ መጓዝ*

**" እንዲህም ሆነ:- እኩል ሌሊት በሆነ ጊዜ እግዚአብሔር በዙፋን ከተቀመጠው ከፈርኦን በኩር ጀምሮ በግዞት እስካሉት እስከ ምርኮኞቹ በኩር ድረስ የግብፃውያንን በግብፅ ምድር የተገኘውን በኩር ሁሉ፣ የእንስሳውንም በኩሮች ሁሉ መታ:: ፈርኦንም፣ ባሪያዎቹም ሁሉ፣ ግብፃውያንም ሁሉ፣ በሌሊት ተነሱ የሞተ የሌለበት ቤት አልነበረምና በግብፅ ምድር ታላቅ ለቅሶ ሆነ:: " ዘፀአት 12:29-30**

ተሀድሶ ማለት ሰው ትክክለኛ አቅጣጫውን ለቶና ግራ ተጋብቶ ነውጥ ባለበት ሁኔታ ሲመላለስ የሚከሰት

የአሠራር ውጤት ነው። ካሁን ወዲያ ልንቀጥልበት የማይቻለንን እስከ ዛሬ የኖርንበትን አንድ ሥርዓት ያመለክታል። ነገር ግን የገባንበትን ያንን ችግር በቅጡ ለይተን ልናውቀው ያስፈልጋል። ነውጥ ተስፋ ለመቁረጥና ለመጨነቅ ምክንያት ሳይሆን እግዚአብሔር አንድን የለውጥ ሂደት እያንቀሳቀሰ ለመሆኑ ምልክት ነው።

ሙሴን ወደ ፈርኦን እንዲገባ በላከው ጊዜ እግዚአብሔር የፈርኦንን ልብ ሊያደነድን ቃል ገብቶ ነበር - ተአምራቱን ሊያሳይበት ያንን ውጥረት የከረረበትን ሁኔታ መረጠ።

> " ያዘዝሁህን ነገር ሁሉ አንተ ትነግረዋለህ፣ ወንድምህም አሮን የእሥራኤልን ልጆች ከአገሩ ይለቅቅ ዘንድ ከፈርኦን ጋር ይናገራል። እኔም የፈርኦንን ልብ አፀናለሁ። በግብፅ ምድርም ድንቄንና ተአምራቴን አበዛለሁ። ፈርኦንም አይሰማችሁም። እጄንም በግብፅ ላይ አደርጋለሁ፣ ሠራዊቴንም የእሥራኤልን ልጆች ሕዝቤን በታላቅ ፍርድ ከግብፅ አገር አወጣለሁ። ግብፃውያንም እጄን በግብፅ ላይ በዘረጋሁ ጊዜ የእሥራኤልንም ልጆች ከመካከላቸው ባወጣሁ ጊዜ እኔ እግዚአብሔር እንደሆንኩ ያውቃሉ።" ዘፀአት 7:2-5

የለየለት አንድ የነውጥ ዘመን ሳይመጣ ሽግግርን ማየት አይቻልም። ከውጥረቱ ጀርባ፣ ሊለቀቅ የተዘጋጀ የእግዚአብሔር ዓላማ አለ። የግብጽን ሕዝብ የጨለማ አስተሳሰብ ሰብሮ የእግዚአብሔርን ኃያል እምላክነት ሊያሳያቸው የሚችለው ያ የገቡበት ብሔራዊ ፈተና ነበር። ተሀድሶ ለእግዚአብሔር ሕዝብ የነፃነትና የመሻሻል ዘመን ሊሆን ለአሕዛብ ደግሞ የእግዚአብሔር ኃይልና የመለኮታዊ ማንነቱ ምስጢር ማስረጃ ነው። ቤተክርስቲያን በአዲስ ጉልበት በምትሞላበት በዚህ ዘመንም ይሄው መርህ እየሠራ ይገኛል። እኩለ ሌሊት ውጥረቱ የሚከርርበትንና የለውጥ ወራት የሚጀምርበትን ነጥብ ያመለክታል። ለእግዚአብሔር የሥራ ሰዓቱ ነው። ትንቢታዊ ተስፋዎች ሁሉ ወደ





መገለጥ የሚደርሱበት በጸሎት የባከኑት ዘመናት በሰማይና በዚህም በምድር ተጨባጭ እንቅስቃሴዎችን አቀጣጥለው የሚታዩበት ጊዜ ነው። ትክክለኛ ጉዞውን ዘመኑ ባመጡ-ቸው ግጭቶች መካከል የሚጀምረው ትውልድ የመጪው ዘመን ትውልድ ነው። አስደንጋጩ የእኩለ ሌሊት የልቅሶ ጩኸት በግብጽ እምብርት ላይ ሲፈነዳ የዚህ አዲስ ትውልድ መወለጃና "ወደ ፊት ሂድ! " የሚለው ሰማያዊ ትዕዛዝ የመምጣቱ ምልክት ነው።

## *✶ ሁለተኛ ሁኔታ፦ ማሕበሩን ሁሉ የሚያነጻ መስዋዕት*

> " ለእሥራኤል ልጆች ሁሉ ተናገሩ በሉአቸ-ውም፦ በዚህ ወር በአሥረኛው ቀን ሰው ሁሉ ለአባቱ ቤት አንድ ጠቦት ይውሰድ። "
>
> ዘፀአት 12:3-5-6

የተሀድሶ ትውልድ የሽግግሩን ሂደት እውን ለማድረግ በሚንቀሳቀስበት አሮጌው ሥርዓት ሊሞት በመጨረሻ ጣር ላይ በሚገኝበት ሰዓት መስዋዕት የማቅረብ ስሜት ሊነሳሳ ይገባል። ቀኑ ሥፍራውን ለሌሊቱ በሚያስረክብበት በምሽት ሰዓት (Twilight) በጉን እንዲ-ሰውት ጥብቅ መመሪያ ተሰጣቸው። ኢያሱ ከነአንን ለመውረር ሁለተኛውን ትውልድ በኢያሪኮ ሜዳዎች ላይ እያዘጋጀ ሳለ አሁንም በምሽት ላይ የፋሲካውን የመስዋዕት ሥርዓት ሲደግመው እናያለን (ኢያሱ 5:10)። ማሕበሩ ሁሉ ከጥቂት ቀኖች በፊት ተገርዞ እግዚአብሔር የግብጽን ነውር ከላያቸው አንከባልሎላቸው የነበረበት ወቅት ነበር፣ ከፊታቸው እስከፊ የጦር ዘመቻ ይጠብቃቸዋል፣ መና ከሰማይ መዝነቡ በቅርቡ ያቆማል፣ ከዚያ በኋላ በድል ከሚገቡባት ምድር ፍሬ ሊመገቡ የግድ ነው፣ የአባቶቻቸው እንደሆነው ለእነርሱም የምሽቱ መስዋዕት ወደ አዲስ የሕይወት ደረጃ መተላለፊያ መንገድ ነበር።

ጠቅላላው የእሥራኤል ሕዝብ በአንድነት ሊፈጽ-መው የተሰጠው ሥራ ጠቅላላውን ሕብረተሰብ ለአንድ ተልእኮ (Mission) በጋራ እንዲቆም አስገድዶታል።

“የእሥራኤልም ማሕበር ጉባዔ ሁሉ ሲመሽ ይረዱት” በርካታ ቤተሰቦች በግብጽ ምድር እየጨላለመ በሚመጣ የተወሰነ ሰዓት ላይ በሕብረት የሚፈጽሙት መስዋዕት ራሱ እግዚአብሔር ብቻውን እንደፈጸመው አንድ ታላቅ መስዋዕት ሊቆጠር የሚችል ነው:: በነዚህ የተሀድሶ ወራት በመላው የክርስቶስ አካል ውስጥ ጥልቅ የሆነ የመስዋዕት ስሜት ሊነሳሳ ያስፈልጋል:: አሁን ስላሰንበት አሮጌ ሥፍራ ግራ ልንጋባና ወደ አዲስ ይዞታዎች ሰሚያሸጋግረን ሕዝባዊ ጉዞ (Migration) ከእኛ የሚጠበቀውን ዋጋ ሁሉ ሰመክፈል የተዘጋጀን መሆን አሰብን:: ያሄም ሊከናወን የሚገባው በተበታተነ አስተሳሰብ ሳይሆን የሰውጥ ልምምዳችንና ሰውጥ የሚያስነሳብን ተቃውሞ በሚፈጥ-ርልን አዲስ የአንድነት ስሜት በኩል ነው::

## ✶ ሦስተኛ ሁኔታ:- ትኩረት በግል ንጽሕና ላይ

> “ በዚህም ቀን ሠራዊታችሁን ከግብፅ አገር አውጥቼአለሁና የቂጣውንም በዓል ጠብቁት፣ እንግዲህ ይህ ቀን ለልጅ ልጃችሁ ለዘላለም ሥርዓት ትጠብቃላችሁ:: በመጀመሪያውም ወር በአሥራ አራተኛው ቀን በመሽ ጊዜ የቂጣ እንጀራ ትበላላችሁ:: ሰባት ቀን በቤታችሁ እርሾ አይገኝ፣ እርሾ ያሰበትን እንጀራ የሚበላ ነፍስ ከመጀተኛው ጀምሮ እስከ አገር ልጅ ድረስ እሥራኤል ማኀበር ተሰይቶ ይጥፋ”
>
> ዘፀአት 12:17-19

በሙሴ በኩል የመጣው የእግዚአብሔር ትዕዛዝ “በቤታችሁ እርሾ አይገኝ!” የሚል ነበር:: እርሾ ያሰበትን እንጀራ ሲበላ የተገኘ ማንም ሰው ከእሥራኤል ማህበር ተሰይቶ መጥፋት ነበረበት:: እርሾ ጉዞውን ዋጋቢስ ያደርገዋል::

መጻሕፍት ራሳቸው የዚህን ቃል መንፈሳዊ ትርጉም በግሰጽ ያስቀምጡታል:: እርሾ እግዚአብሔር የሚጸየፈ-ውንና ሊመሰክተው የማይወደውን የውስጣዊ ባህሪ (Corruption) ይወክላል:: የኃይማኖታዊ አስተሳሰብ እርኩስትና ፈሪሳዊ ልምምዶችን ብቻ ሳይሆን (ማቴዎስ 16:6) ወደ አዲሱ ልምምድ ገብቶ እንዳያቆሽሸው የሚያሰጋውን የአሮጌውን ተፈጥሮ የጥንት ልማድ ጭምር ነው::





> “ መመካታችሁ መልካም አይደለም:: ጥቂት እርሾ ሊጡን ሁሉ እንዲያቦካ አታውቁምን እንግዲህ ያለ እርሻ እንዳላችሁ አዲሱን ሊጥ ትሆኑ ዘንድ አሮጌውን እርሾ አስወግዱ፣ ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዶአልና ስለዚህ በቅንነትና በእውነት ቂጣ በዓልን እናድርግ እንጂ በአሮጌ እርሾ በክፋትና በግፍ እርሾም አይደለም:: ” 1ኛ ቆሮንቶስ 5:6-8

የአርሾ መርሀ የሚያስተምረን ትልቁ ሚስጥር አንድ ትንሽ ብልሽት ወይም ዝገት መስፋፋት የሚችል መሆኑን ነው (ጥቂት እርሾ ሊጡን ሁሉ ያቦካል):: በአዲሱ ልምምድና በአሮጌው መካከል ትልቅ የመሰያየት ገደል እስካልተቆፈረ ድረስ አሮጌው አዲሱን የማበላሸቱ እድል በጣም የሰፋ ነው:: አሮጌው እርሾ ጥርግ ብሎ መውጣት አሰበት. እንጂ ድግሱን ሊያረክስ እንዲቀላቀል አይፈቀ-ድስትም:: ጳውሎስ በእግዚአብሔር ፊት ሊኖረን ስሰሚገባ ወሳኝ የሆነ ውስጣዊ ዝንባሌና ግልጽነት ይናገራል:: እርሾ የሌሰበት ቂጣ ቅንነትና እውነት የተሞላውን ልብ ይወክላል::

## ✶ አራተኛ ሁኔታ:- ከግጭት ነፃ የሆነ የኑሮ ዘይቤ

> “ ከሂሶጵ ቅጠልም ጭብጥ ውሰዱ፣ በዕቃ ውስጥ ባለውም ደም ንከሩት፣ በዕቃ ውስጥ ካለው ደም ሁለቱን መቃኖችና ጉበኑን እርጩ ከእናንተም አንድ ሰው ከቤቱ ደጅ እስኪነጋ ድረስ አይውጣ፣ እግዚአብሔር ግብፃውያንን ይመታ ዘንድ ያልፋልና ደሙንም በጉበኑና በሁለቱ መቃኖች ላይ ባየ ጊዜ እግዚአብሔር በደጅ ያልፋል፡ አጥፊውም ይመታችሁ ዘንድ ወደ ቤታችሁ እንዲገባ አይተውም:: ”
>
> ዘፀአት 12:22-23

የሽግግር ወቅት አጥፊው ሊያጠፋ በትጋት የሚንቀሳቀስበት ወቅት ነው። በዚያን ሌሊት በግብጽ ምድር ሁለት በጭራሽ የተለያዩ ሁኔታዎች በመካሄድ ላይ ነበሩ። እግዚአብሔር ግብጻውያንን ይመታ ዘንድ እያለፈ ነበር። በዚያው ደቂቃ ግን ነፃ ሲወጣ በተዘጋጀው የሽግግሩ ትውልድ በደጁ ላይ እያለፈ ነበር። በእሥራኤል ቤቶች ሁሉ ላይ ሊያጠፋ ከተሰናዱ አጥፊዎች የሚያስጥል የእግዚአብሔር መለኮታዊ መከላከያ ተዘርግቷል። "ይመታችሁ ዘንድ አጥፊው ወደ ቤታችሁ ይገባ ዘንድ አይተወውም"።

ይሄ በዘመነ ተሀድሶ ያለውን ውስብስብ የሕይወት ውጣውረድ የሚያንጸባርቅ መንፈሳዊ ምሳሌ (Metaphor) ነው። ቤተክርስቲያን አንቀሳቃሽ በሆነ የእግዚአብሔር አሠራር ኃይል ወደፊት እየተነዳች ከባርነት በመላቀቅ ላይ ትገኛለች። ዘመኑ ለእግዚአብሔር ሕዝብ በሞገድ መካከል የተከሰተ የእረፍትና የደህንነት ዘመን ነው። ግብጽን ከሚያናውጣት መከራና ከአጥፊው እግዚአብሔር እጁን ዘርግቶ ሕዝቡን ይጋርዳል።

ለእግዚአብሔር ሕዝብ በዚያ ሁሉ እልቂት መካከል ከአደጋ ተጠብቆ በሕይወት መሰንበት ምስጢሩ ቀኑ እስከሚነጋ ድረስ ከቤት እንዳይወጡ የተሰጣቸው ትዕዛዝ ነው። ለደህንነታቸው በተደነገገው መመሪያ ሥር ጸንተው መቆም አለባቸው። በጉበኑ ላይ የተረጨው ደም ከአደጋ የተጠበቁ ለመሆናቸው ምልክት ሊሆን የሕዝብ ወደ ተሀድሶና የለውጥ ሽግግር እየገባ መሆኑን አመልካች ነው።

ዛሬም በእኛ ዘመን በላያችን ያለው የተሀድሶ ምልክት ነው በምድር ላይ እየመጣ ካለው ነውጥ ሊጠብቀን የሚችለው። ኢየሱስ ራሱ በምድር ላይ ሊከሰት ካለው የመጨረሻዎቹ ቀናት አመለካከትና አስተሳሰብ ጋር ተቃራኒ ወደሆነ የአስተሳሰብ ይዘትና አቋም መግባት አስፈላጊያችን ለለመሆኑ አስተምሮአል።

> " ጦርንም የጦርንም ወሬ ትሰሙ ዘንድ አላችሁ ይህ ሊሆን ግድ ነውና ተጠበቁ፤ አትደንግጡ፤ ዳሩ ግን መጨረሻው ገና ነው።"
> **ማቴ 24:6**





## *★ አምስተኛ ሁኔታ፡- በለውጥ ዘመን ነቅቶ የመጠበቅ አስፈላጊነት*

> **" ይህች ሌሊት ከግብፅ ምድር ስላወጣቸው ለእግዚአብሔር የተጠበቀች ናት፣ ይህች ሌሊት በእሥራኤል ልጆች ሁሉ ዘንድ እስከ ልጅ ልጃቸው ድረስ ለእግዚአብሔር የተጠበቀች ናት። " ዘፀአት 12:42**

"ለእግዚአብሔር የተጠበቀች" ተብሎ እዚህ ላይ የተተረጎመው ቃል በዕብራይስጥ "ሺሙር" ይባላል። ሌሊቱን ሁሉ ያለእንቅልፍ ነቅቶ መጠበቅን ያመለክታል። በተሀድሶ ዘመን መንፈሳዊ ንቃት እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው። ለመዘናጋት ሰበብ የሚሆኑብን ነገሮች ሁሉ ከእኛ ሊወገዱ ይገባል። ቤተክርስቲያንን ከሰማይ ለሚመጣው የመጨረሻው ቀን የክተት ጥሪ ንቁና ዝግጁ ሆና እንድትጠባበቅ በተለያየ መልክ የሚገለጡ ጨቋኝ ባህላዊ አስተሳሰቦች፣ የፍልስፍና ቀንበሮች፣ ሙትና ፍሬቢስ ልማዶች፣ አሳሪ ኃይማኖታዊ አመለካከቶችና አቋሞች መወገድ አለባቸው።

## (ልክ) በዚያ ቀን ...

እንግዲህ ፋሲካ ቀስ በቀስ እየተገለጡ ከሚመጡት የእግዚአብሔር ዓላማዎች አኳያ ወደ አዲስ የግንዛቤ ደረጃ ሽግግር ሊያደርግ ዝግጁ የሆነን አንድ ትውልድ የሚገልጡ ሁኔታዎችን በውስጡ ያካትታል። ፋሲካ ብርቱ የሆነን የእያንዳንዱን እሥራኤላዊ የግል ተሳትፎ የጠየቀ ነገር ነበር። አስቀድሞ የተገረዘና የምድሪቱ ነዋሪ ሊሆን ዜግነትን የተቀበለ ካልሆነ በቀር ባዕድ ሰው ከፋሲካው ድግስ ሲካፈል አይፈቀድለትም ነበር። ማንም ይሁን ማን ሰውዬው ያልተገረዘ መሆኑ ከታወቀ ያንን የጥርመሳ ምሽት ለማስታወስ ከተዘጋጀው የፋሲካ ድግስ ተካፋይ ሊሆን አይችልም (ዘፀአት 12:43-51)። ከዳር የቆመ ማንም በፋሲካው ሂደት ውስጥ መግባት አይችልም። ከግብጽ መውጣት ካለብህ ወደ ልምምድና ወደ ጉዞው ተቀላቅለህ መሳተፍ አለብህ።

በትንቢታዊ ድንጋጌ ተወስኖ የነበረው (የተቀጠረው) ጊዜ እስኪመጣ ድረስ ለአራት መቶ ሰላሣ ዓመታት ሳያቋርጥ የሕዝቡ ጩኸት ወደ እግዚአብሔር ይወጣ ነበር:: ሰማይ ምድርን የነካባት ያቺ አንጸባራቂዋ ደቂቃ መጣች፣ እና በዚያው እለት ከግብጽ ጭቆና ወደ ሙሉ ነፃነትና ወደ አዲስ የሕይወት ሥርዓት ሰብሮ መግባት ተቻለ::

> "እንዲህም ሆነ:- አራት መቶ ሠላሳ ዓመት ከተፈፀመ በኋላ በዚያ ቀን የእግዚአብሔር ሠራዊት ሁሉ ከግብፅ ምድር ወጣ::"
> ዘፀአት 12:41

የአሁን ዘመን ተሀድሶአችንም ሁኔታ ከዚህ ጋራ በእጅጉ የተቀራረበ ነው:: ለተሀድሶ ተዘጋጁ የሚለው ግልጽና ኃይለኛ ጩኸት ከሰማይ ተሰቅቋል፣ ትንቢታዊ በሆነውም የቤተክርስቲያን ጆሮ በኩል በምድር ተሰምቷል:: ከአንድ ጫፍ እስከሌላው ተንሰራፍታ ባለችው ቤተክርስቲያን ሁሉ የአዲስ ጉዞ አዋጅ እየተነገረ ሲሆን መንፈስ ቅዱስም በየክፍለ ጦሩ ተሰልፎ የሚጠባበቀውን የተሀድሶ ሠራዊት በየተራ እያንቀሳቀሰው ይገኛል:: ዘመናችን ተወዳዳሪ ያልተገኘለት የሰው ልጆች የሕይወት ዓላማ ፍጻሜ (destiny) ዘመን ነው:: ታላላቅ ገድሎች የሚከናወኑበት፣ እግዚአብሔርን በመገናኘትና ወደ መንግሥቱ በመግባት በኩል ኃይለኛ ጥርመሳ የሚታይበት ቀን ነው:: ዘመነ ተሀድሶ!

## ጌታ ኢየሱስ ሆይ ና!



## ከዚህ በፊት በፀሐፊው የተጻፉ መጽሐፍት::

**Other publications by**
**Noel Woodroffe**

*Understanding the Prophetic Dimension*
*The Ultimate Warrior*
*Spiritual Government*
*Governmental Prayer: The Warfare*
*Expression of the Apostolic*

**Coming Soon!**

*Uncovering Apostolic Technology*

የዚህን መጽሐፍ ተጨማሪ ኮፒ ለማግኘት ወይም አገልግሎታችንን በተመለከተ መገናኘት ለምትፈልጉ በሚከተለው አድራሻ መጠቀም ትችላላችሁ::


**Jubilee Reformation Centre**

**P.O. Box 1814, Code 1110**

**Addis Ababa**

**Ethiopia**

**Tel: 251-9-237659**

**E-mail: tekleab@telecom.net.et**


የአለም ጥርመሳ መረብንና (World Breakthrough Network) የኤልያስ ማዕከል (Elijah Center) አገልግሎትን በይበልጥ ለማወቅ ከታች በሚገኘው ድህረ ገጽ (website) መመልከት ይቻላል::

**www.wbnetwork.org**

**www.elijahcentre.org**

# ለተሀድሶ የተደረገ ጥሪ

ተሀድሶ የአንድን ሕዝብ የአሠራር ጉልበት (Operational Strength) ፡ መገለጦችን የመቀበል ደረጃ (Revelation Parameters) እና አጠቃላይ ማንነት በፊት ከነበረበት ዝቅተኛ ሥፍራ ወደ አዲስ ደረጃ ስለሚያሻግረው በምድር አቀፉ ቤተክርስቲያን ውስጥ አንድን አዲስ መንፈሳዊ ትውልድ የመፍጠር ብቃት አለው። ይህ ተሀድሶ በምድር ላይ ለየት ያለ ባህሪ ወይም የአመለካከትና አሠራር ሁኔታ የሚንፀባረቅበት ራሱን የቻለ አንድ መደብ ሕዝብ በማስገኘት የእግዚአብሔርን መንግስት የፊት ለፊት ጉዞ አዲስ ወደሆነ ደረጃ የሚያሻግረውን ችቦ ተሸካሚ ትውልድ በንቃት ያዘጋጃል።

ለተሀድሶ ተዘጋጁ! የሚል ግልጽና የማያሻማ የአዋጅ ድምፀ ከሰማይ ተስተጋብቷል። ትንቢታዊው የቤተክርስቲያን ጆሮ ያንን የአዋጅ ድምፅ ከምድር ሆኖ ሰምቷል። ለአዲስ ግስጋሴ ተነሱ! የሚለው የአዋጅ ነጋሪ ቃል በሁሉም የምድር አቀፉ ቤተክርስቲያን በሮች በዓለም ላይ እየተነገረ ሲሆን የእግዚአብሔር መንፈስም የተሀድሶ አራማጅ ሕዝቡን ያተለያዩ ክፍለጦሮች (Battalions) ለድርጊት በማንቀሳቀስ ላይ ነው። ዘመኑ እስከ ዛሬ በታሪክ ከታዩት ታላላቅ ወቅቶች ጋር ሲነጻጸር በዐይነቱ ተወዳዳሪ ያልተገኘለት ወሳኝ ጊዜ ነው።

ታላላቅ ድሎች የሚመዘገቡበትና ወደሚቀጥለው የእድገት ደረጃ ግዙፍ እመርታ የሚታይበት ቀን ነው። ዘመኑ የተሀድሶ ዘመን ነው።

## ስለ ፀሐፊው



ዶክተር ኖኤል ውድሩፍ ትሪኒዳድ - ዌስት ኢንዲስ (Trinidad , West Indies) በሚገኘው ጠንካራ ሐዋርያዊ የተሀድሶ ቤተክርስቲያን በኤልያስ ማዕከል (Elijah Center) ዋና መሪ ሲሆኑ በተጨማሪም ትንቢታዊና ሐዋርያዊ አገልግሎትን ለማስተማር ፡ ለማሠልጠንና ለማስፋፋት እንዲሁም የእግዚአብሔርን በአሁን እውነቶች ላይ የተመሠረቱ ዓላማዎች (Present truth purposes) በምድር ላይ በመግለጥ በጽናት የቆመ ኤላይጃ ሚኒስትሪስ ኢንተርናሽናል (Elijah Minsitries international) የተሰኘ ዓለም አቀፍ አገልግሎት ፕሬዚዳንት ናቸው።

በተጨማሪም በውስጡ እንደመረብ አሠራር የተያያዙና በዓለም ዙሪያ የተዘረጉ አያሌ ሐዋርያዊ አብያተክርስቲያንና ሌሎች የእግዚአብሔር መንግስት አገልግሎቶችንና መዋቅሮችን ጠቅልሎ የያዘው የዓለም ጥርመሳ መረብ
( World Breakthrough Network )መሥራችና መሪ ናቸው።

እርሳቸውና ባለቤታቸው ጁን ሦስት ሴት ልጆች አሉዋቸው።